228

የሌሊት ድምፆች

እና ሌሎችም ወጐች



ጋዜጣ
476/2000



በመስፍን ሃብተማርያም

የሌሊት ድምፃች

እና

ሌሎች ወገኖች

በመስፍን ሀብተማርያም

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1992

© ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1992

ስልክ ቁጥር 504470
504496

ፖ.ሣ. ቁጥር 12684

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የሸፋን ሥዕል መስፍን ሀብተማርያም

228

ጥቂት ስለወግ

«ወግ ጸሐፊው ክብር የለውም፤ ቢኖረውም ክብሩ ከሌሎቹ የኪነት ዘርፎች ደራስያን እጅግ ያነሰና እንደሌለ የሚቆጠር ነው» ይላል ታዋቂው እንግሊዛዊ ወግ ደራሲ አሌክሳንደር ስሚዝ። አባባሉንም ሲያብራራ «ጣዕም ላለው አዝናኝ ጽሑፍ ሁሌም መነሻው ቁም ነገር፣ መድረሻውም ቁም ነገር ስለሆነ፤ ደራሲው ሰዎችን ከነአስተሳሰባቸው፣ ከነአነጋገር ፈሊጣቸውና ከነተግባራቸው ከማንም ይልቅ መቅረብና እውነታውን መቅረጽ ይጠበቅበታል። ስለዚህም የዋሉበት መዋል፣ ገጠመኛቸውን ማዳመጥ፣ ድርጊታቸውን ማስተዋል እና እነሱን መምሰል ግዴታው ይሆናል። እናም ልምሰል ያለ ማንነቱን መርሳት ስላለበት ወግ እጽፋለሁ የሚልም ሰው በዕድሜም፣ በኑሮም ፣ በዕውቀት ደረጃም ከማይመጥኑት ጋር በየትኛውም ስፍራ ቦታ መዋል አይቀርለትም...» ይላል።

አሌክሳንደር ስሚዝ አልተሳሳተም። ወግ ጸሐፊው መፈናፈኛ በሌላት ኪሞስክ ውስጥ ሰሌን ላይ ተቀምጦ ቆሎ እየቆረጠመ ቢጫወት፣ ገብቶ የማያውቅበት ጠጅ ቤት ውስጥ የአረጋውያንን ጨዋታ እያዳመጠ፣ ከጠበቆች፣ ከነጋዴዎች፣ ከደላሎች፣ ከጡረተኞች፣ ከአናጺዎችና ከግምበኞች ጋር ቢወያይ፤ ማድቤት እሳት እየሞቀ እመቤቶቻቸውን እያነሱ የሚያወሩ የቤት ሠራተኞችን አኳኋንና አነጋገር ቢያስተውል ምንም አያስገርምም። እሱንም አያስገርመውም። ሲያሰኘው

ከሊስትሮና ከለማኝ ጋር ስለኑሮና ውሎአቸው ሰው አየኝ አላየኝ ሳይል ፒያሳ መሀል ቆሞ ያወራል። የሱ ብጤዎች የሚንቋትን፣ እሱም የማያውቃትን ሴትኛ አዳሪ ሻይ ጋብዞ ወዳጁ የሆነች ይመስል ያቃልዳል። እንዲያውም በወንጀል ሃያ ዓመት ታሥሮ ከወጣ ሰው ጋር ሲያወጋ፣ የለየለትን ዱርዬ ለተወሰነ ቆይታ በጥሞና ሲያነጋግር፣ የመስሪያ ቤቱን ዘበኛ ወይም ተላላኪ የሕይወት ዑደት በየዓውዳመቱ እያስታከከ ሲጠያይቅ... እንደመደበኛ ውሎው ይቆጥረዋል እንጂ ህብረተሰቡ ያገለላቸውና እኩዮቹ አይደሉም የሚባሉትን ግለሰቦች በይሉኝታ ለመራቅ ከቶም አይቃጣውም። ደግሞም ሁሉም ነገር እንደጠበቁት አይሆንምና እነዚህ ሰዎች የሚኖሩበት ህብረተሰብ ባስተማራቸው የእልኸኝነት ጠባይ ወይም በግል ብልሹነታቸው የተነሣ ቢሰድቡት፣ ቢሸረድዱትና ቢያንጓጥጡት ተስፋ ቆርጦ ዓላማውን አይለውጥም። በጎ ስሜቱ ለጊዜው የሚጎዳ ቢሆንም ቂም ሊይዝ ቀርቶ ጠልቶም አይጠላቸውም። ምኞቱም፣ ሩጫውም ከነሱ የሚያገኘውን በጽሑፍ ለማካተት ስለሆነ ርቆ አይርቃቸውም። ምክንያቱም እንደማንኛውም ከያኒ ሰውንና ስብዕናን ይወዳል። ከሁሉም በላይ ደግሞ «እኔ ማነኝ?» ከሚለው የክብር ጥያቄ «እነሱ እነማን ናቸው?» የሚለው የሙያው ጥያቄ ያመዝንበታል።

ወግ ጸሐፊው ሕይወትን፣ ተፈጥሮን፣ ኑሮንና እነዚህን የሚያጫፍሩትን ዐበይት ክስተቶች ከግለሰቦች እስከ ህብረተሰብ ባለው ማንነትና ምንነት ዙሪያ በገሀድ የሚታዩ

ድርጊቶችን በመመንዘር አካባቢያችንንና ዘመናችንን በይበልጥም ማንነታችንን (እኛነታችንን) ልንቀበለው በምንችለውና በሚያረካ ኪነታዊ ጉዞ እንድንቃኝ ያደርገናል። ወግ ጸሐፊው ሰዎች በግላቸው፣ ሰዎች ከሰዎች ጋር፣ ሰዎች በማህበራዊ ሕይወት፣ በአኗኗር፣ በሥራና በመሳሰለው መስክ የሚያጋጥማቸውን በጐም ሆነ ክፉ ገጽታ ከእውነታው በመነሳት በተጨባጭ ማሳየት ተግባሩ ነው። በተጨባጭ ስንል የልቦለድ ፈጠራ ሳይሆን የነበረውን፣ ያለውን፣ የሚኖረውን እንደምናየውና እንደምንሰማው ማቅረብ ማለታችን ነው። ይሄ ሲባል ግን የምናውቀው ግለሰብ ወይም የምናውቃት ግለሰብ እንደ ፎቶግራፍ ይቀረጻል ወይም ትቀረጻለች ማለት አይደለም። በዚህ ፋንታ ምንም እንኳ ወግ ደራሲው ከራሱም ከሌላውም የቀራረመውን ወይም የሚያውቀውን መነሻ ቢያደርግም፣ የብዙዎችን አስተሳሰብና ድርጊት በሚወክል (typical) በሚሆን ሁኔታ ነው ጽሑፉን የሚያካሂደው። ዋናው ቁምነገር በጅምላ ተጨምቀው የሚቀርቡ ጉዳዮች፣ ምናብ ከሚጨመርባቸው በስተቀር፣ እውነት መሆን አለባቸው። በአንዲት ምሳሌ ለማብራራት፣ አንድ ሰው ስለከተማችን የምሽት መዝናኛ ቤቶች ቢጽፍ፣ ወጉ በነዚያ ቦታዎች በየዕለቱ ሲደረጉ የሚታዩትን ከሐቅ ያልወጡ ጉዳዩችን የሚዳስስ ይሆናል። ነገር ግን፣ ከዚህ የሚቀጥለው አንቀጽ እንደሚተነትንልን፣ ወጉ እውነቱን ያንጸባርቃል ማለት እንደ ጋዜጣ ጽሑፍ በደረቁ ያቀርበዋል ማለት አይደለም። ምክንያቱም የኪነት ዘርፍ እንደመሆኑ የኪነትን ውበት ይጐናጸፋልና!

ወግ በምንነቱና በስነጽሑፍ ምደባው የኪነት ዘርፍ ከሆነ ውበት ይኖረዋል። ውበት ስንል በአጭር አነጋገር የሚስብ፣ የሚጥም፣ የሚያጓጓ፣ የሚያረካ፣ ደስ የሚል አጻጻፍ ማለት ነው። ወግ ውበትን ሲላበስ የልቦለድ ያህል ይጥማል። በጉጉት መነበብ ብቻ ሳይሆን ሳይሰለች ተደጋግሞ ይነበባል። ተነቦ አይረሳም። ሁሌም እንደአዲስ በተለያዩ ወቅቶች ቆይቶ ሲነበብ የአርኪነት ደረጃው አይቀንስም። ኪነት ዘላለማዊ ናት የሚባለው ለዚህ ነው።

ጥሩ ወግ ብዙ ነገሮችን የሚያካትት ቢሆንም ዋና ዋናዎቹን ለመዘርዘር ያህል የቋንቋው ማራኪነት፣ የአቀራረቡ ሚዛናዊነት፣ የምሳሌ ምቹ ምርጥ መሆን፣ ጠቅላላ ምጣኔና ማዝናናት መቻል የሚሉትን ብንጠቅስ ላሁን በቂ ይመስለኛል። በተለይ ማዝናናት የወግ ዋነኛው ባሕርይው መሆኑ መታወቅ አለበት። (ሙያነክ ወይም Professional essay የሚባለውን አይመለከትም!) ማዝናናት ሲባል ፈገግ ማስደረግን፣ ማሣቅን የሚያጠቃልል ቢሆንም በተራነት የማይጠበቅ ትግርምት፣ የማይረሳ አድናቆትንና 'እንዲህ ነው ለካ!' የሚያሰኝ የመንፈስ ደስታን በአመዛኙ የሚጨምርም ነው። ዘና እያደረጉ፣ እያዋዙና እያሳቁ ቁምነገርን አሾልኮ መወረወርም የወግ ባሕርዩ ነው። ሆኖም ማዝናናቱም ሆነ ቁምነገር ጣል ማድረጉ መከወን ያለበት አንባቢው የሚያውቀውን ነገር እንደ አዲስ አለማምሮ በማሳየት በግርምት እንዲከታተለው በማድረግ ነው። ለመሆኑ በወግ ውስጥ እንደምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ

አዝናኝ ትዕይንቶች ምን ሊመስሉ ይችላሉ? አሁን ለምሳሌ እናት አባቱ በምስጢር የደበቁትን ዕቃ እንግዶች ፊት የሚያወጣ ሕፃን፣ በቅናት ተጣልተው ቆይተው ንዴቱ ሲያልፍላቸው በፍቅር የሚላቀሱ ባልና ሚስት፣ ሞቅታው ሲብስበት ለልጆቹ የገዛውን ሙዝ ለቆሎ ሻጮች የሚያካፍል የጠጅ ቤት ደንበኛ ወይም ከሩቅ ሲያደንቁት ቆይተው ወንዱ አጠገብ ሲደርሱ አርእስት ድንገት ለውጠው ክርክር የሚጀምሩ ኮረዶች... በተቀነባበረ አገባብ ሲገለጹ ሳቅ ስለሚቀሰቅሱ አዝናኝ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚያው ጋር ደግሞ የዋህነት፣ ሞኝነት፣ ብልጠት፣ ማህበራዊ ልማድና የመሳሰሉት ባሕርያት ከሚጸፍበት ጉዳይ ጋር ተገናዝበው ይገለፁባቸዋል።

ወግ ውበትን ተጐናጽፎ አንባቢን ለማርካት እውነቱ ላይ ሳይጨምርና ሳይቀንስ የልቦለድን ባሕርያት እንደአግባቡ ወስዶ ይጠቀምባቸዋል። ባለፈው አንቀጽ ወግ የልቦለድ ፈጠራ አይደለም ያልነው እንደልቦለድ ገጸ ባሕርያትና ግጭት፣ ታሪክ እንደማይኖረው ለመጠቆም ነበር። ሆኖም እንደልብ መስቀልና ድንገታዊነት (suspense, surprise) ዓይነቶቹን የልቦለድ መሰረታዊ አካሎች በገለጻው ላይ ያውላቸዋል። ምልልስም ልክ እንደልቦለድ አቀራረብ በሚጥምና ነገሮችን በሚያጐላ መልኩ ውበቱን ያጠናክራል። በመሠረቱ እንደልቦለድ ደራሲው የነጋዴውን፣ የባለስልጣኑን፣የአራዳውን፣ የጠበቃውን የአነጋገር ፈሊጥ ወግ ጸሐፊው መያዝ መቻል አለበት። ከሁሉም በላይ የፈጠራ አጻጻፍ የጀርባ አጥንት የሆነው ምናባዊ አመለካከት

ሰዎችንም ድርጊቶቻቸውንም ብሩህ አድርጐ ለማሳየት ብቻ ሳይሆን ሥነጽሑፋዊ ጣዕም ለመፍጠርም ይጠቅማል። እንግዲህ ወግ ከተራ አጻጻፎች፣ ወይም ከጋዜጣ መጣጥፎችና (articles) ከዘገባ ወይም ከሪፖርት የሚለይበትና ኪናዊ በረከቱ ሊያረካ የሚችለው ውበት ስለሚኖረው ነው።

ስለዚህ ወግ ጸሐፊው ገና ብዕሩን ሲጨብጥ የቃላት ዓይነቶች ከነምስላቸው ይዥገሞደገሞዱለታል። ዓላማው በምናቡ አግዝፎ የሚያየውን ጉዳይ በጥሩ አቀራረብ አቆንጅቶ ወረቀት ላይ መቅረጽ ነው። እንደ አርእስቱ ወይም አርእስቱ ወደሚ መራው አቅጣጫ ትንሽ፣ ትልቅ ሳይል በነፃ መንፈስ በምናባዊ እይታው ጭልጥ ብሎ ይነጉዳል። ለተራው ዓይን ከመብረር ባሻገር ትርጉም የማይሰጠውን ንስር አሞራ ገና ከሚዋዥቅበት የዛፍ ቅርንጫፍ ላይ እንዳለ በምናቡ ምጥቀት ጨምሮ ያስተውለዋል። ማስተዋል ማለት ጠልቆ አርቅቆ ማየት ነውና በሚያማምሩ ዓይኖቹ ዳመናውንና አድማሱን እየቃኘ፣ ፀጥ ያለውን አየር በሚሰነጥቀው ማራኪ ድምፁ ታጅቦ በአየር ላይ በክንፎቹ ሲውዘገዘግ፣ መሬትን በኩራት ተጠይፎ ከጉሙ ጋር ላይ ታች እያለ ሲጫወት፣ እሱም እንደሰው ዘሮች የራሱ ልጆች በጐጆው ያሉት መሆኑን እያሰበ ቢገረም፣ የተገረመበትን ከአንዳች ጉዳይ ጋር አያይዞ ቢከትበው የዋህ አይሰኝም። ንስሩ ሰው የማይችለውን መቻሉ፣ ሰው ደግሞ በአዕምሮው ከንስሩ መለየቱ ውበት የተላበሱ ክስተቶች ናቸው።

ወግ ጸሐፊው እንደሂሳብ ባለሙያው በቅደም ተከተ ልና ደንብ ስለማይገዛ ከርእሰ ጉዳዩ ርቆ ሄዶ የመመለስ ነፃነት አለውና የተነሳበትን ዓላማ ሳይስት ውበት ወደጐተተው መሣብ ግዴታው ነው። ሕፃኑን፣ አረጋዊውን፣ ላብአደሩን፣ ወጣቱን የሚያይበት ዓይኑ የውበት መነፅር ስለሚያጠልቅ ከመንግስተ ሰማያት በቅጽበት የወረደ የሚመስል የጨቅላ ሕፃን አሳሳቅ፣ ሽምግልና ላይ ዕድሜ የሚሰራቸው መስመሮች ልዩ ሆነው ይታዩታል። ስለ እመቤትና የቤት ሠራተኛ፣ ስለቢሮ አለቃና ምንዝሮች፣ ስለወላጆችና ልጆች ቢጽፍ በመሃል የሚኖ ረውን ድርጊትና ሁኔታ ለመግለጽ ወደውስጣቸው ጠልቆ መግባትና ማንነታቸውን ውብ አድርጎ ማሳየት ይኖርበታል። ምናቡ የማይ ወስደው ቦታ የለም። የለመለመ ጉንጯ ተሸብሽቦ እሸት የመሠለ ጥርሷ ሻግቶ፣ የብርሃን ጉልላት ዓይኗ ሞጭ ሙጮ ለዕድሜ ያጐበደደችዋን ወይዘሮ ሃያ ዓመት ወደ ኋላ መልሶ የረሳችውን የቁንጅና ካባዋን አልብሶ የራሱን ሥጋና ደምግባት ቢፈጥርላት በተፈጥሮ አድናቆት ምናቡ ይዞት ሄዷል ማለት ነው።

የወግ ጸሐፊው ውበት እንደማንም ከያኒ ሁሌም በጥሩና በበጐ ነገሮች ላይ ብቻ ያተኮረ አይደለም። ኪነጥበባዊ ውበት በክፉውም አለና ሐዘንን፣ ፀፀትን፣ ማጣትን፣ በደልን እና የመሳሰሉትን የደስታ ተቃራኒ ገጽታዎች በሰዎችና በሁኔታ ዎች አስታክኮ ብሩህ አድርጐ፣ አግዝፎ፣ እንደማይረሳና እንደ ሚያረካ አቆንጅቶ መጻፍም የሙያው ድርሻ ነው።

ወግ ጸሐፊው በመስተዋት ይመሰላል። ምክንያቱም በአጻጻፉ ራሱን ያይበታል፤ ሌሎችም ራሳቸውን እንዲያዩ ያደርጋል። ክብር የለውም የሚባለው አንድም በራሱ ላይ ሲቀልድ በመቻሉ ነው። ቀልዱ ግን እንደ «ለፈገግታ ያህል» ብልጭ ብሎ ድርግም የሚል ተራ ቀልድ ሳይሆን ከዕለት-ተዕለት ኑሮ፣ ከሰብእና ድክመት፣ ከሕይወት ውስብሳቤና ከገጠመኝ ጋር የሚያያዝና ብዙዎችን የሚነካካ፣ በመንካቱ ግን የማያስ መርር ወይም የማያስቀይም ዓይነት ነው። ዘና እያደረጉ፣ እያቃለዱ፣ እያዋዙ ራሳችሁን እዩ ለማለት ከውበት በተጨማሪ የሰዎችን የተለያዩ የመደብ ጐራዎች በአስተሳሰብ፣ በባሕርይ፣ በአኗኗርና በአነጋገር ሁሉ በጥሞናና በዕቅድ ማስተዋል የወግ ጸሐፊው ዋነኛ መመሪያ መሆኑ መታወቅ አለበት።

ወገኖች ከየፊርጆ

አህያ

ግመል የበረሃ ባቡር የመሆኑን ያህል አህያም የገጠር ንጉስና የከተማ ታክሲ ነውና ውለታውን እንዲህ በቀላሉ የምና ልፈው አይሆንም። በኔ ግምት «አህያ ለአህያ ቢራገጥ፣ ጥርስ አይሳበር» የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር ያወጣነው ጠንካ ራነቱን አስበን፣ በጠንካራነቱ የሚያበረ ክትልንን ግልጋሎት ከጠቀሜ ታው አኳያ ተመልክተን ሳይሆን አይቀርም። እንዲያውም «ለአህያ ፈስ፣ አፍንጫ አይያዝም» ስንል እንኳ በንቀት ገጽታ ነገሩን ሸፈንፈን አድርገን በማስመሰል ይዘነው እንጂ የአህያን ቅዱስነት በልባችን ጓዳ እያንቆሻበልን ማወደሳችን ይመስለኛል።

አሁንስ ቢሆን አህያ ያልተወደሰ ማን ሊወደሰ ይችላል?! የአህያ ዘሮችን ብንሰድብ እንደማይሰሙንና ሰምተውም እንደ ማያምጹብን ስለምናውቅ ነው እንጂ ከነሱ ተለይተን መኖር እንደማንችል ለቅጽበት እንኳ ለመዘንጋት ስለሚቃጣን አይደ ለም። እቅጩን እንናገርና ከአህዮች አፈን ግጠን ከቶ የት ልንደርስ እንችላለን? ብንኮራባቸው የማይኮሩብን፣ ብንሰድባቸው የማይሰድቡን፣ ብንመታቸው የማይመቱን፣ እንዲያውም በኃይል ስንገርፋቸው ሳይለግሙ በደንብ የሚሮጡ፣ በደንብ ሲሮጡ እንደገና ስንደልዛቸው እጅግ በጣም የሚሮጡ የፍጡራን ሁሉ የዋሆች፣ ከዚያም በላይ ቅንና ታታሪ ሰራተኞች ናቸው።

አህያ አሁንም ቢሆን ታታሪ እንስሳ ነው። ከቶ ምንም ቢሆን የማይችለው ሽክም የለም። አትችልም ቢሉት እንኳን አፍ ቢኖረው ከትሕትናው የተነሳ ማንም ሳይጠይቀው ወይም ሳያፋጥጠው «እችላለሁ» እንደሚል አልጠራጠርም። እኔ ዝም ብዬ በነሲብ ሳስበው አንድ መቶ ኪሎ የመጫን አቅም ያለው ኮሳሳ አህያ እስከ ሰላሳ ኪሎ ግራም የሚደርስ ሌላ ሽክም ቢጨመርበት ጆሮዎቹን ወደኋላ እንደአንቴና ቀስሮ ባለቤቱ (ነጂው) የጣለበትን ጫና ከግብ ማድረስ አያቅተውም። አሁንስ ቢሆን «አህያ የማይችለው ዝናብ» ይባል የለ!

«አህያ እማይችለው ዝናብ» ማለት ኃይለኛ ዝናብ ማለት ነው። አህያ ጠንካራ ነው ማለት ነው። ጥንካሬው ከቆዳው ይሁን ከአህያው በውል የሚታወቅ ስታቲስቲክስ ያለ አይመስለኝም። ለማናቸውም ግን አህያ የማይችለው ዱላ ሲባል አልሰማሁም። ነገሩ «ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ» ዓይነት መሆኑ ነው። ዝናብ እንደሚችል አሳምሮ እየገባን አይችልም ማለታችን፣ ዱላ እንደሚያመው ሳይሰወረን አባባሉን ከዱላ ጋር አለማስኬዳችን ደከምኩ ለማይለው አገልጋያችን ያለንን ዝቅተኛ ግምት ያሳያል።

በርግጥ የራስህን ሃሳብ ተቃረንክ አትበሉኝ እንጂ፣ አህያ ዱላ የሚያስፈልገው ሰዓት አለ። እቤት የተመደበለት ቀለብ እያለ መንገድ ላይቆም እያልኩ ሳር ካልነጨሁ ይላል። በተለይ በዓመት አንዴ ከተማውን የሚያጥለቀልቀውን ሽንብራ እሸት

በጣም ይወዳል። የስራ ሰዓት ስለሚያስታጉል ያኔ ከዱላው ቢቀምስ አያስገርምም። እንዲያውም ከስራ መልስ ጭነቱ ሲራ ገፍሎት ሰው ከመገፍተር አልፎ ኬክ ቤት ሊገባም ይከጅለዋል። ይመታም ሲባል ግን የበሉትን፣ የጠጡትን ያህል ሲሆን አይ ገባም። ደሞ አንዳንዴ ፈጠን ብሎ አልሄድ ሲል፣ ወይም አለ ምክንያት ቆም ሲል (መቼም መዝናናት እሚባለውን ነገር እንደ ሆን አያውቅም) ማንቀሳቀሻ በትር ቢያርፍበት ኩነኔ አይሆንም።

እጅግ የሚያሳዝነው ግን፣ የመብራት ኃይል መኪኖች መሬቱን ቆንጥጦ ለመያዝ እንደሚዘረጉት መሳሪያ አስፋልቱን በእግሩ ተጭኖ እየረገጠ መላው ሰውነቱ ተገታትሮ እስኪው ተረተር ድረስ ከአቅሙ በላይ ሸክም አዝሎ ሲያቃስት የሚወ ርድበት የዱላ መአት ነው። እንደሰው ጮሆ ካላለቀሰ አያመ ውም ብሎ ማሰብን ምን አመጣው? ውሻ ሲመቱት እሪ ብሎ ያለቅሳል። ድመት ሲቆነጥጧት ዋይታዋን አታቋርጥም። እነሱ ለራሳቸው ብልጦች ናቸው። በብልጠት ደረጃ ከሄድን እሺ ብላ አትያዝም እንጂ በአለንጋ ቢገርፏት ከአይጥ ይበልጥ 'የገላጋይ ያለህ' የሚል ፍጡር የሚኖር አይመስለኝም። ምስኪን አህያ ግን ለዚህ አልታደለም። ጮሌ ከሚባሉት የቤት እንስሳት ጋር ምንም አግባብ ኖሮት አያውቅም።

እኔ አህያ የሚያሳዝነኝ ገና አስተያየቱን ስመለከት ነው። ስለእንስሳት አጥንቼ ባላውቅም የአህያ ዐይን ሩቅ ማየት የሚችል አይመስለኝም። አንገቱን ደፍቶ የሚሔደው ለትህትና

ሳይሆን ወይም ከዱላ ብዛት ለማጐብደድ ሳይሆን ሊሸፍን የሚችላቸውን የተወሰኑ ሜትሮች አጥርቶ ለማየት እንዲችል ነው። ፊት ለፊታችሁ ሲመጣ አንገቱን ዘወር የሚያደርገውም በእይታው ክልል ስለምትገቡለት መሆን አለበት። በተበታተነ አመለካከት ብዙ ቦታ ከመቅነዝነዝ በተወሰነ ክልል አጣርቶ ማየት መቻል ለአህያ ሳይጠቅመው አልቀረም። አለበለዝያማ በሚደርስበት ዱላና ግርፊያ የመኪኖችና የአስፋልት ጉድጓዶች ሲሳይ ሆኖ ይቀር ነበር።

እና አህያ ረጋ ባይል ኖሮ ብዙ አደጋ ይደርሰበት ነበር። ይሁን እንጂ የአህያ ጠባይ ይሄ ብቻ ስላልሆነ ሌላ ሌላውን መናገር ግዴታችን ይሆናል። ለምሳሌ አንዳንዱ ጭነቱ ወርዶለት እየሮጠ በሚሄድበት ጊዜ ቀዥቃዣነት ይታይበታል። አንገቱን ከጭንቅላቱ ጋር ወደኋላው እየመለሰ በመፈንጠዝ መልክ የሚያወጣው ድምፅ ለጆሮ ልዩ ቃና የሚሰጥ አስደሳች ቅላጼ ቢኖረውም በሩጫው ወቅት ሰው ለመገፈታተር ምንም አይቀረውም።

እንዲያውም ቀዥቃዣነቱ መረን የሚለቀው ተቃራኒ ጸታውን በሚያሽኮረምምበት ወቅት ነው። ያኔ ምድር ሰማዩ አይበቃውም። በተለይ በገጠር አካባቢ ከፍላጐቱ በመነሳት የደራውን ገበያ መበጥበጥ ልማዱ ነው። በዚህ ረገድ ተመልካቾችን እንደ ግዙፍ አውሬ ሊያስደነግጥ ይችላል።

ይሄ አንዳንዱ የሚከሰት ቢሆንም የአህያን የእርጋታ ባሕርይ ሊሸረው የሚችል አይደለም። አህያ ታጋሽ ነው። እንደመገረፉና እንደመቆሳሰሉ ወላልቆም አይቀር። የመድከሙን ያህል አንድ እግሩን እያቀያየረ ብድግ በማድረግ እረፍት እየወሰደ እራሱን ያድሳል።

ለማንኛውም ስለአህያ ያለኝን አንድ ቁጭት ልናገር። «አህያ» የሚለው ቃል ለስድብ መዋሉ ይገርመኛል፣ ያሳዝነኛል። «ደደብ» ማለት አይደለም? ታዲያ አህያ ምን ነግረውት፣ አስረድተውት ወይም አስተምረውት ምን ሊገባው ይችላል? ደግሞስ መሸከም እስካልረሳ ድረስ፣ ስራውን እስካ ላጓደለ ድረስ ለምን ለደደብነት ተምሣሌት ይሆናል? ያሳዝናል።

ስለአህያ ልጻፍ ማለት ለአንዳንዶች ያስገርም ይሆናል። ወረቀትና ቀለም ማባከን መስሎ ሊታይም ይችል ይሆናል። አህያን ከመጠን በላይ መንከባከብስ እንዴት ሊታይ ይችላል? ይኸውላችሁ «ኢዮር» ከምትባል ወርሐዊ የመዝናኛና የዕውቀት አድማስ መጽሔት የመጀመሪያ እትም ያነበብኩትን አስደናቂ ታሪክ እንዳለ እጠቅሰዋለሁ።

«ኤልተን ጆን ለአህዮች ወደር የለሽ ሕንጻ እያስገነባ ነው። የሮክና ሮል አቀንቃኙ ኤልተን ጆን እንደንጉሥ በራሳቸው እልፍኝ ውስጥ የሚንደላቀቁ ብርቅዬ የሚላቸው አህዮች አሉት። ከበርቴው ኮከብ ድምፃዊ ኤልተን በአገሩ ምድር በእንግሊዝ ከሚገኘው እርስተጉልቱ አህዮች የምድር

ሕይወታቸውን የሚቀጨበት ዕፁብ ድንቅ የሚያስብል «ቤተመጋዣ» የሕንጻ ስራ ያስጀመረ ሲሆን የዲዛይን ስራውን በሁለት ታዋቂ አርክቴክቶች እንዳሰራም ታውቋል::

«ከዚህ በተጨማሪ ይህ ሊገነባ የታሰበው ሕንፃ በመካከለኛው ዘመን ከተሰሩት የእንግሊዝ ነገሥታት ቤተ መንግስቶች፣ በተለይም በቅርቡ በእሳት ቃጠሎ ከወደመው የንግስት ኤልሳቤጥ የእረፍት ማሳለፊያ ሕንፃ ጋር ተፎካካሪ እንደሚያደርገው ከወዲሁ ተገምቷል:: ግንባታው ተጠናቆ አህዮቹ ወደ ቤተመጋዣቸው ከተዛወሩ ኤልተንም አሁን በጋራ ተዳብሎ የሚኖርበት ቤቱን እንደገና የማሳደስ አጋጣሚ እንደ ሚፈጠርለት ተናግሯል:: ይህን የታዘበ ጐረቤትም <ለራስ መኖሪያ የተፈለገውን ገንዘብ መከሰከስ አንድ ነገር ነው:: ለአህዮች ይህን ማድረግ ማለት ግን ራስን ከአህያ አለመለየት ነው> ሲል ይናገራል::»

የ"ኢዮር"ን ወግ እዚህ ላይ ቆም አርገን አንድ ጥያቄ ራሳችንን እንጠይቅ:: ይኸውም ጂ.ኬ. ቼስተርተን የኤልተን ጆንን ጐረቤት ትዝብት ቢሰማ ኖሮ እንዴት ያወግዝ እንደነበር ነው:: (እንግሊዛዊው ጂ.ኬ. ቼስተርተን ከአርባምቹ ዓመታት በፊት የነበረ የአጭር ልቦለዶችና ወጐች ዕውቅ ደራሲ ነበር::) ቼስተርተን በሚያዝናና መልክ የሚጽፋቸው ወጐች ጥልቅ አስተሳሰብና አስተያየት ያላቸው ነበሩ:: ከሁሉ በላይ ነገሮችን

ከሰዎች ለየት አድርጐ በሚያሳምን አኳኋን መመልከት ይወድ ነበር። በሚያስደንቅ ሁኔታ ጽሑፉም ይሳካለት ነበር።

ታዲያ አንድ ቀን የሚያስገርም ዜና ጋዜጣ ላይ ወጥቶ ያነባል። ሴትዮዋ ለንደን ከተማ ውስጥ ባማረ መኖሪያ ቤቷ ጥቂት አሳሞች ታረባና ለውሻና ለድመት (በተለይ ለውሻ) እንደሚደረገው እንክብካቤ ለአሳሞች በማድረግዋ ፖሊስ በንጽሕና ጉድለት ክሷት ፍርድ ቤት ቀርባ ትቀጣለች። ሁለተኛ ድርጊቱን እንዳትቀጥልም ብርቱ ማስጠንቀቂያ ይሰጣታል። ቼስተርተን ፍርዱን በመቃወም "On pigs as pets" (አሣማ ተወዳጅ የእልፍኝ እንስሳ) በሚል ርእስ ጻፈ። ሃሳቡ ከሞላ ጐደል «አሳማ ለምን የእልፍኝ እንስሳ አይሆንም? አሳማ ቅርፁ ያምራል—ደስ የሚል ክብ አፈጣጠር ከተንጠለጠለ ጆሮና ጥያቄ ምልክት ከሚመስል ጭራ ጋር የታደለ፣ ቆዳው ልስልስ፣ ቀለሙ ቆንጆ የሆነ ውብ እንስሳ ነው ...» የሚል ነው። ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ አጻጻፉ ከሕፃን ውበት ጋር አሳማን የሚያመሳስል ነው። እና ቼስተርተን ዛሬ ቢኖር ለምስኪኑ አህያችን ድጋፉን ይሰጥ ነበር የሚል ታስቦኝ በዚህ አጋጣሚ ጠቀስ አደረግሁት።

ኤልተን ጆን ግን ለአህዮች ያንን መሳይ እንክብካቤ ያደረገበት የራሱ ምክንያት ይኖረዋል። ልጆች ስለሌሉት የልጆቹ ምትክ አድርጐ ወስዷቸው ይሆናል። ለእንስሳት ካለው ውዴታ ተነሳስቶ ሊሆንም ይችላል። እንደኔ እንደኔ ግን ሰዎች

የሚንቁትና የዕድሜ ልክ ባርያ አድርገው በአገልግሎት የሚገ
ዙትን እንስሳ ዕረፍት ልስጠው ብሎ ለየት አድርጎ አስቦት
ቢሆን እሰየው ያሰኛል። ለአህያ ያለውን አዘኔታ በዚህ መልክ
ገልጾ በተንከባከበ፣ ጐረቤቱ መቅናት አልነበረበትም። በቅሎን
ያክል ኩሩ ፍጡር ለፅንስ የሚያበቃ አህያ፣ ከበቅሎ የበታች
ሆኖ መኖሩስ እንዴት አያሳዝንም?

ነገራችንን ለማጠንጠን እንደማኮብኮብ እናርግና አንድ
በጐ ነገር ስለአህያ ለመናገር እንሞክር። መቼም በስነ ጽሑፍ
ተረቱም፣ አፈ ታሪኩም እንስሳትንና አራዊትን በየአቅጣጫው
ሳይዳስሱ የቀሩበት ጊዜ የለም። ለምሳሌ አንበሳን ጦጢት
በልጣው ስታሸንፈው፣ ጉንዳን ለአንበጣ ትምህርት ሲያስተም
ረው፣ አንበሳ የሰውን ልጅ እንደእናት አባት ላሳድግ ብሎ
የሰውን ክፉነት ሲታዘብ፣ የነብርና የጅብ ጓደኝነት፣ የአይጦችና
የድመቶች አንድነት እና እነዚህን የመሳሰሉ ተረቶች ከማስታ
ውሳቸው መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

ሌሎች ብዙ የሚያስገርሙ ተረቶችም አሉ። ለናሙና
ያክል ከወጥመድ በዘዴ የወጣችው ቆቅ፣ የሷ ተቃራኒ የሆነው
ደግሞ ቆሻሻ የነካውን ስኳር በውሃ እያጠበ ያሟሟው ዝንጀሮና
ሉል ጓሮ አግኝቶ ምን ያደርግልኛል ብሎ የወረወረው አውራ
ዶሮ ይገኙበታል።

እነሆ ከነዚህ ጋር ሊጠቀስ የሚችል አህያን የሚያስ
መሰግን ተረት አለ። «አረንጓዴው ጓደኛዬ» በሚለው መጽሐፍ

ላይ የቂሎ ማሞን ተረት ብንመለከት እናቱ ስጋ ግዛ ትለውና መሬት ለመሬት ሲጮሁት ውሾች በለብት:: ቂሎ ማሞ ይሄን ያደረገው ከዚያ በፊት «ድመት ገዝተህ ና» ተብሎ በጭንቅላቱ ስለተሸከማትና ስለቦጫጨረችው፣ እናቱም ስሕተቱን ለማረም «በገመድ መጮተት ነበረብህ» ስላለችው ነበር:: በኋላ አንድ ቀን «አህያ ይዘህ ና» ተባለ:: ከነፍሱ በትከሻው ተሸክሞ ወደእናቱ ቤት ይዘድ ጀመር::

በዚህን ጊዜ የንጉሥ ልጅ ከአባቷ ቤተመንግሥት መናፈሻ ባለው በረንዳ ላይ ቁጭ እንዳለች ሁኔታውን ታስተውል ነበር:: ልዕልቲቱ አህያ የተሸከመ አንድ በእሷ እድሜ ያለ ወጣት ስታይ በሳቅ ፈነዳች:: ከትክት ብላ ስትስቅ የነበረባት በሽታ ለቀቃት:: ለካንስ በኋላ ከተረቱ ጠይቀን እንደተረዳነው ልዕልቲቱ ከተወለደችበት ቀን ጀምሮ እንዳውም ከዚያ በፊት ሁሉ ምንም ዓይነት ቃል ከአንደበቷ አፈትልካ የማታውቅ ዱዳ፣ ፍጹም ዱዳ ነበረች::

የልዕልቲቱ ዱዳነት ግን የዕለቱ ዕለት በቂሎ ማሞ አህያ ተሸካ ሚነት ሊመገድላት ቻለ:: ተረት መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ያየነውም ባይሆን ኖሮ ከወዲሁ «ያንን ልጅ አያችሁት? እንዴት የሚገርም ነገር ነው!» ብላ በቤተመንግሥታዊ ቋንቋ እንደተናገረች እንገምታለን:: ለማናቸውም አባቷ (ማለትም ንጉሡ) ልጁን አድናልኛል በማለት ሁለቱን አጋባቸው ይባላል! አህያ ሲባል ለካ በተረቱም ዓለም ባለውለታ ነው!

ባለውለታነቱ በዚህ ብቻ አይወሰንም። ፈረስና በቅሎ እንደልብ ባልተገኙበት ቦታ እነሱን ተክቶ ሲያርስ አይተናል። አጋሰስ ተብሎ እንደቀልድ ይጠራ እንጂ ሥንቅና መሣሪያ፣ ሌላው ቀርቶ ቁስለኛ እንኳ በዘመቻ ወቅት እንደሚያጓጉዝ ስንቶቻችን እናውቃለን?

እዚሁ አዲስ አበባ ከኮልፌ ገርጂ ድረስ ኩንታል ከሚያመላልሱ አህዮች መካከል አንዱ በመኪና የተገጨ ዕለት መሄድ ስላቃተው በሌላው አህያ ላይ ተጭኖ ወደሠፈሩ ሲሄድ መመልከቴ ትዝ ይለኛል። አህያ ለጓደኛው ባለውለታ የመሆን ዕድል ሲደርሰው ማየት ከአዘኔታ ጋር ደስ አያሰኝም?!

ፅልመታዊ አመለካከት

የነገሮች አካሄድ ሁልጊዜም ለሁሉም ሰው አንድ ዓይነት መልክ አይኖረውም። ለአንዱ የማይሆነው ለሌላው ይሆናል።

ይሁን እንጂ ሁሉም እንደተዋረዱ የሚሳካለትን የሕይወት አቅጣጫ ይመኛል። አትራፊው ለትርፉ፣ ደመወዝ ተኛው ለእድገቱ፣ ገበሬው ለአዝመራው፣ ባለሙያው፣ የጉልበት ሠራተኛው... ሁሉም በየመስኩ ሲሯሯጥ የውጤቱን ስኬታ ማነት በጉጉት ይጠባበቃል። ሊስት ሮው የበጋውን አቧራና የክረምቱን ጭቃ ይናፍቃል። ሬሳ ሣጥን ሻጩ ስለሞት አበክሮ ሲያስብ ይውላል። ከሰል ሻጭና ልብስ ተኳሽ አንድ ቤት ውስጥ ያለ ኪራይ ተቀመጡ ቢባሉ እንኳን አይኖሩም።

ታዲያ በእንዲህ አይነቱ የኑሮ መፍጨርጨር መሃል ከሥራ ትጋት በተጨማሪ በህብረተሰቡ አባላት ዘንድ እንደእድል ወይም አጋጣሚ እየተደረጉ የሚወሰዱ፣ ተወስደውም የሚለመ ዱና የግል ባሕርይ ሆነው የሚቀሩ ነገሮች አሉ። እነዚህን ነገሮች «እምነት» በሚል ሰፋ ያለ አርእስት ጠቅለል አድርገን ብንመድባቸው የሚያስኬድ ይመስለኛል። እስቲ ባንዳንድ ምሳሌዎች ቃኘት እናድርጋቸው። ሰውዬው የልኳንዶች ደንበኛ አይደለም። «እንዴት ነው እባክህ

የሥጋው ዋጋ ንረት?» ሲባል፣ «እስከናካቴው ወደፊት ባይናችንም አናየው» ይላል። ባለታክሲው «እንዴት ነው ሥራ?» ስትሉት፣ «አይ ታክሲ እኮ አበቃለት» ይላችኋል። ለመመንዘር የሚያወጣው የብር ዓይነት ግን ሌላ ነው። «ምን ትርፍ አለን ብለው ነው? ፀሐይ ይምታን ብለን ነው ቤት ከመቀመጥ» የሚለው አባባል እየተዘወተረ መጥቷል። የማይመስል ነገር መናገር ይሏል እንዲህ ነው። እንዲህ ያሉትን ሁኔታዎች ስንመለከት በእምነት ሽፋን ውስጥን ያለማሳየት ሙከራ ወይም ድብቅነት፣ ራስን ዝቅ አድርጎ በማቅረብ በምሥጢር መደሰት፣ የሌላውን ግምታዊ ግምገማ (speculation) ያላወቁ መስሎ በዘዴ ለማግኘትና አልፎ ተርፎ ተጠራጣሪነት እንደሚስተጋባበት ለመገመት አንቸገርም።

ይሄ በመሥሪያ ቤቶችም አካባቢ ይስተዋላል። ደመወዙ አድጐለት፣ ደረጃው ጨምሮ ተሳክቶለታል የምትሉት ሰው «የኛ ነገር እንደ ግመል ሽንት ምንጊዜም ወደኋላ ነው!» ሲል አጋጥሟችሁ አያውቅም? ጥሩ መኪና ገዝቶ «መቼም በእግር ከመሄድ...» የሚላችሁስ? አጋንንክ ባትሉኝ ፈረስ የሚያስጋልብ ቤት ሠርቶ «አንድ የወፍ ጉጅ ብጤ...» የሚል አለ። ጉዳዩ የትሕትና የሚሆንበት ጊዜ አለ። መመሪያችም ብት ሊል እንደሚችል አብሮ ይታሰብባችሁ። በዓይናፋርነት ወይም ራስን ከፍ ላለማድረግ እንደሚሰነዘርም መገመት አለባችሁ።

የሆነው ሆኖ ለቀና ጥያቄው ቀጥተኛ መልስን ለሚጠብቅ ሰው ከእምነት በደረጃውም ሆነ በመጥፎ ገጽታው ከፍ የሚለውና የሚስበው አምልኮአዊ እምነት (superstition) ነው። በአምልኮአዊ እምነት መለከፍ ማለት «አይቀናኝም» ማለት ብቻ አይደለም። ትናንትም፣ ዛሬም፣ ነገም፣ ተነገወዲያም ጥሩ አይሆንም ማለትም ጭምር ነው። በአምልኮአዊ እምነት የሚንቀሳቀሱ ሰዎች በጠቆረ ደመና ውስጥ የፀሐይን ብርሃን የሚፈልጉ፣ ጉርፍ ሲወርድ እያዩ ውሃ ወደአቀበት ሲፈስ በምናባቸው የሚያስተውሉ ናቸው። ነጭ ጠርሙስ ቢያዩ <ለምን ነጭ ሆነ?> ብለው ለማሰብ ባይችሉም እንኳ ሰማያዊ የሆነ የበሽታ ዓይነት እዛው በዛው ይፈጥሩበታል። ነገሮችን ሁሉ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣ ብሂል፣ አባባል እና ከንቱ አስተሳሰብ ጋር ስለሚያያይዙ በግል አመለካከታቸው ብሔራዊ «ባህል» ቀርፀው ለልጅ፣ ልጅ ልጆቻቸው እያስተላለፉ የሚኖሩ ናቸው።

ለአምልኮአዊ እምነተኞች «ነገ» እሚባለው ቀን ጠራቸው ነው። ምክንያቱም «ትናንትናም እንደዚያው ነበር»። የለበሱትን አዲስ ልብስ አሮጌ አርገው ያዩትና ክፉ ክፉውን የራሳቸውን «ዕድል» በቅፅበቱ መቅረፅ ይጀምራሉ። ልብሱ ቶሎ ያልቃል ወይም ሌባ ይሰርቀዋል። ወይም ማን ያውቃል በሽታ አብሮ ይዞ ይመጣ ይሆን?! በዚህ ብቻ አይመለሱም። የሰው ውራጅ መልበስ፣ መሐረብ መዋዋስና የተለቀቀ ወንበር

ላይ ቶሎ ሄዶ መቀመጥ፣ ሰውን ቸኩሎ ቀድሞ መጨበጥ ሁሉ ያስፈራቸዋል::

በዚህ ዓይነት አይጥ ልብሱን ሲበላበት፣ ባዶ እንሥራ የያዘች ሴት ወይም ጥቁር ድመትና ቀበሮ ሲያቋርጡት፣ መስ ተዋት ሲሰበርበት፣ የዓይኑ ቆብ ሲርገበገብ፣ ቁራ ቤቱ ላይ ቁጭ ብሎ ሲጮህ... የተለያዩ አምልኮታዊ እምነቶችን የሚያ ሳድር ሰው ሞልቷል::

እስቲ አሁን ደግሞ ወደሌሎቹ ሁኔታዎች ሻገር ብለን ከፍርሃት፣ ከብቸኝነት፣ ከኋላቀርነትና እንደወግ ከሚያዙ ፈሊጦች ጋር የሚያያዙ ጽልመታዊ አመለካከቶችን ዳሰስ ብናደርግ የሚከፋ አይመሰለኝም::

በመሠረቱ «ጽልመታዊ አመለካከት» ከ«አምልኮአዊ እምነት» ይለያል—የቀጭን መስመር ግንኙነት ቢኖራቸውም:: ትልቁ ልዩነታቸው አምልኮአዊ አመለካከት አያት ቅድመ አያቶች ያሉት መሆኑና ይሄኛው ራሱ በራሱ አያት ቅድመ አያት መሆኑ ነው:: ጽልመታዊ አመለካከት ያለው ሰው ጽልመትን እየወለደ የሚኖር እንጂ ከዘር ወረስኩ የሚለው አንዳችም ነገር የለውም:: ጽልመታዊ አመለካከት (pessimism) በቀላል አነጋገር መጪውን ጊዜ ጨለማ አድርጉ ማየት ማለት ነው:: የተዳፈነ የስቃይና የመከራ ፍሞችን በራስ አነሳሽነት አራግቦ ለነበልባሉ መስገብገብ ማለትም ነው:: ጽልመተኛው ሰው «አውቶብስ ምነው ዘገየ?» ስትሉት፣ «ጮማው መንገድ

ፈንድቶ ይሆናላ ጌታዬ...»፣ የሚልና «ነገ ለመሄድ አስቤ ነበር» ብትሉት፣ «አይሄዬ፣ እኔ አያምረኝም...» እሚላችሁ ዓይነት ሰው ነው። «ምኑ ነው ያላማረህ?» ብላችሁ ከጠየቃችሁት መመለስ የሚችል ዓይነት አይደለም። ሆኖም አንገቱን ወደጉልበቱ ዘቅዘቅ እያደረገ ሰለል ደከም ባለች ድምፅ በእርጋታ በሚያወጣቸው አፍዛዥ ቃላቱ ዞሮ ዞሮ እንደሚበልጣችሁ አትጠራጠሩ። ባያሳምናችሁም ለጊዜው ይስባችኋል።

ጽልመታዊ አመለካከት ያለው ሰው በንግድም ይሁን በሥራ ዓለም፣ በሌላም በሌላም ሙያ (ትልቅ ደረጃ ላይ የሚያደርስም ቢሆን)፣ በአስተዳደግና በፍቅር፣ በአኗኗር እና በመሳሰሉት ማህበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ በቂ ቦታ ያገኘ የማይ መስለው ነው። በኔ ግምት የትም ብትሄዱ «ማን ያውቃል? እስቲ ዝም በሉ...» የሚል የጥርጣሬ መነጽር የማይ ለየው፣ ክፉውን ነገር ካለበት ፈልጐ የሚያሸት፣ ጭንቀት አድማጭ ሰው በተአምር አታጡም። እንዲህ ዓይነት ሰው ምግብ የሚያ ላምጠው፣ መንገዱን የሚጓዘውና የቢሮ ፋይሉን ሁሉ የሚያስ ተካክለው ሚርት በማይለየው ድብቅ ሐሳቡ እየተዋጠ ነው።

በምሣሌያዊ አነጋገራችን ድመት «ሺ ቢታለብ ያው በገሌ ነው» አለች ይባላል እንጂ፣ «ምንጊዜም ቢሆን ተጠቅመን አናውቅም» በማለት ያለ ገደብ ማማረርን ሙያ አድርገው የያዙ ከሰዎችም መካከል አሉ። ጉዳዩ ከራስ ጋር መሰላቸት፣ ሌላው ከደረሰበት ደረጃ አለመድረስ፣ የሕይወት መክፈቻ

ቁልፍ እድል ነው በሚል እምነት መጠመድ፣ አካባቢንና ማህበራዊ ኑሮን መጥላትና በውስጣዊ ፍርሃት መብሰልሰል ሁሉ ያለበት ይመስለኛል።

በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የሚታየው ሁኔታ በዚህ ረገድ በትዝብት ሲቃኝ ከማስገረም አልፎ ያሳዝናል። አዲስ ጀማሪ ለሚሆን ግለሰብማ አፈቀላጤ ለመሆን ትንሽ የሚቀራቸው፣ እዚያው ጥርሳቸውን የነቀሉና «በጐ አሳቢዎች ነን» የሚሉ በየመሥሪያ ቤቱ አይታጡም። አንዳንዶቹ የምዝበራውን ሂደት ለማለማመድ ጭር ያለች ሰዓት ጠብቀው ሹክክ ብለው ድምጽ ሳያሰሙ የሚመጡ ናቸው። «ብዙ የማያውቁት ነገር አለ ጌታዬ...እኔ አስረዳዎታለሁ» ብለው ይጀምራሉ። ብዙ ካወሩ ላችሁ በኋላ «ሰው እንደሆነው መሆን ነው። መቼስ...» ብለው ይደመድሙና ሹልክ ብለው ይወጣሉ።

አንዳንዶች ደግሞ ስለቢሮ አደረጃጀት (የዕቃዎች አቀማመጥና ንጽሕና) ከብዙ ዓመት የሥራ ልምድ ተነስተው ምክርና አስተያየት እንስጥ ይላሉ። «ይቺን ወንበር ምነው ቢቀይሩልዎት፣ እስቲ ካልጠፋ ወንበር! መጋረጃው ደሞ ስስ ነው፤ በዛሬ ብርድ!» ማለት ይቀናቸዋል። «ትዝ ይለኛል እገሌ የነበረበት ቢሮ ነው። ያችን ስዕል እሱ ነበር የለጠፋት... ውጭ አገር ከሄደ የትና የት ሆነ ጊዜው?! ደግ ሰው ነበር። ቤቱ ደግ ሰው አይቀመጥበትም እንጂ...» ደሞ ቀጠል አርገው። ዞሮ ዞሮ አመጣጣቸው በቀና አስተያየት እንጂ በተንኮል አይሆንም።

የጐደለው ይሚላ ባዮች ናቸው። ብቻ ባስ ሲል ሻይ የምታመ ላልሰውን ልጅ «ያንን ወልውይው እንጂ! ምነው ጠማማ ማንኪያ አመጣሽ?!» ከማለት አይመለሱም።

በመሥሪያ ቤቶች አካባቢ ነገሮችን ጨለማ አድርገው የሚያዩና ለሌላው የሚያሳዩ ሰዎች ለቢሮክራሲ መንጠላጠያ ብቻ ሳይሆኑ የተጐነጐኑ ነገሮች እንዳይላሉ፣ የተወሳሰቡ ችግሮች እንዳይፈቱ ዓይነተኛ መሣሪያ የሚሆኑም ናቸው። ራሳቸው በሚኖሩበት ፍርሃትና ጭንቀት በተሞላበት ዓለም ሌላውም እንዲገባ ይፈልጋሉ። ውል የለውም ብለው በጭፍን የሚያምኑበትን የራሳቸውን ማህበራዊ አመለካከት ወደሌላው ለማጋባት ይጥራሉ።

ጽልመታዊ አመለካከት ወደአምልኮ ደረጃ ባይደርስም ከመጥፎ እምነት ጋር አብሮ የተወለደ ያህል ይቆራኛል። መስመሩ ምንግዜም ሠፊ ነው —ደግ ነገር የለበትም። «እንዲህ እንዲህ ሊሆን ነው» ለሚል ቀና አስተሳሰብ ጋሬጣ ነው። ለእንዲህ ዓይነቱ ብሩህ ምኞትና ተስፋ አማራጭ የሌለው አቋራጭ መልስ «አይሆንም፣ አያምረኝም» ብቻ ነው።

በቢሮዎች አካባቢ የሚኖር ፀለምተኛ ሁሉ ነገር የማይጥመው፣ አዲስ ሐሳብ የሚያስበረግገውና ከነበረው ልማድ ለየት ያለ አዝማሚያ እንኳ የሚያስኮርፈው ነው። ለሱ በመሥሪያ ቤቱ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች በጥቅሉ ፋይዳቢስ

ናቸው። «የረባ ሰው የት አለበት? ቤቱ ቤት መሰልዎት?» ከአፉ እማይለያት አባባል ናት። በሱ ግምት ዘበኛው ነዝናዛ፣ ተላላኪው ቀርፋፋ፣ ደመወዝ ከፋዩ ሽረኛ ነው። በሱ ግምት አለቃው እሱን አጋፍጦ ሲዞር የሚውል፣ ፀሐፊዎች በመታዘዝ ፋንታ መስተዋታቸውን ደጋግመው ማየት ደስ የሚላቸው፣ ክበቡ የማንም መጠራቀሚያ፣ የማስታወቂያ ሠሌዳው አሰሱን ገሰሱን መለጠፊያ፣ ስልኩ ሁሉ የማንም መጫወቻ ነው። መመረርና ማማረር የጽልመታዊነት ተጓዳኝ እንደመሆኑ፣ ያየውና የሰማው ቢያበሳጨው አያስገርምም። ወንበሩ ሰባራ፣ ቁልፉ ጠማማ፣ የሚጽፍበት ወረቀት ሸካራ እየሆነ ይታየዋል። «በቢሮው ደስ ተሰኝቻለሁ» ከሚል ይልቅ የሌለ ቢንቢና ትንኝ በሐሳቡ እየፈለገ ቢገድል እርካታ ያገኛል።

ፀለምተኛው ካላማረረ መኖር አይችልም። በመኪና ሰርቪስ ተበደልኩ ባይ ነው። ያ ቢሟላለትም እንኳ በጭንቀት ከመባከን አያርፍም። በደመወዙ ማነስ ላይ የዘመድ አሠራር ይታሰበውና በዚያ እንባ ቀረሽ ችግር አጋጠመኝ ሲል ይሰነብታል። ይሄም ሳይበቃው «ትእቢቱን ቢያዩት? ሰው ሲንቅ! ትናንት እዚህ ግባ እማይሉት ዛሬ ጊዜው ተለወጠና...» የሚላቸውና በሰርሳሪ ዓይኖቹ የጐሪጥ እየተከተለ በትኩረት የሚገመግማቸው የመሥሪያ ቤቱ ባልደረቦች አሉት። ለአዲስ ቢሮ ለማጅ «ልብ አትስጣቸው» የሚላቸውን ግለሰቦች በዝርዝር ያውቃቸዋል። አንጋፋው የቢሮ ሰው የዛሬ ስንት ዓመት በግቢው የተፈፀመውን «ጉድ» ጨርሶ የሚረሳ

አይደለም። ለሁሉም ጥቃቅን አሠራርና ሁኔታ አቃቂር ያወጣል። አቃቂር የሚያወጣለት ነገር ካጣ የራሱን ፈልጦ ማግኘት አይሳነውም። ለምሳሌ አንድ የቢሮ ጸሐፊ እንደማንኮራኮር ቢቃጣትና ሳታስበው እንደወንድ ልታፏጭ ሞክራ «ወይኔ! ምን ነካኝ» ስትል ቢያጋጥመው ባህልን አስታክኮ እሪ እያለ ሲያማርር ታገኙታላችሁ። ደሞ ክፉ ነገር ላይ ቀድሞ የሚደርስ እሱ ነው። ፍቅረኛችሁን በስልክ እየተ ጨቃጨቃችሁ የስድብ ቃላት ከአፋችሁ አምልጠው ሳያበቁ በሩን ከፍቶ ከች ይላል። በእዳ ሊያፋጥጣችሁ የሚመጣባችሁን ቁጡ ሰው የሚያገኘው እሱ ነው። እየመራ ጠረጴዛችሁ ድረስ ያስገባና መጽሔት ብጤ ሸብለል አድርጎ በረጅሙ ይተነፍስና ይቀመጣል። የሚስጥር ማስታወሻም ከጣላችሁ እሱን መጠየቅ ነው — እንዲህ ያለ ድብቅ ነገር ማግኘት ይቀናዋል።

ባጋጣሚ በሚደርሱ የተለያዩ ሁኔታዎች ፀለምተኛው አይታጣም። ኮሬንቲ የተያያዘ እለት፣ ሌባ ሊሠርቅ መሥሪያ ቤት ግቢ አጥር ሲዘል የተያዘ እለት፣ የሥራ ባልደረቦች ተጣልተው ሲደባደቡ ወይም የፍቅር ጨዋታ ሲለዋወጡ... በቦታው መገኘቱ የማይቀር ነው። ከዓይኑ እሚያመልጥ ነገር የለም። የኮታችሁ ቁልፍ ቢበጠስና የሱሪያችሁ ዚፕ አልዘጋ ብሎ በስፒል ብታያይዙት ከማንም በፊት የሚያየው እሱ ነው። ለእንዲህ ያሉ ነገሮች ተፈጥሯል ለማለት ይቻላል።

የመሥሪያ ቤቱን ፀለምተኛ በዚህ እንለፈውና ሌሎችን ጠቀስ አድርገን ነገራችንን እንቋጨው። ሁሉ ነገር የማይጥ ማቸው ከደጉ ይልቅ ክፉ ክፉው ብቻ እሚታሰባቸው ግለሰቦች በተለያዩ የማህበራዊ ሕይወት መስኮች አሉ። «ጮበዝ ተማሪ የታለ ዛሬ» የሚል መምህር፣ የቤት ሠራተኞችን ሁልጊዜ ሌባና ቀጣፊ አድርጋ የምታይ እመቤት፣ ጋራዥ ማመን እማይችል ባለመኪና፣ የሚገዛውን እቃ ሁሉ የሚጠራጠር ገበያተኛ በየቦታው አለ። አንዳንድ ጊዜ የሆቴል ምግብ በጭራሽ ምግብ ነው ብሎ የማያምን ሰው እጁን ታጥቦ ገና ቁጭ ከማለቱ አካባቢውን ከመሬት ተነሥቶ ሲገላምጥ ሊያጋጥ ማችሁ ይችላል። ይሄ፣ ይሄ ሁኔታ እንደቢሮው ሰው ማማረርና መበሳጨት ይታከልበታል።

ቢሮክራሲ

ስለቢርክራቶች ለማውራት ከየትና እንዴት እንደ ምጀምር አላውቅም። ጠቅለል ባለ መልኩ ግን መጀመሪያ ስለቢርክራሲ ጥቂት መናገሩ ሳይጠቅም አይቀርም። ወተትን ሲፈልጉ ወደላሚቱ መሄድም አለና! ቢሮክራሲ ስራን በተለያየ ስልት ማደናቀፍ፣ ባያደናቅፉም ማጓተት፣ ባያጓትቱም መጥፎ የሥራ ልምዶችን ኮትኩቶ አሳድጐ አዳብሮ ለነገው ትውልድ ሆነ ብሎ የማተበልና የማውረስ ሂደት ገኖ የሚታይበት የአሰራር ሁኔታ ነው። ቃሉ ቢ«ቢሮ» እና «ክራሲ» መጣመር የተፈጠረ ነው። እሱን የመሰሉ ሌሎች አባባሎች እንዳሉም እናውቃለን። ዲሞክራሲን፣ ኦቶክራሲን፣ ቲኦክራሲን፣ አሪስቶክራሲን ዓይነቶች ግሉቴ ነው። በነገራችን ላይ የማውቃቸው እነዚሁ ናቸውና ለምን ሁሉንም አልዘረዘርክም? በማለት አንዳንድ አንባቢዎች ባይከራከሩ ደስ ይለኛል። ሰው አላውቅም ቢል ምን አለበት? ሰው «የማውቀውን ያህል ብቻ ተናግሬ በዚያው ቢተናገርኩት ክልል የአምንታ ወይ የአሉታ አስተያየት ይሰንዝርልኝ» ቢልስ ደግ አይደለም?

እንግዲያው በዚህ ከተስማማን፣ አላውቅም ማለትን በማይፈቅደውና ቦሚያውቀው መጠንም ስለማይረካው ቢሮክራት ማንነት ላሚውታችሁ። ለምን እንደሆነ እንጃ፣ አለማወቅ የሚያስበረግገውን ቢርክራት ዛሬ በደንብ አስታወስኩት። ዱሮም በአእምሮዬ ብዙ ሳብሳላው ቆይቼ ነበር። ምናልባትም በአሁኑ

ወቅት ሐቁ ፍንትው እያለ ስለመጣ ይሆናል ይበልጡን ገሀድ እየሆነ ባልጠበቅኩት መስመር በጣም ጐልቶ ሊታሰበኝ የበቃው::

ስለዚህም የመጀመሪያው የቢሮክራት ዓይነት «አላውቅም» ማለት የሚቀፈው እንዲሆን ፈለግሁ:: ይሄ ቢሮክራት ብዙውን ጊዜ የትምህርት ደረጃው ዝቅ ያለ ነው:: ከፍ ያለ ቢሆንም እንኳን በወጉ የተኮተኮተ ወይም የዳበረ አይደለም:: ዲግሪም ቢኖረው በተለየ «ጥበቡ»፣ በዕድል አልያም በደረቅ ጥረት ያገኘው ሊሆን ይችላል:: ለነገሩማስ ዲግሪን ሁልግዜም የእውቀት ዋስትና (መንፀባረቂያ) ያደረገው ማነው?!

እና ይሄ ዓይነቱ ሰው በአመዛኙ ሲገመገም ትምህርት፣ችሎታ፣ በቂ ልምድም የሌለው ይሆናል:: ነገር ግን ከቀድሞው የቢሮ አለቃ ሆኖ እሚሾመው በዘመድ፣በአድልዎና በሌላም በሌላም መነሾ ብቻ አይሆንም:: «ይገባኛል» በሚለው ሽኩቻ ላይ በድፍረቱ የመድረክ ጨዋታ ብዙ ተጫውቶም ነው:: ስለዚህ «ልክ ነኝ» የተሰኘውን የሕይወት መመሪያው እንደትዳሩ አንከብክቦ ይይዛል:: «ልክ አይደለህም» የሚለውን ሰው «እንዴት?» ብሎ ከመጠየቅ ይልቅ ተኮሳትሮ ብቻውን መሆንን ይመርጣል:: በተቻለው መጠን ከሌሎች ራስን ማራቅ፣ ሲቀርቡት መንገድ መዝጋት እና ሌላም ሌላም ዘዴ ሲያጠና መዋሉን የተለየ ሙያው ያደርገዋል:: ፊት መንሳት ደሞ ሌላው ጥበቡ ነው:: ቢሮው ስትገቡ ለመቀመጥ እንኳ

ደጅ ያስጠናችኋል። በቀና መንፈስ ነገሮችን አይጀምር ላችሁም። የሚያስደነግጥበት አርዕስተ ነገር ቢያጣ እንኳ፣ ቢያንስ የሚነጫነጭበትና የሚያልጐመጉምበት አንዳች መነሻ ይኖረዋል። «ከክቡርነታቸው ቢሮ ቆሜ» የተሰኘው የሰይፉ መታፈሪያ ግጥም ትዝ የሚላችሁ ያኔ ነው። የነገር መትረየስ ይደገንባችኋል። አስፈሪ ፊት እፈታችሁ ይደቀናል።

ይህ ሰው በውሎው ሁሉ ጠባያችሁንና ጠቅላላ እንቅስ ቃሴያችሁን ከመከታተል የማይቦዝን ነው። የምትጠይቁትና የምታዋዩት ነገር ሁሉ የባለሥልጣንነት ካባውን የሚገፍበት ይመስለዋል። በልበ ንፋግነቱ ላይ ሰበብ ፈላጊም ነው። ለምሳሌ እናንተ ያላካችሁዋት ዝንብ ለስላሳ ጉንጩ ላይ ብታርፍ በእናንተ ላይ የሚያዝንና የሚቆጣ መሆኑን መዘንጋት የለባችሁም። የዚህ ቢሮክራት ዋናው ጠባዩ ስህተቱን አለማመኑ ነው። ሁልጊዜም ይከላከላል እንጂ እጁን ሊሰጥ አይቃጣውም። ማድመጥ አይችልም። ቀላሉ ነገር እንዲ ገባውም አይፈልግም። ታላቁ የግሪክ ፈላስፋ ሶቅራጥስ «ትልቁ ዕውቀቴ አለማወቄን ማወቄ ነው» ማለቱን በድምፅ ማጉያ ብትነግሩት ሃሳቡ ከሥልጣን መሰላል ላይ እንደ ተንጠለጠለ ስላለ ፈጽሞ አይሰማችሁም።

ሌላው ቢሮክራት ደሞ ይኸውላችሁ። ስታዩት ለስላሳ ነው — በመልክ ሳይሆን በጠባይና በአቀራረብ ጥሩ ሰላምተኛ ነው። ሽቁጥቁጥ ሲል የዋህ ይመስላል። አለባበሱ ሽክ ስለሚል

የሸቶው፤የኮለኛው ዓይነት **አፍንጫ ይሰባል**። በአስገራሚ ገጽታው ካያችሁት ጽጌረዳ **አታክልት መሀል** የቆማችሁ ሊመስላችሁ ይችላል። በኋላ **ግን** ማንኑቱን ስትደርሱበት ጽጌረዳምች አያስፈልጉም **የሚል ሆኖ** ታገኙታላችሁ። ጽጌረዳን እየጠላ እሾሁን ልሁን የሚል ነው። 'ይህች ዓለም ደጋጮችን አትወድም' ብሎ ያምናል። **ዓላማው ሮጠሀ ቅደም** ብቻ ነው። ተሹሞ ገንዘብ፣ አሳብቆ **ገንዘብ**፣ **አታሉ** ገንዘብ ብቻ ነው የሚያውቀው። ማንኑቱን ላጋልጠው ካላችሁ እናንተንም ሰነዶ ችንም የማጥፋት ረቂቅ ችሎታ አለው።

የሚያቅደው **ሁሉ** አይታወቅበትም። የመጀመሪያ መስትንግዶውና ተግባቢነቱ የሚደነቅ የሚሆነው ድጋሚ እስክትፈልጉት ብቻ ነው። ያኔ በድ ካልሄዳችሁ (ጉቦ ካልሰጣችሁ) በመጣችሁበት **እግራችሁ ይመልሳችኋል**። ማንኑቱ ምስጢር እንደሆነባችሁ **ግን** አይቀርም። ሌላው ቢቀር ከአንዲት ደሞዝ ያልተጨመረላት ኮሳሳ ታይፒስት አንደበት «እሱ እኮ ችሎታ ያለውን፣ **የሚሰራለትን** ሰው አይወድም!» ብላ ስታማርር አንድ ቀን **መስማታችሁ** አይቀርም። የሱን ማንነት ለመቋጨት ጉቦን ብቻ አስቦ የተቀጠረ፤ ለጉቦ የሚኖር፣ ባለጉዳይን በገንዘብ ዓይን ብቻ ቀርጾ የሚያይ ሁለመናው ሳንቲም አሽታችኑቱን የሚናገርበት እስኩት መልክ ያለው ቢሮክራት ነው።

ቢሮክራሲ አያልቅም። ትልቅ ትንሽ ብሎ መከፋፈሉም አይበጅም። አንዳንዴ ጊዜው ካመቸ ትንሹ ቢሮክራት የራሱን እመርታ ይጠቀምና ትልቁን ቢሮክራት ይሆናል። ያንን እንኳን ባይሆን እንደገባር ወንዝ ትልቁን እያጐላመሰ በራሱ ዓቅም ስራን ለማጫጫት አስተዋፅየ ያደርጋል።

ሌላው «ትንሽ» ሊባል የሚችል ቢሮክራት ደግሞ እነሆ። ትንሽ ሊባል የሚችለው ግን ኃላፊነትን ስለሚፈራና ስለሚሸሽ ነው እንጂ ከሥራ ጐታችነት አኳያ ካየነው ከሌሎች ቢበልጥ እንጂ አያንስም። ይሄኛው ገና የተቀጠረ እለት «ሐላፊነት ደግ አይደለም። ከጥቅሙ በስተቀር ሌላው እዳ ነውና የምታውቀውን አትስራ። የምትችለውንም <እኔ እንጃ> ብትል ይሻልሃል!» የተባለ ይመስል፣ የገዛ ፊርማውን እንኳን ስለማያምን እየደጋገመ የሚያረጋግጥ ነው።

እንዲህ ያለው ቢሮክራት ባለጉዳዮች ብቻ ሳይሆኑ የገዛ መስሪያ ቤቱ አዲስ ተቀጣሪዎች፣ቢሮው ድንገት የሚያገኛቸው ያልተለመዱ እቃዎች...አካባቢው ሁሉ ተጠራጣሪ ያደርጉታል። የክፋቱ ክፋት ደሞ ኃላፊነቱ ገንዘብን በሚመለከት ቁልፍ ቦታ ላይ ይሆናል። እሱ ካልፈረመ ገንዘብ ወጪ አይደረግም —ለውስጥ አሠራርም ሆነ ከሌሎች ባለጉዳዮችና መሥሪያ ቤቶች ጋር። ታዲያ እዛ ቦታ ተቀምጦ አላውቅም ባይ ነው።

የሚፈርመው ነገር ሁሉ እዳ ውስጥ የሚያስገባው ይመስለዋል። እሱ የወር ደመወዙን ከተበደረ ዕዳ አይባልም። የሶስት ወር ለሰርግ ለሌላም፣ ሌላም ቢበደር ዕዳ አይባልም። በሐላፊነቱ ከተሳሳተ ብቻ ነው ዕዳ ውስጥ የሚገባው። በመሆኑም ለራሱ ጥንቃቄ ሲል ለሌሎች ደንታቢስ አቋሙን የሙጥኝ ብሎ ይይዛል።

ታዲያ በዚህ ምክንያት የተነሳ ትንሹ ቢሮክራት በዕለትተዕለት አኳኋኑ ለጥንቃቄው ልቅ መንገድ የማይከፍት፣ በራሱ አስተሳሰብ ክልል ብልጥ የሚባል ፍጡር መሆኑን ልታውቁ ይገባል። ከተላላኪ አንስቶ እስከ ፀሐፊዎች ድረስ ያሉትን ጆሮ ጠቢዎቹ ያደርጋቸዋል።

ቢሮክራቱ በልዩ ዘዴው የተቆራኘውን አራጣ አበዳሪ ሁኔታ ለማወቅ የሰራተኞቹን ጭምጭምታ ያሰባስባል። ትንሹ ቢሮክራት ባለበት የገንዘብ ኃላፊነት ንክኪ ከአራጣ አበዳሪው ጋር ልዩ የጥቅም ግንኙነት እንደሚኖረው አይጠረጠርም። ጠንቃቃነቱ ምንግዜም እንደተጠበቀ ነው። ሲያወጣ ሲያወርድ የሚውለው ስለሳንቲም ስለሆነ ልብ ብላችሁ ካላስተዋላችሁት «ስነልቡናዊ ችግር ይኖርበት ይሆን?» ያሰኛችኋል። መቁነጥነጥ መብጀርጀር፣ ደግሞ አለምክንያት ድንገተኛ ሳቅ፣ የፊት መኮማተር፣ መፈታት፣ በሐሳብ መባከን፣ መሄድ፣ መመለስ... ሁሉ ይታይበታል። አትፍረዱበት። ቦታው ራሱ እንደዚያ ያስደር

ጋል። ገንዘብ ላይ የተቀመጠ ሰው ገንዘብን ካልመሰለ ከቶ ምን ዋጋ አለው?! አጠቃላይ ፍልስፍናው ይኸ ነው።

ኧረ ስለቢሮክራሲ ብዙም ጊዜ አልፈጅም ነበር እኮ —ተፎካካሪዎቹ መጡብኝ እንጂ። እነዚህ ደሞ ከማገልገል ይልቅ ለመከልከል የተዘጋጁ ናቸው። ከቀና መልስ ይልቅ «እኔን አይመለከተኝም» የሚሉ ናቸው። በዐውዳመት ማግስት ካጋጠ ሟችሁ ደግሞ «እንጃልህ የራስህ ጉዳይ ነው» ይሉና መኪና የሚነዱ በሚያስመስላቸው ቆንጆ ቁልፍ ጠረጴዛውን ደጋግመው ደብድበው በድንጋጤ ስትሮጡ፣ ፋይል ይዞ ከሚገባ ተላላኪ ጋር ያጋጫችኋል። የተፎካካሪ ቢሮክራቶች የሚያናድደው ጠባይ ምን መሰላችሁ? ገንዘብ የሚነጥቁም ባይሆኑ፣ ዓይናቸው መገኛ አቅጣጫውን አይሳት እንጂ፣ ዋናው ቁባቸው ገንዘብ አይደለም ለማለት ይቻላል። የርስ በርስ ቂም ወይም እኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ የሚል ልማድ ስላላቸው አንድ ቦታ ምልክት ብጤ (አጠር ያለች ፊርማ ቢጤ) አድርገው ወደሌላ ሊመሩት የሚችሉትን ጉዳይ (ፋይል) ተራ በተራ እየተያዩ ባለበት ያቆዩታል።

የለመዱት አሰራር ነውና ሶስት ቀንም ቆዩ አንድ ወር ለነሱ ልዩነት አያመጣም። ትንሽ ከፍ ብዬ እንዳልኩት ገንዘብ በጉቦም ሆነ በፈለገው መልኩ ቢያገኙ አይጠሉም። ትኩረታቸውን ወደዚያ እንዳያደርጉ ግን ኃይለኛ የሆኑ በጣም የሚበልጧቸው የበላዮች አሉባቸው። ስለዚህ የእነሱ አማራጭ

ቢቻልና ጊዜም ካገዘ ወደላይ መሳብ ያ ካልሆነ በርስ በርስ ሽኩቻ የራስን እልህ ተወጥቶ ባለጉዳይ ማንገላታት::

ስለነዚህ ተፎካካሪ ቢሮክራቶች ሁለት ወትሮአዊ ጉልህ ሁኔታዎችን መቅረጽ ይቻላል:: አንደኛው «እሱ ለምን አይሰራውም?» ወይም «ማን በሠራ ማን ሊመሰገን» በሚል የእስኪ-እናያለን ንትርክ መካከል ፋይል ይታይልኝ ባዩ ቆሞ እየተማፀነ፣ ሹራብ የምትጠልፈው ጸሐፊ ውብ ዓይኖችዋን ከወዲያ ወዲህ እያንከባለለች «ደሞ ተነሳባቸው» በሚል የተለመደ አመለካከቷ ሁኔታውን በሳቂታ ስሜት የምትከታ ተልበት ዓይነት ትርዒት ነው::

ሁለተኛው ደግሞ በተፎካካሪዎች የነገር ውጣ ውረድ ሳቢያ ዝንተዓለም የወሬ አርዕስት ሆኖ የኖረው የራሳቸው መስሪያ ቤት አሰራር (ይሄ ቤት በሚል የሚታወቅ) ጉድለቱ፣ ስሕተቱ፣ ደንቡና አንቀጹ፣ አስተዳደሩ፣ ኮሚቴው ሳይቀር ከነውሳኔው እየተነሳ ብርቱ ክርክር ሲመጣና «ጉዳዩ ይጠና» እየተባለ ባለጉዳዮችን የማንገላታት ሁኔታ የመፈጠሩ ነገር ነው::

እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን አንድ ነገር አለ:: የጥቅም ጉዳይ የማይሳካላቸው ተፎካካሪ ቢሮክራቶች ሰው በማጉላላት ይፅናናሉ:: ለምሳሌ የሚያውቁትን እንደማያውቁ መምሰል፣ ቁምነገር ስታወሩላቸው አርዕስቱን ወደሌላ መለወጥ፣ እናንተን ጉልተው ለረጅም ጊዜ በስልክ ማውራት፣

ተቀምጣችሁ ሌሎች እንግዶች ማስገባትና እነሱን ማስተናገድ... ምን ልበላችሁ፣ ዝርዝሩ ያሰለቻል።

መቼም ብዙ ነገር በልምድ ይመጣል ይባላል። ክፋት ግን ሱስ ደረጃ እንዴት ሊደርስ ይችላል?! አይገባኝም። ለምሳሌ ጉዳይ ይዛችሁ እቢሮው ገብታችሁ ምልክት (ፊርማ ብጤ) ካደረገላችሁ በኋላ ምንም ተጠቅሞ ላይጠቀም ከሱ ቀጥላችሁ የት ክፍል (ወይም ወደየትኛው ዘርፍ) መሄድ እንዳለባችሁ ሊነግራችሁ የማይፈልግ፣ ብትጠይቁትም እንዳልሰማ የሚሆን ልበ ንፉግ ሰው ሲገጥማችሁ ያለአግባብ እንድትደክሙ ያደረጋችሁን ሰው ማን ፈጠረው ትላላችሁ?

ጠጅ ቤት

ጠጅ በጣም የሚወድ አንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነበር። ገና ከልጅነቱ ልምዱን እያዳበረ ስለመጣ ሳይጠጣ ውሎ አያውቅም። አራተኛ ዓመት ደርሶ ለመመረቅ አንድ ሴሚስተር ሲቀረው «አትመረቅም» ተባለ። ምክንያቱን ሲጠይቅ «አንደኛ ዓመት ላይ ያልወሰድከው አንድ ትምህርት ስላለ እሱን በሚቀጥለው ዓመት መውሰድ አለብህ» የሚል መልስ ተሰጠው። እሱ ግን እየተማረ ክርክሩን ቀጥሎ በብዙ ውጣ ውረድ ተሰሚነት አገኘ። በመጨረሻም ጓደኞቹ የማይመረቅ መስሏቸው እያዘኑ ካባና ቆባቸውን ለብሰው ለምረቃው ስርዓት እንደተሰለፉ ሳያስቡት እሱም ለብሶ ከኋላቸው ከች ሲል ገረማቸው። «እውነት አንተ ልትመረቅ ነው? ተሳካልህ?» አሉና ጠየቁት። እሱም «ዕድሜ ለጠጅ ቤት፣ ክርክር እዛ ባልማር መች እረታ ነበር!» ሲል አሳቃቸው።

በዚህም ብቻ አልተመለሰም። የምረቃው ስነሥርዓት እንዳበቃ፣ ካባና ቆቡን እንደለበሰ፣ አበባውን በሁለት እጁ እንደያዘ፣ ከጓደኞቹ ጋር ከግቢው ሲወጡ «በቀጥታ ወደ አራት ሰላሳ አንድ!» አላቸው። አላመኑትም። «አራት ሰላሳ አንድ» በዩኒቨርስቲው ውስጥ ለትልቁ የማስተማሪያ አዳራሽ የተሰጠ ስም ነበር። በሱ አባባል ግን ሁሌም ወደሚያዘወትርበት ወደትልቁ የጠጅ ቤት አዳራሽ አራት ኪሎ እንሂድ ማለቱ ነበር። እዚያ ደርሰው ሲገቡ ከነቆቡና ካባው ያዩት ጠጪዎች

ሁሉ ተገረመ። እሱ ከምንም አልቆጠራቸውም። በቀጥታ ጠጪ ወዳጆቹ ወዳሉበት ዘለቀና «ደስ ብሎኛል፣ ደስ ይበላችሁ። በናንተ አምላክ ይኸው ለመመረቅ በቃሁ!» አለና ቀጂውን ሳይቀር ስሞ ተቀመጠ። ከዛ ጠጁን በብርሌው ምንዶቅዶቁን ተያያዘው። በርግጥም ጠጅ ቤት ክርክር ማካሄጃ መሆኑን ይኼ እውነተኛ ትርክት (anecdote) ያሳየናል። ከዚህ በተጨማሪ ጠጅ ቤት ምን ዓይነት ትዕይንት እንደሚካሄድበት በዚህ መንደርደሪያነት እስቲ ቃኘት እናድርግ።

ወደጠጅ ቤቶች ትዕይንት ለመድረስ በመጀመሪያ ትልቅ አስፋልት ፊታችሁ ላይ ተንጣሏል እንበል። ግራና ቀኝ ካማተራችሁ በኋላ አንድ የኮረኮንች መግቢያ ታያላችሁ። ታጠፉ። ልክ እንደታጠፋችሁ ወደል ውሾች በዙሪያችሁ ውር ውር ይሉባችኋል። ይናከሳሉ ብላችሁ ፍጹም እንዳትሰጉ። እንኳንስ ሊናከሱ ይቅርና አጥር ግቢ ውስጥ እየተንቆራጠጡ የሚጮሁትን መሰሎቻቸውን የማይቀርቡ፣ ጠጅ ቤት ሰፈር ተወልደው ያደጉ ሰላማዊ እንስሳት ናቸው። ከዚያው ብዙም ሳይርቅ ግዙፍ ድመቶች አጥንት መሳይ ይዘው በየግድግዳውና በየጣራው ሲሯሯጡ ታያላችሁ።

ከድመቶቹ አንዳንዶቹን የምትንቋቸው ዓይነቶች አይደሉም። ከጠጅ ቤቱ የጐድን ጥብስ ትርፍራፊ እንደልብ ስለሚቀራርሙ ኮሰስ ካለ ውሻ ጋር ጠብ ለመግጠም ወደኋላ የማይሉ ናቸው። ልትገቡ ሃያና ሰላሳ ሜትር ሲቀራችሁ የጠጁ ሽታ ያውዳችኋል። በተቀሙት ማር ተስፋ ያልቆረጡ አንዳንድ

ንቦች ክብብ ያደርጓችኋል። ከወደጓሮ መውጫ በኩል ትልቅ ባልዲ ይዞ ቆሻሻ ውሀ ቦዩ ውስጥ ለመድፋት ወጣ ብሎ ግራ ቀኙን የሚያማትር፣ ጠቆር ጐሰቆል ያለ፣ ቁምጣ ሱሪ የለበሰ፣ ባቱ ፍልጥ መስሎ የጠጠረ፣ ፀጉሩ የተንጨባረረ ሰውዬ ያጋጥማችኋል። ጠጅ ከምትበጠብጥ አንዲት እዛው ቤት ካደገች ወፍራም (ደንደሮ) ሴት የሚወረወርበት ስድብ መሣይ ቀልድ ቢዘገንናችሁም የወትሮ ጠባያቸው ነውና እምብዛም አይክበዳችሁ።

ለማናቸውም ጠጅ ቤት ልትገቡ ነውና እንዳትሰለቹ። ደሞ አስተያየት ከመስጠት ተቆጠቡ። ምክንያቱም «ፈጣሪዬ እንኳን ለዚህ አበቃኸኝ» ብለው የሚያመሰግኑ የሚመስሉ ጨዋ ጨዋ ሰዎች ስልክ እንጨትም ግንብም ጋ ቆመው ሽንት ያፈሳሉ። ለማኞች፣ ቆሎ ሻጮች፣ ልብስ አዟሪዎች፣ ዱርዬዎች... በሩን ከበው የቆሙበት የጠጅ ቤቱ መግቢያ ነውና አሁን ልትገቡ በሯ ላይ ናችሁ ማለት ነው። ብቻ ቦዩ መሸጋገሪያ ላይ ያለችውን የምታረገርግ ጣውላ በጥንቃቄ ልብ ብላችሁ ማየት አለባችሁ። በኋላ ስትወጡ ልትጥላችሁ ትችላለች —አታስተማምንም።

ግቡ፣ ደርሳችኋል። ከዚያ በመረጣችሁት አግዳሚ «ወንበር» ላይ ቁጭ ስትሉ «ነወር፣ይንበሩ፣» የሚሉ ትሁት ሰዎች ያጋጥሟችኋል። «ነወር» መባባል የዕድሜ ገደብ የለውም። ዓይነ ስውር አባቱን ቤት ለማድረስ ከሚመጣ ልጅና

ከቆሎ ሻጮች፣ ከልብስ አዟሪዎች በስተቀር ሁሉም ጠጅ ጠጪ የ«ነወር» ባለመብት ነው። ታዲያ ባንድ የሚያበቃ አይምሰላችሁ። ሽንት ቤት ስትመላለሱና ወይራ ጭስ አጨናብሷችሁ ስትመጡ ሁሉ ትሕትና አትነፈጉም። ከተቀመጣችሁ በኋላማ «ቆሎ ዝገኑ!» ስትባሉ ትዘግኑና ላታስቡት እፊታችሁ ገጭ ያለውን አደይ አበባ የመሰለ ጠጅ በብርሌ ማንዶቅዶቅ ነው።

ከዚያማ ጨዋታው ይመጣል። በያይነቱ። መቼም ጠጅ ቤት አሽሙር ሞልቷል። ድንገት ከየት መጣ ሳትሉ «ኧረ ንቦ አትናደፊ!» የሚል ዘፈን አይሉት ንግግር የማላዘን ዓይነት ድምፅ ትሰማላችሁ። ቆይ፣ ዝም በሉት። ጠጅ ቀጂው እስኪሰማው ነው።

በዚህ ዓይነት ጨዋታችሁን መኮምኮማችሁን ትቀጥላላችሁ። ከዛ ዓይናችሁን ወዲያ ወዲህ ስትማትሩ ብዙ ነገሮችን ታያላችሁ። የቤቱ ጣራ ሩቅ ነው። ኮርኒስ ቢኖረው ጠጪዎች የሚያድሙ ይመስል የትም ቢሆን የሰፋፊ ጠጅ ቤቶች ቆርቆሮ ባንድ በኩል እርቃኑን ነው የሚሆነው። የጣራው መራቅ ግን ምክንያት ሳይኖረው አይቀርም— በመጠጡ ላይ ሌላ የፀሐይ ግለት ለመከላከል። አሠራሩ የጋራዥ አይነት መምሰሉ ደሞ ሌላው ገጽታ ነው። እንዲያውም ነፋስ ቢጤ ለማስገባት አልፎ አልፎ ድመቶች የሚረማመዱባቸው ክፍተቶች ይኖራሉ። መጠጫው አግዳሚና

የውስጥ ቆርቆሮው አረንጓዴ የተቀባ ነው። ጠጅ ቤት ሲባል ቀለሙ ወይ አረንጓዴ ወይ ሰማያዊ ነው። ቢጫ ቀለም ብዙውን ጊዜ የማይፈለገው ከጠጅ መልክ ጋር ይፎካከራል ተብሎ ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ቀይ ቀለም ግን ለምን እንደማይፈለግ አይገባኝም።

ቆሎ አዟሪዎችና ልብስ ሻጮች ውር ውር በሚሉበት አዳራሽ ለማኞችም ከመለመን አልፈው ለድምፃቸው ማስተካከያ እንዲሆን አንድ ሁለቷን ሲቀማምሱ ይታያሉ። ሁሉም ጠጪ የተለያየ የራሱን ወሬ ስለሚኮመኩም አዳራሹ ቢያንስ ስልሳና ሰማኒያ ጉዳይ በአጀንዳ የተያዘበት ሊመስል ምንም አይቀረው። አንዳንዱ ይከራከራል። አንዳንዱ ይወራረዳል። የግል ትዝታውን፣ ተረቱንና ታሪክ ነክ ወጉን በያይነቱ እያወራ ሁሉም ይጫጫሃል። በዚህ ሁሉ መካከል «የዛሬን አያርገው... ወይኔ ካቺሳው... እምቢ በሉ ሰዎች...» የሚሉ ሰዎች ይኖራሉ።

ደሞ የጠጪዎቹ ማንነትና የወሬው ውጥንቅጥነትስ? ለምሳሌ አንዱ ግንበኛ፣ ሌላው ነጋዴ ነው። አንዱ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ጥርሱን ነቅሎ ያደገ ሲሆን እፊቱ ቁጭ ያለው፣ በደላላነቱ ብቻ፣ በቅልጥፍናውና በዘመናዊነቱ ፈረንሳይኛም እንግሊዝኛም የቀራረሙትን የመንግስት ሰራተኞች ሊያስንቅ ይችላል።

በቤተክህነት ያደጉ አዛውንት አዛው በዛው ቀላል በሆነው የህብረ ቅኔ ነገሮችን ጣል እያደረጉ «እባክዎን ደግመው ያሰሙን» ሲባሉ፤ ስለኑሮው ውድነትና ስለታክሲዎች ውጣውረድ ወይም ስለዛሬ ሴቶች ብልግና የሚያወሩ ሰዎች ድምፅም ከዛው ከአግዳሚው ሳይርቅ ይሰማል። እዚያ ስፍራ ለትዝብት እምብዛም ቦታ የለም። ልታዘብ የሚል ሰው አለ ቢባል እንኳን ተማሪዎቹ በፈጠሩበት ትግርምት ከራሱ ጋር እያልጐመጐመ ሲጃራውን የሚያከታትል አንድ ምስኪን መምህር ሊሆን ይችላል።

እውነትም የጠጅ ቤት ደንበኞች ከመልካቸው አንስቶ የተለያዩ ናቸው። «ጠጅ ቤት እንዴት ገቡ?» አትበሉኝ እንጂ የሸበተ ማራኪ ጺም ያላቸው ረጋ ባለ ትሕትና የታጀቡ ዐይነት ሰዎች አልፎ አልፎም ቢሆን ያጋጥማሉ። እንዲህ ያሉ ሰዎች አላግባብ ሲጐነትሏቸው አይወዱም። በሰለለ ድምፃቸው በንግግር መጋፋት ስለማይችሉም ረጋ ብለው እንደገቡ ረጋ ብለው ይወጣሉ።

የቀድሞውን አልጋ ወራሽ የመሰለ ሰልካካ ጐረምሳ አንዱ ጥግ ተቀምጦ በሚያምር ቀይ መልኩ ሳይኮፈስ ከአንዷ ቆሎ ሺያጭ ጋር ሲላፋ ቢታይም አያስገርምም። የቀበሌ ሰዎች «መታወቂያ» ቢሉት ላይኖረው ይችላል። ጐረምሳው ታክሲ አጣቢ ቢሆንስ?! ደሞ እኮ አንዳንዴ የምታዩት ሁኔታ ሊያስደንቃችሁም አይገባም። ልጅዋን እንዳዘለች የምትጠጣ

ሴት ከጐልማሣ ሰው ጋር ቁጭ ብላ ብትታይ ስለጋብቻ ለመወያየት እንዳልመጡ መገመት አለባችሁ። ሊጠጡ ነው። ይጠጣሉ። ልጁ ፊቱ እንደተሸፈነ፣ በእናቱ ጀርባ ላይ ሆኖ የሚሰማውን ጫጫታና ሁካታ ለማወቅ ባለው ጉጉት ፊቱ የተሸፈነበትን ነጠላ ካልገለጥኩ እያለ ሲታገል እናቱ መልሳ ስትሸፈነው፣ ያ ሲያቅተው ደሞ በለጋ እግሮቹ የእናቱን ሽንጦች እንዴት እንደሚረግጥ ካስተዋላችሁ ሳትወዱ ሳቃችሁ ሊመጣ ይችላል። የሆነው ይሁን የጠጅ ቤት ሳቅ ነውና ከሞቅታውም ከውርውርታውም ጋር ትችሉታላችሁ።

ከሁሉም በላይ የምትገረሙት የጠጪዎችን የተለያየ ጠባይ ስታስተውሉ ነው። አንዳንዱ ጠጪ ኪሱ የደበቀውን የሙስሊም ክፊያ በሞቅታ ገና ከአዳራሹ ሳይወጣ እዛው ያጠልቀዋል። አንዳንዱ ደሞ ልጆች ለመሸጥ የሚያዞሩትን የመልአክ ስዕል ሲያይ የረሳውን የዲያቆን ቅላፄ ያንቆረቁረዋል። የጫት ቤት መንዙማ እየዘመረ ልበጥብጥ የሚልም ይኖራል። በዛ ጫጫታና ሁካታ መሀል ያሳለፈውን ደግ ዘመኑን ጠጅ እያባበለው የሚያስታውስም አይጠፋም። ለምሳሌ ዱሮ ለአዝማሪ እንደሚሰጠው ዓይነት ግጥም፣

«ባቡር ሄዶ፣ ሄዶ ይገባል አዋሽ፣
የማንደፍሮ ታላቅ የአስካለ ታናሽ፣
የኔ አካል ወላንሣ እንደምን አለሽ።»

እያለ እንባ ቀረሽ የፍቅር ትዝታውን የሚያንጐራጉር። ይሁን እንጂ የጠጅ ቤት ትዕይንት ሲባል በሁካታ ብቻ የሚጠቃለል

አይደለም። የጥሩ ጨዋታ፣ የጥምቢራ አስኪዞር መስከሪያ፣ የእንካስላንቲያና የለከፋ ሌላም የተለያየ ቡድን አለ። ለጥሩ ጨዋታቸው ቦታ በክብር የሚያዝላቸው ሰዎች የመኖራቸውን ያህል ከበርሜሉ አጠገብ ንቅንቅ የማይሉና ከማንም ሳይቀላቀሉ በሰዓቷ ገብተው በሰዓቷ የሚወጡ፣ ካልታመሙ በስተቀር አንዲት ጀንበር የማያስተጓጉሉም ይኖራሉ። በዓውደ ዓመት ዕለትማ ትዕይንቱ በሀገር ልብስና በጭፈራ ይደምቃል። ለሎተሪ የሚያዞሩት ሙክት መተላለፊያ እስኪያጣ ድረስ ትርምስ ይሆናል። ለደብረ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ማሰሪያ መዋጮ የሚጠይቁ ቆብ ያጠለቁ ሰዎች የየወሩን በዓል አስታክከውም ይመጣሉ። ደንበኞች በብዛት ያውቋቸዋል።

የጠጅ ቤት ደንበኞች ከባለስልጣን እስከሊስትሮ በኑሮና በሙያ ደረጃ የተለያዩ ናቸው። አለቃና ምንዝር ባንድ አግዳሚ ላይ ባይቀመጡም አዳራሹን እኩል ይጠቀሙበታል። ጠበቆች፣ ዳኞች፣ ነጋዴዎች፣ ሹፌሮች፣ አናጢዎች... የዕለቱን ጽዋ ተቃምሰው ሰዓታቸው ሲደርስ ወደ ውይይት ታክሲ ተጣድፈው ይሄዳሉ። ትላልቅ ጠጅ ቤቶች የማያስተናግዱት የለም። ጠጁ አንድ ብር ከሀምሳ በብርሌ መሸጡን አትዩ። ብር ኪሳቸውን የወጠራቸው ሀብታሞች ብርሌያቸውን እያንደቀደቁ በመቶ ሺ ብር ደረጃ የዕለት ገበያቸውን ሲያወጉ ያጋጥማችኋል። ጨዋታ ልሳተፍ ብትሉም ከነሱ ጋር አትግባቡም። ደግሞ አንዳንዱ ዘመናዊ ወጣት መኪናውን እበራቱ አቁሞ አንድ ሦስቷን ለመቅመስ ይመጣና ወቅቷ

ስትደርስ ውልቅ ብሎ ይወጣል። ጠጅ መጀመሪያ ካልጠጣ ውስኪና ጮርደን ጂን ከጉሮሮው እሺ ብሎ አይወርድለትም።

በነዚህ አንጻር ከአንዱ ረድፍ አካባቢ ጠጥቶ «የለኝም!» የሚልና ዲስኮ ሰዓቱንም ቢሆን የሚያስይዝ ይኖራል። ዕድሉ ካጋጠማችሁ ብዙ ብዙ ታያላችሁ። ነገሩ የልማድ ጉዳይ ነው። በብዙ ዓመት ደንበኝነት ብርሌ እንደቤተክርስቲያን መሣለምን ስራዬ ብሎ የያዘ፣ የራሱን ትልቅ ጠጅ ቤት አሟሙቆ በሰዓቷ ወዳስለመደው ሌላ ጠጅ ቤት ሄዶ የሚያመሽም አለ። ያልጠበቃችሁት ሰውም ሊያጋጥም ይችላል። ለምሳሌ ጡረታ የወጡ ጀኔራል አጠገብ አንድ ቀን ብትጠጡ ያ ቀን የማትረሱት ቀን ይሆናል።

ለማናቸውም፣ ጠጅ ቤት ስትገቡ በፖለቲካውም፣ በማህበራዊ ጉዳዮችም፣ በኪስ ጨዋታውም፣ በፍቅርም፣ በሃይማኖትም... ጭውውት ከሚወዱ ሰዎች ጋር ነው የምታመሹት። ታዲያ አስተዋዮችና በሳሎች እንዳሉ ሁሉ ነገር አክራሪዎች አሉና ጠንቀቅ ማለቱ አይከፋም። ሌቦች በዛ አካባቢ ስለሚታወቁም ደንበኛም ስለሚሆኑ እምብዛም አይተናኮ ሏችሁም።

ከአክራሪዎች መካከል ግን አንዳንዶቹ በግድ ክርክር የሚጭሩ፣ እናንተ በማይገባችሁ ነገር የሚናደዱና የሚያኮርፉ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ነገሮችን በጣም የሚያጋንኑና

እናውቃለን ባዮች ናቸው። ቆሎ ጋብዞ በግድ ካላወጋን የሚልም ሞልቷል። «ጌታዬ ይኸውልዎት...» ብሎ ሶስት አራቱ የሚጐተጉታችሁ ሰው መልካም ጨዋታ ወይም አርክ. እይታ ይከለክላችኋል። «መቼስ ጨዋታን ጨዋታ ያመጣዋል ... ዕውቀትና ፍጥረት አንድ ቀን ነው... ጌታዬ ያዳምጡኝ... ምነው ጃል» ብሎ የሚወተውታችሁ ግን ጨዋታው የተናቀበት የሚመሰለው ነውና ወደሌላ አግዳሚ መሄዱ ነው የሚያዋጣችሁ (ካልጠፋ አግዳሚ!)። ሌላ ደሞ አለ። «ጊዜው ተለውጧል ጌታዬ። ያ የጥንቱ የጓደኛ ታማኝነት ፍቅር... ይሁን እስቲ... ጤና ካለ... ዋናው እሱ ነው...» ብሎ ዓይኖቹን ወደጣራ ሰቅሎ ጢሙን የሚፈትግ ፊተብሩህ ሰው። እሱን በርጋታ ቀርባችሁ ብታጫውቱት ሳርያን ኮቱ ካፈነችው የልቡ ማህደር ቆንጆ ወግ ወይም ታሪክ ልታገኙና ልትረኩ ትችላላችሁ።

የጠጁ ቆሌ ይርሳንና ጠጅ ቀጂውን በዚያ ጫጫታ መሀል ረሳነው። ጠጅ ቀጅዎች ከሩቅ ተመልክቶ የማስተናገድ ችሎታ ያላቸውና ፍጥነት ከእርጋታ የተላበሱ ኮራ፣ ኮስተር ያሉ የአዳራሹ አንቀሳቃሾች ናቸው። ተራ ማስጠበቅ የሚባል ነገር እነሱ ጋ የለም። ከአራት ያላነሱ ብርሌዎችን ይዘው መቶ ሰው ሲያስተናግዱ ይውላሉ። ከቀልደኛው ጋር ቀልድ ዓዋቂ፣ ከጠበኛው ጠበኛ መሆን ይችሉበታል። ሌላ ቦታ ‹ያዙኝ ልቀቁኝ› የሚሉ ወፈፌዎችና ሰካራሞች ውሻ ጌታዋን እንደምታከብር ዓይነት እነሱ ፊት ጨዋ ይሆናሉ።

በቡና ቤቶችና ሆቴል ቤቶች ፊላጭ ቆራጩ ባለቤቱ ነው::እዚህ ግን ጠጅ ቀጂው ትልቅ ስልጣን አለው:: ባለቤቶች በነሱ ላይ ነው አመኔታ የሚጥሉት:: የደንበኛ ግብግ ስልችት የሚላቸው ተወዳጅ ሰዎች ናቸው:: አልፎ አልፎ ደንበኞች ሲጣሉ አስታራቂ፣ ሲወራረዱ መስካሪና የአደራ ገንዘብ አስቀማጭ ይሆናሉ:: የአንድ ዘፈን ሁለት ስንኝ መያዝ የሚያቅታቸው ቀጂዎች የዛን ሁሉ ሰው ሂሳብ ሲያስታውሱ ለጉድ ነው:: አንዷ ብርሌ ዝንፍ አትልባቸውም:: ሲቀዱ ከሰማያዊው ትልቅ ማንቆርቆሪያ ከሩቅ የሚወረወረው ጠጅ የብርሌዋን አፍ ፈልጐ እንዴት እንደሚገባላቸው ሳስበው የልምድ ጉዳይ በጣሙን ያስደንቀኛል::

አሥቂኝ ትዕይንቶችና አሥቂኝ ተዋንያን

«ሳቅ የደስታ ምንጭ ነው» የሚል የቆየ አነጋገር አለ። በኑሮ ውጣ ውረድ አንዳች እፎይታ ለማግኘት፣ በተደራራቢ ድካም የተወጠረን ውሎ ዘና ባለ መንፈስ ለማሳለፍና ወቅታዊ ችግሮችን አዘናግቶ ለማለፍ በጐ አስተዋፅኦ አለው። ሳቅ ወጉን ጠብቀው በተገቢው መልክና መጠን ከተጠቀሙበት እንደጥሩ የሙዚቃ ቅኝት የሕሊና ትፍሥሕት፣ ቁም ነገርና ትምህርትም ይለግሳል። ሌላው ቀርቶ ከመንፈስ ጭንቀት ፋታ ለማግኘትና በጤናማ ሕይወት ራስን ከጊዜ ወደጊዜ ለማደስ ይረዳል።

እንደምናውቀው፣ አሥቂኝ ነገሮች በጽሑፍ፣ በድምፅ፣በካርቱን፣ በስዕልና በመድረክ ትዕይንት፣ አንዳንዴም በእንቅስቃሴ ብቻ ይቀርባሉ። የሚነበበው በየጽሑፉ ይነበባል፣ ተነቦም ግንዛቤ ላይ ይደረስበታል። በደንብ ለመረዳት ግን ከጥሩ አነባበብ አንስቶ ብሩህ በሆነ ምናብ (imagination) ነገሮችን ቀርጾ የማስተዋል ችሎታም ልምድም ይጠይቃል። በድምፅ ብቻ የሚደመጠውም ከጽሑፍ እምብዛም አይለይም። እንደሬዲዮ ድራማ ያለውን ማለታችን ነው። ትዕይንቶቹ የሚካሄዱባቸውን ቦታዎችና ለዎቹን ከነአኳኋናቸው መከታተል ያሻል። እዚህ ላይ ከጽሑፍ የተሻለ ዕድል ሊኖር የሚችለው በድምፅ መሪነት በሚመነጨው የግንዛቤ ጥቆማ ነው። በሶስተኛ ደረጃ የጠቀስነውን የካርቱን ስዕል ሰፋ አድርገን

ስናይ ደግሞ ራሱን የቻለ ድንቅ ጥበብ ሆኖ እናገኘዋለን። በካርቱን የሚታዩ አስቂኝ ሁኔታዎች ተደንቀው አይጠገቡም። ወፍራምና ቀጭን ሰዎች በገሀድ ከሚታዩ ይልቅ ካርቱን ላይ ያምራሉ። ምክንያቱም የወፍራሙ ቦርጭና ጉንጭ፣ ማጅራቱም፣ ጣቶቹም ተጋንነው ይቀርባሉ። የዐይኖቹ ትላልቅነት፣ የሽፋሉ መድመቅ፣ የጥርሱ መተለቅ ሁሉ ከወፍራሞች አገር የመጣ የሚያስመስል አሥፈሪ ድባብ ያጐናጽፈዋል።

ከሲታውም ሰው ቅጥንጥን ብሎ ጉንጮቹ ጐርጉደው ወስፌ መሳይ ዐይኖቹን መሬት ላይ ተክሎ በኮሳሳነት ሲታይ ንፅፅሩ ይጐላል ። ለምሳሌ ወፍራሙ ሰውዬ ሰፊውን በር ዘግቶበት ጆሮው ላይ በለጠፈው ስልክ «የአርባ ሺ ብር ጆንያ ጭኜላችኋለሁ፣ አራግፉ!» እያለ ለሌላ ሰው ሲደውል፣ ኮሳሳው ሰውዬ ኋላው እንደቆመ «ኧረ እኛ ሻይ ልንጠጣ ነው! አሳልፉን» ብሎ ሲማፀን ሁለቱን በካርቱን ብናይ የሚያስቅ ትዕይንት ይሆናል።

ካርቱን ሰዓሊዎች እንደወግ ጸሐፊዎች የህብረተሰቡን የቅርብ ችግር የሚያዩና ለየት ባለ ተሳልቆ በአስቂኝ መልክ አዝናንተው የሚያስ ተምሩ ናቸው። አስመሳይ ለማኝ፣ የውሸት አፈቀርኩ ባይ ኮረዳ፣ የቢሮ ወሬኛ፣ ቢሮክራት አለቃ፣ ሰነፍ አስተማሪ፣ አጭበርባሪ ቄስ፣ እና የመሳሰሉት... ዓይነተኛ ዒላማዎች ናቸው። ካርቱኒስቱ ለሥራው አመቺ የሚሆኑለትን አንጠርጥሮ ያውቃቸዋል። በስልክ ሐሜት የሚያበዙ የቢሮ

ፀሐፊዎች፣ መሀል መንገድ አቁሞ ወሬ የሚያወራ ባለታክሲ፣ የዕቃ ካታሎግ ለጠጪዎች እያሳየ «ሁለት ብር» የሚል መጽሐፍ አሟሪ፣ «እንካ!» ብለው ቆሎ ሲሰጡት «ጠግብያለሁ» እሚል ለማኝ... ለስዕሉ ይመቹታል።

ታዲያ አቀራረቡ ልዩ መሆኑ ለኔ ይደንቀኛል። ለምሳሌ ሙሽሮች ቢስል ሴቷን ሆነ ብሎ ነፋስ ይዟት የሚነጉድ ዓይነት ወገበ ቀጭን መለሎ ያስመስልና አፏን ጡጦ የሚጠባ ሕፃን ያክል ያሳንሰዋል። ወንዱንም ሙሽራ ሽክ አርጎ ያቀርበውና ኮፈስ ኮስተር ያለ ግርማ ይሰጠዋል። የነገሩ ቅኔ የሚገኘው ግን አባባላቸው ላይ ነው። ለምሳሌ፣ ሴቷን በሐሳቧ «እንደኔ ሰርግ የደመቀለት የለም» እንድትል ሊያደርጋት ይችላል። ወንዱንም በሐሳቡ «የዕዳው ብዛት የራሱ ጉዳይ!» ሊያሰኘው ይችላል። እግረ መንገዱን እያዝናና ቁምነገር አቀረበ ማለት ነው።

በርግጥም እኔ ሳስበው ለካርቱን አስቂኝ ትዕይንት የሚመቹና ተመልካቾችን ለአድናቆት የሚጋብዙ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሣሌ፣ ፀጉር አስተካካይ በመሰልቸት አኳኋን «ፀጉርህ በጣም አድጓል» ሲል፣ እንደማርያም ፅዋ አንገቱን ጨርቅ ውስጥ የደበቀ፣ ፊተ ትንሽ ተስተካካይ «አመሰግናለሁ፤ የዘራችን ነው!» ብሎ ቢመልስ ዓይን የሚስብ ይሆናል። በተለይ አታላይ ሰው ለካርቱኒስቱ አመቺ አቀራረብ ይፈጥርለታል። አንዳች ዕቃ በጨርቅ ጠቅሎ «ሎተሪ ግዙ!»

የሚል አጭበርባሪ የተሰበሰቡት ሰዎች «ዕቃው የታል? ዕቃው ምንድነው?» እያሉ ሲወተውቱት፣ «ገንዘቡ ይሰብሰብ ብዬ ነው! የት ይሄድባችኋል?» ካለ ሳቅ የግድ ይኖራል። የሞተች ዶሮ ይዞ «ደክሟት፣ተኝታለች» የሚል ወስላታ ደግሞ የበለጠ ሣቅ ይፈጥራል።

የካርቱን አንዱ ዋነኛ ገፅታው ባጭር ጊዜና በጠባብ ቦታ አስቂኝ ሁኔታን ከትምህርታዊ ግንዛቤ ጋር አሟልቶ ለማቅረብ የሚያስችል ጥበብ መሆኑ ነው። ባልና ሚስት፣ የቤት ሰራተኛና እንግዳ ባንድ ክፍል ቁጭ አድርጐ ሠፊ የቤተሰብ ፅንሰ-ሐሳብ ሊያመነጭ ይችላል። መምህርና ተማሪን ሁለት ሶስት ቃላት አናግሮ የዕውቀቱን ዓለም፣ ዲስፕሊኑን፣ በአጠቃላይም የትውልዱን ባህልና እምነት እንዲሁም አስተሳሰብ፣ አሟጦ ባይዘልቀውም፣ ዳሰስ አድርጐ በትግርምት እንድንረካ ያደርገናል።

በውነቱ ለስዕል ጥንቱንም አልታደልኩም እንጂ፣ በተለይ ካርቱን ብችል ኖሮ፣ ፀጉሩ የተንጨባረረ ሰካራም ሰውዬ እግሩን ትልቅ ሊስትሮ ላይ እንዳስቀመጠ፣ እሱ እንቅልፍ እያንገላጀው ትንሹ ጠራጊ ልጅ ቀዩን ጫማ ቢጫ እያወጣ ሲቀባ ብንን ብሎ «ምን ማለትህ ነው... ምን ዓይነት ቀለም ነው እሱ?» ብሎ ሲጠይቀው፣ ሊስትሮው «ቀይ ቀለም ነው፣ የፀሐይ ጨረር ስላረፈበት ቢጫ ይመስላል» እያለ ሲመልስ ካርቱን ብስል ደስ ይለኝ ነበር። እንዲያውም ከዚህ አልፎ ተርፎ የመንደር ውሾችና ድመቶች በአዲስ አበባ

መንገድ ላይ የቆሻሻ ክምር እያግበሰበሱ «ተመስገን፣ ዕድሜ ለማዘጋጃ ቤት ዘንድሮ እንደልብ ጠግበናል» ሲሉ የሚያሳይ ቆንጆ ካርቱን ጋዜጣ ላይ አስል ነበር።

የካርቱን አሳሳል ጥበብ፣ በኔ የሙያው ጭላንጭል ብርሃን እንኳን በሌለው ግለሰብ እንደዘበት ተነሳ እንጂ በኢኮኖሚውና በፖለ ቲካው መስክ እያዝናና ትልቅ የቁምነገር ሚና ይጫወታል። በውጭ አገር መጽሔቶች (ኒውስዊክንና ታይምስን በመሳሰሉት) ላይ የሚታዩ መሪዎች በካርቱን አሳሳል እንዴት እንደሚያምሩ ታውቃላችሁ። «ዘ ኢኮኖሚስት» እሚባለው መጽሔት ከቁምነገሩ አስቀድሞ ለቁም ነገሩ የመጋበዝና የመሳብ ኃይል የሚያመነጨው በኪነጥበቡ ውበት ነው። እና ካርቱን ይዜን ለማሳየት ትላልቅ የሚባሉትና ዓለም ያወቃቸውን መሪዎች ዋነኛ የመልክ ቅርጻቸውን እየለየ ሲያቀርባቸው ዘወትራዊ የሆነ ዕውቅና ይሰጣቸዋል። እኔ በግሌ ከማስታውሳቸው እንኳ ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ ብሬዥኔቭ እና የመሳሰሉት ትዝ ይሉኛል። ካርቱኒስት የታወቀ ሰው ሲነድፍ ጉልህ የሆነ የሰውነት አካል ፊልጉ እሱን ያጋንናል። ባልሳሳት ብሬዥኔቭ በሥዕሉ የሚታየው የሽፋላቸው ብዛቱ ነበር። ጂሚ ካርተር ጥርሳቸው ይተኮርበታል። ኒክሰን፣ ሄዶ ሄዶ በርዝማኔ ተቀልብሶ በሚያልቀው አፍንጫቸው፣ፊርናንድ ማርቆስ በጠባቡ ሰንጠቅ ያለች በምትመስለው ትናንሽ ዐይናቸው፣ አዶልፍ ሂትለር በላይኛው የከንፈር ጺሙ መድመቅ፣ ሙሶሊኒ በፈርጣማ

አጭርነት በካርቱን ሰዓሊያን በደንብ ታውቀው እንዲታወቁ ተደርገዋል። ታዲያ አሳሳሉ የሚያስቅ ይሁን እንጂ ቁምነገሩም የበለጠ ጉልህ ሆኖ አብሮ ይታያል።

ካርቱኖች ማህበራዊ ችግሮችን ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችንም እንደሚያስተናግዱ እናውቃለን። ከቅርብ ትዝታችን አንዱ የሆነው የፋርስ ባሕረ-ሰላጤ ውዝግብ በመገናኛ ብዙሃን ሲገለጽ ከመቆየቱ በተጨማሪ፣ በሚያስገርሙ የካርቱን ስዕሎችም በየመጽሔቱ ሲታይ ነበር። ኒውስዊክ በአንድ ወቅት ያወጣው ይህንን ይመስላል። የኢራቅ ፕሬዝዳንት ሳዳም ሁሴን የኩዌትን ሼህ ጥለው በፈርጣማ እግር ረግጠዋቸዋል። ጆርጅ ቡሽ ግዙፍ ቁመና ተጐናጽፈው ወፍራም ዱላ ሳዳም ላይ ሰንዝረዋል። ከኋላቸው የዐረብ መሪዎች ትናንሽ ተደርገው እንደተሰለፉ ተስለዋል። ጠቅላላው ካርቱን ሲታይ የመፋጠጣቸው ሁኔታ ያስገርማል። የኩዌቱ መሪ ኮሳሳነት፣ የሳዳም ጡንቻና በዛቻ የሚጉረጠረጡ ትላልቅ ዐይኖች፣ የጆርጅ ቡሽ ቁጣ... ጉልህ ሆኖ ይታያል። እያሳቀ ግን የወቅቱን ፍጥጫ ጥሩ አድርጐ ያስገነዝባል።

የካርቱን አሳሳል ከሕፃናት አልፎ ተርፎ ለዐዋቂ መዝናኛነት የሚውልባቸው ለየት ያሉ ሁኔታዎችም አሉ። ለምሳሌ ትናንሽ ልጆች ራሳቸው በካርቱን አሥቂኝ ሆነው ይቀርባሉ። አሁን ለምሳሌ በመኪኖች ትርምስምስ መሀል ብስኪሌት እያወላገደ የሚነዳውን ጋጠ-ወጥ ልጅ አስመልክቶ

ምክር ለመስጠት ከተፈለገ፣ ካርቱኒስቱ እሱው አጠገብ ደብተር ይዞ የሚገረም ሌላ ትምህርት ወዳድ የሚመስል ልጅ ሊስል ይችላል። «በደንብ ሳይለማመድ ለምን ልንዳ ይላል? ከየትኛው ኦሎምፒክ ለመድረስ ነው?» የሚል ዓይነት። በተለይ ሌባው በከፋበት ባሁኑ ሰዓት ለአውቶቡስ እንደተሰለፈ ኪሱ ውስጥ እጁን ለሚያስገባ ሌባ «እስቲ ከኛ ምን ይገኛል?» የሚል ትንሽ ልጅ ሲታዘብ የተሳለ ካርቱን ባይ ደስ ይለኛል።

ዐይኖቻቸው ከስፒል ጭንቅላት ትንሽ ከፍ የሚሉ አሻንጉሊት ሕፃናት ፀጉሩ ከተንጨባረረና ጢሙ ከተንሸረገገ ሳቂታ ጠንቋይ ጋር አንጋጠው ሲያወሩ የሚያሳይ ካርቱን ዐዋቂንም ፈገግ ያስደርጋል። ትልቁን ሰውዬ አላስገባም ብላ የምትጮህ ድንክ ውሻ፣በመዶሻ የምትማታ ጦጣ፣ ዶሮ የታሰረበትን ገመድ በቢላ እምትቆርጥ አይጥና የመሳሰሉት የእንስሳትና የአራዊት ካርቱኖች ንግግር ተጽፎላቸው ሲሳሉ ለሕፃናት መልካም ጊዜ ማሳለፊያ ይሆናሉ። በበኩሌ፣ ዘላ፣ ዘላ ወይኑን ማውረድ ያቃታት ቀበሮ «ወይን እኮ አይጣፍጥም!» ስትል የሚያሳይ ካርቱን፣ ወይም ዝሆን ጀርባ ላይ ተቀምጣ «በዚህ ሁሉ ጉልበትህ እስቲ ስታወ ርደኝ ልይህ?!» የምትል ጉንዳን ተስላ ብመለከት ምን ያህል ሊያስቀኝ እንደሚችል እገምታለሁ።

አስቂኝ ትዕይንቶች በረጅምም ሆነ በአጭር የጊዜ ክልል አመቺ ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉት በመድረክ ላይ ነው። በዚህ አቅጣጫ የሚቀናበር ትዕይንት የብዙ ነገሮች አስተዋፅዖ

አለበት። አለባበስ፣ አነጋገር፣ አካሄድ፣ የእጅና እግር እንቅስቃሴ፣ የዐይን አኳኋን፤ በአሳሳቅ፣ በቁጣና በመሳሰሉው ፊትን መለዋወጥ መቻል ሁሉ አስፈላጊ ይመስለኛል። ጥሩ ተዋናይ ማለት ሌላውን መምሰል የሚችልም ነውና በዚህም ረገድ ተሰጥዖና ልምዱ ሊኖር ይገባል።

ታዋቂው እንግሊዛዊ የፊልም ተዋናይ ሪቻርድ በርተን የቲያትር ጥበብ ሲማር ጀምሮ ብዙ ፊልሞች እስከሰራበት ዘመን ድረስ በዚህ የማስመሰል ችሎታው ተወዳዳሪ አልነበረውም። እንዳውም አንድ ጊዜ የመምህሩን አኳኋን ከነእንቅስቃሴው ከነአነጋገሩ እሱን አስመስሎና እሱን ሆኖ ለክፍል ጓደኞቹ ሲያሳይ፣ መምህሩ በመስኮት ተደብቆ ተመልክቶት ኖሮ «ያንተ ዓይነቱን ድንቅ ችሎታና የተሟላ ተሰጥዖ ያለውን ተማሪ አስተምራለሁ ለማለት አልደፍርም» ብሎ ትምህርት ቤቱን እንደለቀቀና ወደሌላ ድራማ ማሰልጠኛ እንደተዛወረ ይነገራል።

ሌላውን መምሰል መቻል ትልቅ ተሰጥዖ መሆኑ የታወቀ ነው። ስለተዋንያን የምንገረምበትም በዚህ ችሎታ ምን ያህል ሌላውን መስለው ሊመስጡን እንደሚችሉ ስለምናስብ ነው። እናንተስ ስታስተውሉት የቅርብ ጓደኞችን የሆነ ሰው ለማኝ ተመስሎ በአኳኋኑና በአነጋገሩ መስጠን፣ ማንነቱን ለጊዜው እስክንረሳ ድረስ እንድናዝን ሲያደርገን የጥበቡ ሉዓላዊነት አያስደንቅም ትላላችሁ?! በተለይም በአስቂኝ ተውኔቶች ማስመሰል ትልቅ ሚና ይኖረዋል። እዚህ ላይ ድምፁን

መለወጥ የሚችል ተዋናይ ድንቅ እንደሚሆን ይታሰበኛል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሲፈልግ ሽማግሌ፣ አሮጊት፣ ሕፃን ሲያስኝው አስተማሪ፣ ጠበቃ፣ ስፖርተኛ፣... መሆን ይችላል።

የድምፅ ነገር ከተነሳ አንድ ጊዜ «ሪደርስ ዳይጀስት» በተባለው መጽሔት ያነበብኩትን ላጫውታችሁ።ሰውየው የአንድ መንደር ግሮሰሪ ባለቤት ነው። ብቻውን ብዙ ሰዎች ሲያስተናግድ ይውላል። እና አንድ ቀን፣ ያለ ምንም ረዳት አንገቱን ቀብሮ በሚዋከብበት ሰዓት፣ «እባክህ አንድ ኪሎ ስኳር ስጠኝ» የሚል የወፍራም ሰው ድምፅ ዓይነት አነጋገር ይሰማል። ቀጥሎ «የተፈጨ ቡና ሩብ ኪሎ» የሚል ቀጠን ያለ ድምፅ ወደ ጆሮው ይመጣል። ነገሩ በዚህ ብቻ አላበቃም። «ሶስት ፓኬት ሻይ ቅጠል በዚያው ያቀብሉኝ» የሚል የሕፃን ዓይነት ድምፅ ሰማ። በተከታታይ ያዳመጠው ተለዋዋጭ አነጋገር ከብቸኝነት ድካሙ ጋር ተዳምሮ አደናገረውና፣ «አንድ ባንድ አትጠየቁኝም? እባካችሁ ተራችሁን ጠብቁ» አለና የመጨረሻ የብስጭት ትንፋሹን በረጅሙ ተነፈሰ። የሚገርመው ግን ያንን ሁሉ የተለያየ ድምፅ እያወጣ ብዙ ሰዎች ሲመስለው የቆየው አንድ የተዋናይነት መልካም አዋይ የተዛመደው፣ ለወደፊት ዕውቅናው ራሱን ሳያውቅ የሚያዘጋጅ የማስመሰል ችሎታ ያለው ደንበኛው ነበር።

እና፣ ተውኔትን — በተለይም አስቂኝ ተውኔትን — ሳስብ ከሚደንቁኝ ነገሮች አንዱ ወንድ ሆኖ በወንድ ድምፅ ሴት እንደተናገረች ያህል ማስመሰል የሚችል የመድረክ ሰው ነው።

ይሄን ተሰጥዖ በተመለከተ ዛሬ እንደዘበት ላንሳውና «ፍቅር እስከመቃብርን» ያነበበው ወጋየሁ ንጋቱ ትዝ ይለኛል። ወይዘሮ ጥሩ ዓይነትን፣ ካብትሽ ይመርን፣ እነ ደብራቱን፣ ስንዮች ስንዮችን ድምፁን እየለዋወጠ ሲናገረው ለጉድ ነበር። ስለሱ እማደንቀው ነገር ቢኖር ወጋየሁ ንጋቱ ሲተርከው ካብትሽ ይመርን እንጂ እሱን ፍጹም አለመምሰሉና ዝም ብለን ካብትሽ ይመርን በዐይነ ሕሊናችን እንድናያት ማድረጉን ነው። ቀደም አርገን ለረጅም ጊዜ የምናውቀውን የልቦለድ መጽሐፍ እንደገና በደንብ እንድንወደው ያደረገን መሆኑ ሲታሰበኝ፣ ድምፅ በተዋናይ ሕይወት ከበድ ያለ ድርሻ እንዳለው እገነዘ ባለሁ።

በኔ ግምት የመድረክ ተውኔት ከሁሉም ቀደም ብለን ካነሳናቸው በላይ የበለጠ የመታየትና የመደመጥ አመቺነቱ የላቀ መሆኑ አይካድም። ታዲያ አሁንም ቢሆን መሰረታዊው የተዋንያን ተሰጥኦና ችሎታ ማስመሰል ነው። የማስመሰል ችሎታ ሲባል ምን ማለት ነው? እንደ ሚገባኝ ራስን መለወጥ፣ ራስን ሲለውጡ ራስን መርሳት እና በድምሩ ኪነታዊ ድባብን ተላብሶ ተደራሲያንን (audience) ማርካት ነው።

ማስመሰል የተውኔት (በተለይም የሚያስቁ ዓይነቶች ተውኔቶች) ቋሚ ባሕርይ መሆኑን እንግሊዛዊው ደራሲ ጂ. ኬ ቼስተርተን እየደ ጋገመ ይናገረው ነበር። ወግ በመጻፍ በይበልጥ የታወቀው ቼስተርተን «ማስመሰል ማለት የተዋናዩና

የአርቲስቱ ጥበብ እንጂ የሌላ የማንም አይደለም» ብሎ ይጀምርና «የማስመሰል ተሰጥኦ ያለው ተዋናይ በወርቅ የተለበጠ የንጉስ ዘውድ ሳያጠልቅ፣ ቆርቆሮ መሣይ ጌጣጌጦችን በዛም በዚህም ሰካክቶ እውነተኛውን የንጉስ ሚና ሊጫወተው ይችላል። ተውኔት መምሰል መቻል ነው» በማለት የጥበቡን ለዓላዊነት አገልቶ ይናገረዋል። ቼስተርተን በአንድ ወቅት እንግሊዛውያን ቲያትር አሰሪዎች የድራማን ጥበብ ካገር ልጆች ጋር በማቆራኘታቸው ቅሬታ ገብቶት ትችት አቅርቦበት ነበር። ለምሳሌ፣ «በቻይና መቼት (setting) ላይ የሚጻፍ ተውኔት በቻይናውያን መሰራት አለበት ለምን ይባላል? ከቻይናዊ ይልቅ ሌላ የሩቅ አገር ሰው፣ ኪነታዊ ተልእኮውን ከተገነዘበ፣ ይበልጥ ሊሰ ራውና እንደ ቻይናዊ ታይቶ ተደንቆ ተመልካቹን ሊያስደንቅ ይችላል...» ይላል።

የቼስተርተን አባባል፣ ተውኔት ሲባል የሌላውን ማንነትና የነገ ሮችን አካሄድ እንደሁኔታው ተገንዝቦ፣ ያንኑ ማንነት መሆን፣ ያንኑ የነገሮችን ይዘት በተግባር ማሳየት ነው የሚል አቋም ያንፀባርቃል። «ለምሳሌ፣ የሀገሩን ሰው ተውኔቱን ስራ ማለት ልክ አይደለም። የአን ቶኒንና የክሊዎፓትራን ድራማ ለመሥራት ግብፃውያን የሜዲትራንያን ባሕርን አቋርጠው እንግሊዝ አገር መምጣት የለባቸውም» ይላል።

የሱን አነጋገር እስቲ ከጀመርነው ነገር ጋር እናዛምደው። ተዋናዩ፣ ሌላውን ሲመስል ምን ዓይነት አስቂኝ ባሕሪውን ሊያስተላልፍ ይችላል? ይህንን በተመለከተ «አንድ

ሰው» ይላል ቼስተርተን፣ «የአንድ አሳማ ድምፅ አሰምቶኝ በዚያ ብቻ ሊማርከኝ አይችልም። ይልቁንስ እንደ አሳማ አኳኋኑን ለውጦ የአሳማን ኪነጥበባዊ ቅርጽና ሁኔታ ሰው ሆኖ፣ነገር ግን አርቲስታዊ መንፈስ ተጐናጽፎ የሚያሳየኝ ተዋናይ ግቡን መቷል ለማለት እችላለሁ።»

እውነትም አንድ ተዋናይ፣ በተለይም አስቂኝ ትዕይንቶችን የሚያቀርብ ቲያትረኛ፣ የሚጫወተውን ሚና በኪነጥበባዊ ምናቡ መቅረጽ የሚችል መሆን አለበት። ችሎታ ያለው የመድረክ ሰው ጤነኛ መሆኑን አስረስቶን እንደዕብድ፣ ሞኝ፣ ሰካራም እየተነጋገረና በአኳኋኑም ሁሉ እየመሠለ የሚያስገርመን በማስመሰል ተሰጥኦው ብቻ አይደለም። ብዕርና ወረቀት የሚያገናኝ ባይሆንም፣ ኪነታዊ ፍንጥቅታ በቅርበትም ይሁን በርቀት የተለገሠው ስለሚሆን ነው። በሌላ አነጋገር ጥሩ ተዋናይ በውስጡ የከያኒው ባሕርይ ያለው ነው ማለት ነው። ያ ባይሆንማ ኖሮ በተፈለገው ሚና፣ያለምንም ገደብ፣ እንደ ቦታውና ሁኔታው ራሱን መለዋወጥ አይችልም ነበር።

ለእኔ ብዙ ጊዜ እንደሚታሰበኝ አስቂኝ ተዋናይ በተፈጥሮው ለየት ያሉ ሳቅ ጠቋሚ ሁኔታዎች ይታዩበታል። የዓይን ቦዘዝ ማለት፣ የጆሮ አቀማመጥ፣ የአካሄድ ፍጥነት፤ ለምሳሌ እግር አጣጣል፣ እጅ አወነጫጨፍ፣ አነሳስና አቀማመጥ ሁሉ ሚናቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ጠደፍ ጠደፍ ማለት የማይቀናው አስቂኝ ተዋናይ የሚኖር አይመስለኝም። ምናልባትም ቻርሊ ቻፕሊንን ቀርጩ እንደሆነ

አላውቅም እንጂ እንዲህ ዓይነቱ የመድረክ ሰው በዓይነ እንቅስቃሴ (ነገሮችን ሲቃኝና ሲያማትር ማለቴ ነው)፣ በሽፋሉ ከፍ ዝቅ ማለትና በዓይኖቹ ቆብ መርገብገብ፣ በቁጣው በአሳሳቁ ሁሉ የሚያፍነከንክ ሁኔታ የሚታይበት—ይመስለኛል በተፈጥሮው። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም አንዳንዱ እጁ አጠር ያለ፣ በመጠኑ ጉች ያለች ቦርጭ ያለውና የሚጠቅሱ ከሚመስሉ ትናንሽ ዓይኖቹ ጋር መለስተኛ በራ ራስ የሚታይበት፣ ሲራመድ ለመጥ ብሎ እጁን መስቀለኛ የሚያወናጭፍ አጭር ሰው ሲያጋጥመኝ ጥሩ አስቂኝ ተዋናይ ሊወጣው ይችላል ብዬ አስባለሁ። ታዲያ ይሄንን ልገምት እንጂ ባለሙያው ተቃራኒውንም ሊሆን ይችላል።

የማስመሰል ተሰጥኦ ያለው ተዋናይ ሁሉን ነገር መሆን ይችላል። እናም በሚሆንባቸው ጊዜያት ሁሉ በቅድሚያ ራሱን ለሁኔታ ዎች መገበር አለበት። ማለትም ማንነቱን ለጊዜው መርሳትና በሚጫወታቸው ሚናዎች ውስጥ በተመስጦ ጠልቆ መግባት ግዴታው ነው። ዳኛ ከሆነ እንደዳኛ፣ ሀኪም ከሆነ እንደሀኪም፣ ወላጅ አባት ከሆነ እንደወላጅ አባት፣ ሚስት ከሆነ እንደሚስት፣ ማሰብ፣ እንቅስቃሴውንና ድምፁን ሁኔታውን ሁሉ በዚያው ክልል አድርጐ ወትሮአዊ ስሜቶቻቸውን ሳይቀር መላበስ ይኖርበታል። ለተውኔት ታማኝ መሆን ይሄንንና ሌላ ሌላ ሁኔታ የሚጠይቅ ከመሆኑ የተነሳ፣ እናም በደንብ ስለሚከውኑት፣ ብዙ ጥሩ ተዋንያን ደጋግመው መድረክ ላይ የተጫወቱት ባሕርይ

ከመድረክ ውጭም እንደሚቆራኛቸው ይናገራሉ። ያንን የወከሉትን ባሕርይና ያስመ ስለትን ሁኔታ አስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ተላምደውት ይቆያሉ ማለት ነው።

ቼስተርተን እንደጻፈው፣ ጥሩ ችሎታ ያለው የመድረክ ተዋናይ ሌላው ቀርቶ አልባሳቱና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችም ሳይመቻችለት እንኳ ያሰኘውን ባሕርይ ሆኖ ሊጫወት ይችላል። በቲቶ ሳይለብስ ለማኝ መሆን አያቅተውም። ጥምጥም ሳይጠመጥምና ጭራ ሳይዝ የቂስ ሚና መጫወት ይችላል።

በቀን፣ ተቀን ውሎው ሲያይ ሲሰማ፣ሆነ ብሎም ይሁን ሳያውቀው ያጠራቀማቸው የተለያዩ ገፀ ባሕርያት አኳኋኖች ከተደበቁበት ብቅ እንዲሉ የኪነት ተሰጥኦ ያስገድዳቸዋል። በተለይ ለአስቂኝ ተዋናይ የእጅ መወናጨፍ ራሱን የቻለ አጋዥ ችሎታ ነው። የአነጋገር ፍጥነትና፣ የአካሄድ መለዋወጥ፣ ፊትን እንደስሜቱ ሂደት መቀያየር ሳይጨምር። ከሁሉም በላይ የሚያስገርመኝ ተዋናዮች ዓይን ላይ የማየው ሁኔታ ነው። ለምሳሌ አንድ ተዋናይ በሴቷ ቦታ አሮጊት ሆኖ ሲጫወት፣ ዓይኑ ባይሞጨመጭም የመዳከም ስሜትን እዛው በዛው ይቀርጽና የአሮጊት ዓይነት ሙሉ ድባብ (atmosphere) ይፈጥራል። የተዋናዩ ዓይን የብር አሎሎም ቢያክል ዕድሜ የተጫነውን ትንሽ ዓይን ተመስሎ በቦዘዘ ሁኔታ መቅረጹ አይቀርም። መርማሪ ፖሊስ ሆኖ የሚሰራ ተዋናይም የሚያስፈራ ሽንጮበት (ሙስታሽ) እና

የሚጉረጠረጠ ትላልቅ ዓይኖች ባይኖሩትም፣ መስፈ የሚያካክሉ ዓይኖቹን የመርማሪ ፖሊስን ሁኔታ በሚገባ እንዲያንፀባርቁ ሊያደርጋቸው ይችላል።

በመሰረቱ፣ ለአስቂኝ ትዕይንቶች አመቺ የሚሆኑ ይዘቶች አሉ። ሆኖም አስቂኝ ድራማ መድረክ ላይ ሲከወን ሁሉም ትዕይንት ሁሉንም ተመልካች በተመስጦ እኩል ያረካል ማለት አይደለም። ምክንያቱም የተመልካቾች ፍላጐት ይለያያል። በርግጥ ሳቅ የመጫር ይዘቱ ከፍተኛ የሆነና በድንቅ ተዋናይ የተከወነ ትዕይንት ከሞላ ጐደል በሁሉም ተመልካች ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘቱ አያጠያይቅም። ሆኖም አንዳንዴ፣ ለአንዱ የሚያስቀው ሌላውን ላያስቀው ይችላል። ላንዱ ያረካው ደግሞ ሌላውን ላያረካ ይችላል። ሚስቱን የሚደበድብ ባል የሚያንከተክተው አለ።አፉ የሚንተባተብ ዘበኛ ወይም አሽከር የሚያፍነከንከው ሰው አለ። በሚስቱ መረን የለቀቀ ሁኔታ የሚቀና ባል ሲያይ ጥርሱን የማይከድንም ይኖራል።

ለማናቸውም ሳቅ የደስታ ምንጭ መሆኑ እየታወቀም መሣቅ ሁሌም የማይሆንላቸው አንዳንድ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይገባናል። መሳቅ የማይችል ሰው በዚህ ዓለም ላይ ሊፈጠር እንደማይችል እያወቅን ማለቴ ነው። የሚገርማችሁ ግን፣ ሌሎች ስቀው ካበቁ በኋላ ከእንቅልፉ የባነነ ይመስል በመጨረሻ የሚስቅ፣ ቀልድ ቁሎ እማይገባው ሰውም አለ።

ከዚህም አልፎ ተርፎ የተፈጠረን ቀልድ በቀልድነቱ ብቻ ዝቅ አድርጐ የሚመለከትና ልምዱም የሌለው ኮስታራ ከጥሬው እውነት በስተቀር ሌላው የማይጥመው ሰው በነዚህ መካከል ያጋጥማል። ጉዳዩ የሕሊና መለኪያ፣ የትላልቅና ትናንሽ ስብእና መመዘኛ ለመሆን አይበቃም እንጂ ሰዎቹ በላቁበት ጉዳይ ላይ እንደመኪና ማርሽ ወደኋላ ተመልሰው ሊስቁና በድምቀት ሊያጅቡት አለመቻላቸው ቅር ያሰኛል። የተውኔት አሳሳቅ አምልጦ የሄደ ባቡር ያህል ከሩቅ እያዩት ብቻ ትዶ ሊሄድ ይችላል ለማለት ነው።

ሳቅ መጫር የማይችሉ ሁኔታዎች ህብረተሰቡ ውስጥ ተፈጥረው ያሉና በየጊዜውም የሚፈጠሩ ናቸው። ለምሣሌ የዋሁ ብልጠትን፣ አንዱ ሌላውን ማሞኘቱ፣ አንዱ ከሌላው ይበልጥ አውቃለሁ ሲል መሳሳቱ፣ ገላጋይ መወንጀሉ፣ አስታርቃለሁ ባዩ ጉዳዩን አባብሶ ማጣላቱ፣ ሌባው መስረቁ፣ እና የመሳሰለው ሁሉ በገሀድም ያለ ነገር ነው። እና ከእንደዚህ ዓይነቶቹ ቅራኔዎች ውስጥ አስቂኝ ትዕይንቶች ሊመነጩ ይችላሉ።

ላንዱ የሚገባው ለሌላው ሳይገባው፣ እርስ በርስ የተፋጠጡ ገፀ ባሕርያትን መድረክ ላይ መፍጠርም ሌላው የአስቂኝ ትዕይንት ገጽታ ነው። አንዱ የራሱን አስተሳሰብና ስሜት ብቻ ይከተላል። ሌላውም የራሱን። ተመልካች ግን ሁለቱንም በየክልላቸው ብቻ ሳይሆን እርስ በርስ ሳያውቁ

በፈጠሩት አለመግባባትም እያስተዋላቸው የራሱንም አስተያየትና ምኞት እየጨመረ በተውኔት ዓለም ይፈነድቃል።

የተዋንያን ፅንሰ-ሐሳባቸው እኛው ነን። ጎብረተሰቡ ነው። ስለዚህም ማንም ሰው ተዋናይ ባይሆንም ለአስቂኝ ተውኔት የሚያመቹ ትዕይንቶች በራሱ ሊቀርጽ ይችላል። አንድ ወዳጄን በቅርቡ ጠይቄው የሚያስቅህ ተውኔት ምን ዓይነት ነው ስለው «መንገድ የሚሄዱ አዛውንት ለልጆቻቸው ብርቱካን ይዘው አንዲት የአስራ ሰባት ዓመት ልጅ አግኝተው ግሮሰሪ ገብተው ከሷ ጋር የሚያወሩትን ነገር በተውኔት ባይ እስቅ ነበር» ብሎኛል።

ለአስቂኝ የመድረክ ተውኔት እስከታሰበ ድረስ ማንም ግለሰብ የራሱ ምርጫም ፍላጐትም ይኖረዋል። አንድ የጥንት ጓደኛ አለኝ። «አስቂኝ ተዋናይ ምን ሲሰራ ብታይ ደስ ይልሃል?» ብዬ ስጠይቀው፣ «አውቶብስ ፌርማታ ላይ ላጫውትሽ እያላት የምትዘጋውን ቆንጆ ልጅ ሲለማመጥ፣ እሷ ፊቷን እያዞረችበት እሱ ያለ የሌለ ቃላቱን እያዘነበላት ሲለማመጣት ማየት ደስ ይለኛል» ብሎኛል።

«ታዲያ ከዚህ ካልከው ሁሉ አስቂኝ ነገር ይመነጫል ብለህ ታምናለህ እንዴ?!» ብዬም ጠይቄው ነበር። የመለሰልኝ መልስ «ግዴለ ሀም ተዋናይ ይጫወተው እንጂ ሁሉም ነገር ያምራል። ማን ያውቃል! እጮኛዋ ከተፍ ይል ይሆናል። ብቻ ለማናቸውም ለአርቲስቶች ብንተውላቸው» የሚል ነበር።

እስቲ አሁን ደሞ እኔ የሚመስለኝን አንድ የራሴን ሐሳብ ለአስቂኝ ተዋንያን ላቅርብላቸው። ተውኔቱን ልመነህ፣ አለባቸው፣ ደበበ እሸቱና እንግዳዘር አራት ሆነው ይጫወታሉ ብዬ ላስብ። ነገሩ እንዲህ ነው። ባልና ሚስት በሆነ ነገር ተጣልተው፣ ተሰዳድበው፣ እንዲያውም ባልዬው ካልተማታሁ እያለ እሷም «ኤጭ እባክህ፣ እስቲ ጥፍሬን ንካት» እያለችው በቤታቸው አነስተኛ ሳሎን ሲንሎራደዱ፣ ሲፎካከሩ ቆይተዋል። ሁኔታውን ስናጤነው ግን ባልና ሚስቱ እንደዚያ መሆን ፈጽሞ አልነበረባቸውም። ምክንያቱም ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ለእራት የጋበዟቸው ሁለት ጓደኞች ወይም ወዳጆች ሊመጡ ነው። ልክ ተጋባጉቹ ሲገቡ ባልና ሚስት ግዴታቸውን በይሉኝታ ለውጠው ሁለቱም ደህና እንደሆኑ ሁሉ በጥሩ መንፈስ እንግዶቻቸውን መቀበል ይጀምራሉ። ንዴታቸው ወደ ኩርፊያ ተለውጧል። ሆኖም ተጋባጉቹን ላለማስቀየም ይሞክራሉ። በተለይም መኮራረፋቸው ፍጹም እንዳይታወቅባቸው የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ነው።

በእንዲህ ዓይነቱ ትዕይንት ላይ በይሉኝታ ዋጥ ያደረጉት ኩርፊያቸው፣ያልተጣሉ ለመምሰል በውሸት የሚያሳዩት ፈገግታና የአንገት በላይ ጭውውት፣ ከሸካራ ጉሮሮአቸው ድንገት እየገነፈለ የሚታመቀው ንዴታቸው ሁሉ በጣም አስቂኝ ይሆናል። ሚስት ለማዘዝ ወደጓዳ ገባ ስትል፣ «እስቲ ልጥራት» ብሎ ባል ሄዶ ባዶ ክፍል ውስጥ «ቆይ እንግዶቹ ይሂዱ» ብሎ ሲዝት፣ ተጋባጉቹ የጠረጠሩትን ነገር

እየተነጋገሩ ሲጠብቁ፣ ከዛ ሁለቱም ተመልሰው በአንድ ድምፅ በውሽት ፈገግታ «ኧረ ብሉልን፣ ጠጡልን» ሲሉ፣ እንደውም ከዛ አልፈው ተርፈው የማስመሰል ቀልድ፣ ለምሳሌ ባልየው «ሚስቴ ባለሙያ ናት» ሲል፣ ወይም እሷ ሌሎቹን ስታጐርስ፣ «አንተስ ለምን ይቅርብህ?» ብላ በኃይል ስታጐርሰው...እንዲህ ዓይነቱን የማስመሰል ጭውውት ሲለዋወጡ፣ ባልታወቀ የነገር አሸሙር ሲጐሻሸሙ፣ እንግዶች ግራ ሲገባቸው... ሁሉም አለምንም ምክንያት እኩል ሲስቁ ወይም ያደሙ ይመስል ዝም ሲሉ ሁኔታው ኃይለኛ ሳቅ ይጭራል::

ኪዎስክ

ቃሉ ወደሀገራችን መቼ እንደገባ አላውቅም። «ኪዎስክ» ሲባል ስሰማ ሰላሳ ዓመት ያህል ሳያልፍ አይቀርም። የእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት እንደሚለው ትርጉሙ «ጋዜጣ፣ ሳንድዊችና ለስላሳ መጠጦች ወዘተ የሚሸጡበት አነስተኛ ቤት» ማለት ነው። የኪዎስክ ቅርጹ (መደበኛው ማለቴ ነው) በሰፋፊ ጣውላዎች በጠባቡ ክብ ሆኖ የሚሰራ ሲሆን፣ ጠቅለል አድርገው ሲያዩት እንደተገጣጣሚ ነገር ከአንድ ቦታ አንስተው ሌላ ቦታ የሚያስቀምጡት የሚመስል ኢኮኖሚያዊ ቤት ነው። በዚህ መልክ የተሰሩ በቁጥር ነው ያሉት። የጥንቶቹ ኪዎስኮች ዛሬ በብዛት ተሰራጭተው ከሚገኙት ሱቆች የሚለዩት በቀለማቸው ደማቅነትና ከመደርደሪያና ከውስጥ ይዞታቸው ጀምሮ ባላቸው ንጽሕና ጭምር ነው። ሰፊ ቦታ ያለመፍጀታቸው ግን ዱሮ ነበር እንጂ ባሁኑ ጊዜ አስደናቂ ሆኖ ሊታይ አይችልም። ምክንያቱም ዛሬ እነሱን የተኩ ሱቆች በቤትና ቤት መሐል የሚወርደውን የዝናብ መከላከያ አሸንዳ ሳይቀር ድንገት እየቀደዱ፣ ግድግዳም ሳያግዳቸው በአስገራሚው ጥበት በየመንገዱ እንደአሸን እየፈሉ ናቸው።

እንግዲህ ስለጥንታዊ ኪዎስክ ይሄን ያህል ካልን ከዚያው ዘመን ጀምሮ እየበዙ የመጡትን በተለምዶ አጠራር «ሱቅ»፣ «ዐረብ ቤት»፣ «መደብር» የምንላቸውን የንግድ

ቦታዎች በዚሁ አጠቃላይ ስም ኪምስክ እያልን ወደዛሬው ምንነታቸውና የሥራ እንቅስቃሴያቸው እናምራ።

የዛሬ ኪምስኮች በአሰራራቸው ቦታ እና ጊዜ የማይፈጁ ናቸው። ለምሳሌ መኖሪያ የነበረው ቤት በረንዳው በቆርቆሮ ታጥሮ ወይም በረንዳም ባይኖረው ወደአስፋልቱ ገባ የሚል ትንሽ ክፍል ተሰርቶ ድመት ብቻ ሊያዘልል የሚችል በር (ቀዳዳ ቢባል ያስኬዳል) ተበጅቶለት «ኪምስክ» ይሆናል። ወይም መኖሪያ ቤቱ ራሱ ቆጥ መሳይ የጣውላ ርብራብ በመስኮቱ አቅጣጫ ተሰርቶለት መስኮቱ እንደበር እያገለገለ ሽቀጦች ይደረደሩበታል። እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን ሁለት ግልጋሎቶች መገኘታቸውን ነው። ይኸውም ከሱቁ በተጨማሪ በትንሽ መሰላል ወደታች ይወርድና ምድር ቤቱ መኝታም ዕቃ ቤትም ይሆናል ማለት ነው። ሕፃናት መስኮቱ ላይ ተንጠራርተው አይደርሱበትም እንጂ መኖሪያ ቤት ውስጥ ኪምስክ ተፈጠረ ማለት ነው።

ኪምስክ ለማቆም የተለየ ቦታ ሲፈልጉ ወይም ሲመርጡ የመዋል ችግር እምብዛም አይኖርም። ግቢ ካለ ለአጥር የቆሙትን ሶስት አራት አሮጌ ቆርቆሮዎች ነቅሎ፣ እነሱን ጣራ ወይም ግድግዳ አድርጎ፣ በጐደለው ክርታሱንም፣ የውሻ ቤቱንም፣ ያረጁ ቆርቆሮዎችንም ጨምሮ መስራት ነው። ከዚያ በኋላ የአስፕሪን ወይም የፔፕሲ ምልክት በሩ ላይ ቆርጦ በክር ማንጠልጠል። እንደምገምተው በየአስፋልቱና በየድልድዩ ስር የሚሮጡ አንዳንድ ውሾች በዚህ ዓይነት

ማደሪያ ቤታቸውን እያጡ በመከፋት የተሰደዱ ሳይሆኑ አይቀሩም። መቼም በዚህ ወቅት አንዳንድ የፈረደበት ግራዋ፣ ኮባ ወይም የኮክ ዛፍ እንዲቆረጥ የሚደረገው ለኪዎስኮች ቦታ እንዲለቅ ሲባል ይመስለኛል። ለልብስ ማስጫ እንኳን ችግር አይኖርም። የማስጫው ገመድ ሱቁ ማገር ላይ ወይም ቆርቆሮውን በተጫነው ትልቅ ድንጋይ ላይ ሊታሰር ይችላል። ለዓውዳመት የሚመጣም ቢግ ካሉ—በዛሬ በግ ማነስ—ሽብ ለማድረግ ትንሽ ጉቶ መሳይ ይበቃዋል።

በቅርብ ጊዜ በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት የሚቆሙት ኪዎስኮች ከግቢ ውጭ ስራ የፈታውንና መንገደኛውን፣ ለመፀዳዳት የሚፈታተነውን ቦታ የሚሸፍኑና በኋላቸው ያለውን የግንብና ቆርቆሮ አጥር ድጋፍ አርገው ፌስታልና መሐረብ በሁለት ሶስት ቀን ውስጥ እያውለበለቡ ሰንደል የሚጨስባቸው ናቸው።

በርግጥም የኪዎስኮች መፈጠር እንደዱብእዳ ቢቆጠር አያስገርምም። እስቲ የምትኖሩበትን ሰፈር ልብ እያላችሁ ተዘዋወሩ። በቦኖ ውሃው በኩል እየተቻኮላችሁ ወደሥራ ስትሮጡ ግራ ቀኝ አልቃኛችሁ ይሆናል እንጂ ካንዱ አሮጌ ቤት ጐን ባዶ ቦታ ፈልጋ የተቀጠለች ገና ከእንቅልፋችሁ ሳትነቁ ሥራዋን የጀመረች ኪዎስክ ትኖራለች። አውቶብስ በምትጠብቁበት ፌርማታ አካባቢም ቢሆን ዱሮ የምትደገፉትን ግንብ በርቅሳ ከነበልኳ ጉብ ያለች አራት በአራት ስፋት ያላት ሱቅ ድንገት ልታጋጥማችሁ ትችላለች። ዱሮ ለማቋረጫ

የምታዘወትሯት ቀጭን የአፈር መንገድ ብትጠፋባችሁ ምልክቱ ወይም ቦታው የተረሳችሁ መስሏችሁ ባትገረሙ ይሻላል። ሥራዬ ብላችሁ ነገሩን ከተከታተላችሁ ሁለት ሰው በማያስተላልፍ ሽንጠ ረጅም ኪዎስክ የተደፈነ መሆኑን ትደርሱበታላችሁ።

ከኪዎስኮች አሠራር ትልቁ አስገራሚ ገጽታ በፍጥነት የመዋቀ ራቸው ሁኔታ ነው። ከምኔው ጉድጓድ ብጤ ሶስት አራት ቦታ ተምሶ፣ ከምኔው እንጨቶቹ ተተክለው፣ ቆርቆሮው በምስማር ተቸንክሮ፣ ጠባቂ እንደሚቀመጥበት ለማመን ያስቸግራል። ቤቱን ለመስራት የሚፈጀው ጊዜ ከአንድ ቀን ስለማያልፍ የዕለቱ ዕለት ዝናብ ያስጠልላል። በቀጠሮ ብዛት ስትጉላሉ ብዙ ወራት ላሳለፋችሁበት የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ፈቃድ ጧት ወጥታችሁ አስራ አንድ ሰዓት ግድም ስትመለሱ እንደ ዱብ እዳ የተፈጠረች ሱቅ በተለያዩ ዕቃዎች ታምቃ ከሰል እሳት ሲነድባት ማየት አያስቀናችሁም?

ሆኖም እንዲህ ዓይነቱ አሠራር የመቻኮሉን ያህል የጥበት ችግርም (ችግር ከተባለ ማለቴ ነው) አያጣውም። አሁን አንዳንድ ኪዎስኮች መስኮት መሳይ በራፋቸው በጣም ከመጥበቡ የተነሣ ቁመቱ ረጅም ለሆነ ሻጭ የመውጣት የመግባቱ ነገር ራሱን የቻለ መሰናክል ሲሆን ምንም አይቀረውም። እውስጥ የሚኖረው መጨናነቅ የዚያኑ ያህል ነው። በደንበኛውም በኩል ቢሆን ስልክ የሚደውል ወፍራም ሰው መግቢያውን ከተደገፈ ቦታውን በሙሉ ስለሚሸፍነው ዕቃ

ለመጠየቅ ያስቸግራል። እንዲያውም እንዲህ ያሉት ሱቆች በራቸው ላይ ሻሹን፣ መሐረቡን፣ ፌኛውን፣ ፌስታሉን፣ የጫማ ክሩን፣ ቀበቶውን ሁሉ አጠጋግተው ስለሚያንጠለጥሉ፣ ዕቃዎቹን ነፋስ ካላወዛወዛቸው በስተቀር አንዳንዱ ባለቤቱን ራሱን ቶሎ ለማየትና አነጋግሮ ለመገብየት አያመችም። ለተቻኮለ መንገደኛ ከሠልፍ ወደኋላ ያስቀራል። ጠፍቶ የዋለ አውቶብስ ያስመልጣል። ዝናብ ካለማ ኪዎስኮች በረንዳ እሚሉት ነገር ስለማያውቁ የሚኖረው አማራጭ ፌስታል ፊት ለፊት ቆሞ በጽሞና መበስበስ ነው።

የኪዎስክ አቀማመጥ ጐላ የሚለው አንድም ደማቅ ቀለም ያላቸው የተለያዩ ዕቃዎች በመደርደሪያው ላይ ችምችም ብለው ዓይን ስለሚስቡ ነው። በሌላ በኩል በጨው የሚፈላው ቡና፤ የሚቆላው ቆሎ፣ ሰንደሉና ዕጣኑ ሽታው ተደማምሮ ወከክ ካለው ከሰል እሳት ጋር ጠባቧን ክፍል ልዩ ሕይወት የሰፈነባት ያስመስላታል። ሌላው ቀርቶ በመብሰል ላይ ያለ የክክ ወጥ እንኳ ኪዎስክ ውስጥ ለየት ያለ ደስ የሚል ቃና ይኖረዋል።

የዕቃዎቹ አቀማመጥ ራሱ አንዳች ዘዴ ሳይጠይቅ አይቀርም። ምክንያቱም ተጨናንቆ የመቀመጡን ያህል መናጢ የሆነች አይጥ ካልገፋችው በስተቀር የታጨቀውና የተደራረበው ዕቃ ቦቴ ከነተሳቢው በደጃፉ እየተንደረደረ ቢያልፍ ከቦታው ዝንፍ ብሎ ሲወድቅ አይታይም። ታዲያ ባለኪዎስኮች የገበያተኛን ዓይን ለመሳብ ፊት ለፊት የሚደረድሯቸውን

ዕቃዎች የማይመራርጡ እንዳይመስሏችሁ::ወሬ ስታወሩዋቸው እንኳን የሚመልሱላችሁ አላግባብ የተቀመጠ ዕቃ በዐይናቸው እየፈላለጉ ነው:: ደሞ ሁለት ኒያላ አቀብለዋችሁ ከለኮሱላችሁ በኋላ አንዱን ፓኮ ከአንዱ ጥግ ወጣ አርገው ሌላው ጋ ሽጐጥ ሳያደርጉ አይቀመጡም:: በተለይ ገንዘብ የተቀመጠበትን ትንሽ ሣጥን ከቦታ ቦታ ማንቀራጠጥ ደስ ይላቸዋል:: ዕቃዎቹን የመነካካት ነገር ልማድም ስለሚሆን የሚሠራ እንኳን ቢጠፋ አቧራ ሳይኖርበት፣ ዝንብ ሳያርፍበት፣ አርፎ የተቀመጠውን ሚዛን በተነሱ ቁጥር በጭራ መታ ማድረግ ይቀናቸዋል::

ኪዎስኮች አነስ ጠበብ ያሉ ስለሆኑ ጽዳታቸውን ልጠብቅላቸው ላለ ሰው አመቺ ናቸው:: ረዘም ያለ መጥረጊያ ቢጤ ይዞ የተቀመጠ ሻጭ ከተቀመጠበት ለመነሣት እምብዛም ሳይደክም መደርደሪያው ላይ የምትቀናጣ ሸረሪት ከነድሯ ለማባረር ወይም ወለሉ ላይ የፈሰሰ ስኳር ጠረግ ለማድረግ ይቻለዋል:: ሆኖም ይሄ አባባል ዘይት የሚሸጥባቸውን ሱቆች አይመለከትም:: ምክንያቱም ከወለሉ ላይ ቢጠረግም ከሻጩ እጅ ምንግዜም ስለማይጠፋ ወደአንዳንድ ዕቃዎች ቃናው መጋባቱ አይቀርም:: ጋዝም ቢሆን በኮካኮላ ጠርሙስ የመሸጥ ጥድፊያን እንጂ የጽዳትን ጉዳይ ስለማያሳስብ መንጠባጠቡ ግድ ነው:: ስለዚህ አንዳንድ የምትገዟቸው ነገሮች ለምሣሌ ሲጃራ፣ ሻይቅጠል፣ ስኳር የጋዝ ቃና ቢያመጡባችሁ መነሻውን ለማወቅ መቸገር የለባችሁም::

የኪምስኮች ዋናው መለያቸው ቅልብጭ ደመቅ ያለ እይታ የሚጋብዙ መሆናቸው ነው። የዕቃዎቹ በቀለም መሻሮርጮር ራሱ ዓይን ማረፊያ ማሳጣት አለበት። የቀለማቱ ማማር ከልጆች ተርፎ አዋቂ ቢያማልል አያስገርምም። በተለይ ለልጆቹ አንዳች ነገር ይዤ ልግባ የሚል ሰው ከዳቦ ቤት ሲወጣ መንገዱን ወደኪምስክ ነው የሚያቀናው። ከረሜላው፣ ማስቲካው (ድቡልቡሉና ጠፍጣፋው)፣ ብስኩቱ፣ እሚቆረጠው፣ እሚበላው፣ እሚጠጣው ሁሉ በያይነቱ አለ። «ያ ፊኛ ስንት ነው?» የሚል አዋቂ ሰውም ቢያጋጥማችሁ ቤቱ ደርሶ ለልጆቹ እስኪሰጥ ድረስ መንገድ ላይ ሁለት ሶስቴ እየነፋ ሊሄድ እንደሚችል መገመታችሁ አይቀርም። አንድም የዘመኑ ጨዋታ ሊሆን ይችላል። ዋናው ግን ለሙከራ ነው — የተበላሸ አለመሆኑን ለማረጋገጥ።

የዕቃዎቹ አደራደር ራሱን የቻለ ዘዴ አለው ብለናል። እውነትም ልብ ብላችሁ ስትመለከቱ ጊዜያዊ ነገሮች ወይም ቶሎ የሚፈለጉ ዕቃዎች በቅርብ ነው የሚደረደሩት። ለምሳሌ የተለያዩ የከረሜላ ዓይነቶች በቆንጆ ቆንጆ ጠርሙሶች በረድፍ ይቀመጣሉ። ቅባት፣ ሳሙና የጥርስ ቡርሽ፣ ኮልጌት፣ የከንፈር ቀለም... በግራ በቀኝ ግድግዳዎችና በመደገፊያው ላይ መስተዋት ውስጥ ተጠጋግተው መታየት አለባቸው።

አንዳንዴ፣ አንዳች ብልጭልጭ ነገር ላይ ድንገት ዓይናችሁ ቢያርፍና «እስቲ ያንን አምጣው» ብትሉ «ናሙና ነገር ነው» የሚል መልስ ልታገኙ ትችላላችሁ። እንዲሁ ሱቅ

ለማድመቅ ከዕቃዎቹ ጋር የተቀላቀለና ዋጋ የማያወጣ ነገር ነው ማለት ነው። ለምሳሌ ባዶ ፓኬትና አርቴፊሻል መሳይ ብልጭልጭ ነገር ከክርታስ ተሠርቶ ቀለም የተቀባ አሻንጉሊት ሊሆን ይችላል። ከኪዎስክ መደርደሪያዎች ባዶአቸውን የሚሆኑ ቢኖሩ ጥቂቶች ናቸው። በመክሰር ላይ ያሉ ባለመጠጥ ቤቶች ቤቱ ባዶ እንዳይሆን ጠርሙሶችን ውሃ እየሞሉ ከደህናዎቹ ጋር እንደሚያስቀምጡት አይነት እነዚህም አልፎ አልፎ ሱቃቸውን ለማድመቅ ባዶ ቆርቆሮዎችን አሰባጥረው ቢያስቀምጡ አያስገርምም። ለምሳሌ ሼል ቶክስ፣ የላይተር ጋዝ፣ ቆርቆሮ ወዘተ።

ሌላው ሱቆች ይደምቃሉ የሚባሉበት ሁኔታ ውርውርታ የሚበዛባቸው መሆኑ ነው። «ያለሥራ መቆም አይፈቀድም» የሚል መስመሩን ያልጠበቀ ድርብ ጽሕፈት እንደ ማስታወቂያ ይለጠፍባቸዋል እንጂ ኪዎስክ ደጃፍ መቆም፣ ከመቆም አልፎ በክብ መቀመጥ፣ ጫት መቃም፣ ሲያወሩ መዋል ሁሉ የተለመደ ነው። ደላላው፣ አዋዋዩ፣ የአየር በአየር «ጥበበኛው»፣ የአሥራ ሁለተኛ ፈተና ሶስቴ ወስዶ ያላለፈው ሁሉ ኪዎስክ ደገፍ ሳይል አይውልም። ውኃ እሚቀዱ ሴቶች፣ ስልክ ደዋዮች፣ ፀሐይ እየሞቁ ጥርሳቸውን የሚፍቁ የሠፈር ጉረምሶች፣ መቅረሚያ ለብሰው ለልፊያ ዘና ብለው የሚታዩ ኮረዶች ሁሉ ኪዎስክን ሳይሳለሙ አይውሉም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሌላው ቀርቶ ከአደራ ዕቃ አልፎ ተርፎ በአደራ የተቀመጠ ራሱን የተላጨ ልጅ ሚዛኑ አጠገብ

ቁጭ ብሎ መኪኖችን ሲመለከት ሊያጋጥም ይችላል። ታዲያ ባለኪምስኮች የንግድ ቤታቸው ደጃፍና አካባቢያቸው በሰው ደመቅ ሲልላቸው ገበያ የመሳቢያ አንደኛው ምልክት አድርገው ስለሚቆጥሩት ፡ በጨዋታውም በቀልዱም መሣተፉን አይጠሉትም። ግርግር ወይም ጠብ ካልገጠማቸው በስተቀር በነገር አይተናኮሉም። እንዲያውም በዚህ ረጋ ያለ ባሕርይ ይታይባቸዋል። እንደመቆጣት እንኳ የሚቃጣቸው ስልክ ሲደውሉ ቶሎ የማይጨርሱ ደንበኞች ወይም ውሀ የሚቀዱ አንዳንድ ተጨቃጫቂ ሴቶች ሲያጋጥሟቸው ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ነው «ነጃሳ፣ የተለከፈ፣ ፋራ፣ ደቡር» የመሳሰለው የስድብ ቃል ከአፋቸው የሚወጣው።

አንዱ አንድ ጊዜ «ኪዎስክ ገንዘብ አይጠቅማትም» ብሎ ግጥም እንደጻፈባት በቅርብ ጊዜ ሰምቻለሁ። እውነትም ኪዎስክ የተጠቀለሉ ብሮች በግድግዳዎቿ የምትደብቀውን ያህል ከደንበኞቿ እጅ በእጅም፣ በዱቤም ደህና አርጋ ገንዘብ ትበላለች። የዚያኑ ያህል ደግሞ ግልጋሎት ትሰጣለች። በርግጥም ማንኛዋም ኪዎስክ እንደማነሷ የምትናቅ አይደለችም። ለምልክትነት በመዋል ከአጂፕና ሼል እንዲሁም ቶታል ያላነሰ ጠቀሜታ አላት። ለምሳሌ «የእንትን መሥሪያ ቤት የት ነው?» ብሎ መንገደኛ ሲጠይቅ «አ ያንን ቦቴ ታየዋለህ? እሱን አለፍ ስትል አንድ ኬክ ቤት አለ—ሰማያዊ ቀለም የተቀባ። ከዛ አንድ የተበላሸ ታክሲ አለ ... ተበላሽቷል ብዙ ጊዜው ነው። ... እጅህ ይረፍ አንተ ልጅ ዛሬ ቀን...

ቀጥሎ ደሞ አንድ ኪ.ሎስክ አለች—እዛ ጋ ነው» ምልክቱ ተገኘ ማለት ነው! እድሜ ለኪ.ሎስክ!

ኪ.ሎስክ አሁንም ቢሆን አትናቅም። ገበያ የጠፋ ላሙና፣ ቶሎ እሚጫረው ክብሪት፣ ፋርማሲ እስኪከፈት የሚዋጠው አልጮን፣ እነካፌኖል ከነዘሮቻቸው የሚገኙት እዛ ነው። መብራት ሲጠፋ ሻማ ለመግዛት፣ የሕዝብ ቴሌፎን ሲበላሽ ስልክ ለመደወል፣ በችግር ጊዜ እቃ ለማስያዝ፣ የጠፋ ሰው ለማፈላለግ ሁሉ እርዳታ ትሰግሳለች። ዝርዝር ስታጡ ቡና ቤትና ሊስትሮ በሌለበት የምታስተናግዳችሁ አንድ ጠማማ ኪ.ሎስክ መቼም የትም አታጡም። ለመስተንግዶው ብር ማስያዝ የማይሻር ደንብ ቢሆንም ከባለታክሲ ግልምጫ እንደምንም ትድናላችሁ። እድሜ ለኪ.ሎስክ!

ለመሆኑ መኖሪያ ቤቱ የጠፋባችሁን ሰው ኪ.ሎስክ ገባ ብላችሁ ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? ሁኔታው እንዲህ ይመስላል። ጠባቢ በር ጋ ቆም ስትሉ ከሰል በማራገብ ላይ ያለ ሻጭ ቀና ይልና «ምን ፈለጉ?» ይላችኋል። «ሶስት ኒያላ እስቲ»፤ «ቀጥሏል ኒያላ» (ወደምድጃው ዞር ብሎ)፤ «ምን እናርግ ፈቃድ የሌላቸው እየተጫረቱን ሥራ የታለ ብለው ነው?»፤ «በል ይሁን እስቲ... እባክህ አንድ እዚህ ሰፈር የሚኖር...»፤ «እኔ እንግዳ ነኝ ለሰፈሩ...»፤ «እባክህን የኔ ወንድም...»፤ «ምኑ ነዎት እርስዎ?» በዚህ አይነት ሳትለማመጡ አይነገራችሁም።

ታዲያ ባለኪምስኮች ጠቋሚነቱን እየጠሉ፣ «ምን አገባኝ» በሚል ፈሊጥ ጠንቃቃነቱን ያበዙታል እንጂ በክልላቸው ስላለው ሁኔታ ከሞላ ጎደል የማያውቁት ነገር የለም። ቁጭ ብለው ስለሚውሉ ብቻ ሳይሆን የሥራው ጠባይ ከብዙ ሰዎች ጋር ስለሚያገናኛቸው አዘውታሪ ወጭ ወራጁን፣ ቢሮ ተመላላሹን፣ መኪና የሚያሳጥበውን፣ ለሴት ቀጠሮ የሚያደፍጠውን፣ ዱርየውን፣ ሰካራሙን፣ ለማኙን ሳይተው ያውቋ ቸዋል። ወሬውንም ቢሆን ውኃ ከሚቀዱት ሴቶች፣ ማታ እቃቸውን እነሱ ጋ ከሚያሳድሩ ሊስትሮዎችና የመንገድ ሽቃጮች ይሰማሉ።

ሁሉም ሻጭ እየሆነ ገዥ እንዳይጠፋ እንጂ ኪምስኮች፣ እድሜ ለሰፊር ሰዎች፣ ደንበኛ ይበረክትላቸዋል። ዱቤ በመስጠትም፣ ከኮርፖ ሬሽን የሚወጡ እቃዎችን በመግዛትም ሳንቲም አይርቃቸውም። ደንበኞ ችም ቢሆኑ መርቆ የሚሸጥላቸውንና ለችግር ጊዜ የሚሆናቸውን ባለሱቅ አሳምረው ያውቃሉ። አጥብቀውም ይይዛሉ። «ከእገሌ ጋ አምጣ» የሚሉት ፈሊጥ አላቸው። የሚላከውም ትንሽ ልጅ ሽልንጉን ጨብጦ፣ በሌላው እጁ ቀበቶ እማያቅ ሱሪውን ከፍ አርጐ ይዞ ሲሄድ እግሩ እሚመራው ወደደንበኛው ሱቅ ነው።

በዚህ አጋጣሚ ትናንሽ ሱቆች ሳይ ከሕፃናት ጋር የማያያዝ ሁኔታ በአእምሮዬ ይመጣብኛል። ድሮ ልጆች ሆነን ... ምሽቱ ጫን እያለ ሊመጣ ሲቃረብ... ወደሱቅ ስንላክ... ከገበያው መሀል የቡና ቤቱ ማሾ ፏ ብሎ ቀጭን የብርሃን

መስመር ሲሰራ... የደንበኞችን ሱቅ ከነኩራሂ ጭር ብላ እየጠበቀችን ሳለች... የአሥር ሣንቲም ቡና ወይም የአምስት ሳንቲም ስኳር ገዝተን የከረሜላ ምራቂ ተቀብለን፣ የምሽቱን ቀዝቃዛ ነፋስ እያቋረጥን... በውሾች ጩኸት መሀል... በማሽላብ ላይ ወዳለችው ሰፈራችን ስንመለስ... አልፎ አልፎ ትዝታው ብቅ ይልብኛል። ታዲያ አሁንም አንዳንዴ ኪዎስክ በራፍ ላይ ግንባሩን ባንኮኒው ላይ ደገፍ አርጐ «ከረሜላ ካልሰጣችሁኝ አልሄድም» እያለ እሚያለቅስ ሕፃን ሲያጋጥመኝ ኩራሂ ጭል ጭል የምትል ሱቅ በሀሳቤ ውል ትላለች።

የጥንቷ ኪዎስኳ ከዛሬዎቹ ኪዎስኮች ብዙ የምትለይበት ሁኔታ መኖሩም አብሮ ይታሰበኛል። ጥቂቱን እንኳ እንጥቀስ ብንል ያለቀ ባትሪ ድንጋይ፣ ቃናውን የሚለውጥ ሲጋራ፣ የተሰራበት እስክሪፕቶ፣ የክብሪት ጐደሎ፣ የደነዘ ምላጭ ያኔ አልነበረም። የኪዎስኮች ሁለገብነታቸውም አያጠያይቅም። ከዕቃ በተጨማሪ ምስር፣ ክክ፣ ቅመማቅመም፣ የጢስ እንጨቶች፣ ሳምቡሳ፣ጫት፣ ጐመን፣ ቀጤማ፣ አሪቲ፣ በሶብላ ሁሉ አላቸው። እስካሁን ያላጋጠመኝ ሽንኮራና ሽምብራ እሸት ብቻ ነው።

ቤሳ ልቦለዶች

ቤሳ ልብወለዶች ሲባሉ ለጥሩ አባባፍ አስፈላጊ ናቸው የተባሉትን አለማሚላታቸው ዋንኛው መታወቂያቸው መሆኑ መቼም አያጠያይቅም። እዚያም ሳንደርስ፣ ውስጣቸውንም ገልጠን ሳንመለከት፣ ገና ከውጭው የምናያቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ የገፃቸው ብዛት ብዙ ጊዜ ከሰባና ከሰማኒያ አይበልጥም—ብአነስተኛ ጥራዝ። የደራስያኑ ፎቶግራፍ በሽፋኑ ጀርባ ባይኖር ከውስጥ አይጠፋም። አንዳንዶቹ መታሰቢያ ያደረጉላቸውን ዘመድ ወዳጆች ፎቶም ያወጣሉ። ከደራስያኑ ፎቶ ግርጌ «ጥልቅ አስተያየት» የማያኖሩ ጥቂቶች ናቸው። በመጀመሪያዎቹ አምስት አስር ቅጠሎች የደራሲውን መብት ለመጠበቅ ከሚጻፈው የተለመደ አባባል አንስቶ ታሪኩ እስከሚወነጨፍበት የመጀመሪያ ምዕራፍ ድረስ መዘክር፣ መቅድምና መግቢያ ይጻፍባቸዋል።

አልፎ አልፎ ስለተመሳሳይ ፊደሎች አጠቃቀም አጠር ያለ መግለጫ የሚሰጡም አሉ። በስመ ሞክሼነት በሕይወት ያሉ ሰዎች ከታሪኩ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑንና መስሎ ቢታይም ያጋጣሚ መሆኑን ጠቅሶ በትሕትና ይቅርታ መጠየቅ የተለመደ ነው። አልፎ አልፎ በጽሑፋቸው መሀል ግጥም የሚደባልቁም አሉ። አንዳንዶቹ እንዳሰኛቸው ግማሹን በስድ ንባብ የቀረውን በግጥም ያቀርቡታል። በአጠቃላይ

ሲታይ፣ አብዛኞቹ ታሪካቸውን የሚደመድሙት የግጥም መግለጫ በመስጠት ነው።

ቤሳ ልቦለዶች በጣም ከሚታወቁባቸው ምልክቶች አንዱ አርእስት አወጣጣቸው ነው። አንዳንዱ ርዕስ ታሪኩን ባጭሩ ይናገራል። አንዳንዱ ተሰምቶ የማይታወቅ ቃል ወይም ሐረግ ይሆናል። አብዛኞቹ ግን ስለሰው ተፈጥሮ፣ ስለሕይወት፣ ሞራላዊ የሆነ ፍልስፍና ነክ ምክር መያዛቸው አይቀርም። ለምሳሌ ያህል አጠቃላይ መልካቸውን በሁለት ሶስት አርእስት አስመስሎ ማስቀመጡ ያልታሰበ ማጋነን እንዳይሆንብን እንጂ የሚጽፍባቸው ርዕሶች አጠቃላይ መንፈሳቸው ሲታይ «ሰው ሆይ ማንን ትመስላለህ?፣ ሰው ለጋብቻ እህል ለስልቻ፣ ዲዲሞስ የበረሃው መላከተኛ. . .» የሚል ዓይነት ቃና ያላቸው ናቸው።»

ስለርዕስ ዓይነቶች ሐተታ ከማስፈርና በገበያ ላይ ያሉትን ከመጥቀስ ይልቅ መሰል የሆኑና ሊወክሏቸው የሚችሉ የመሰሉኝን አንዳንድ አርእስት በተለያየ መልክ ራሴ አውጥቼ እንደሚከተለው አቅርቤያቸዋለሁ። ምሳሌዎቹ በሙሉ ራሴ የፈጠርኳቸው መሆኑን በድጋሚ መናገሩ ሳይጠቅም አይቀርም። *«የሰሜት መሰላል፣ የእኔነት መነጽር፣ ሳይገሉ ተኳሉ፣ በእንቆቅልሽ ደከምኩልሽ፣ አቶ እውነቱ፣ እጮኛ ለጓደኛ፣ የሕይወት ቡራኬ፣ ቃሜላድ ጠቢቡ፣ ሠርግና መርዶ፣ ጥፋቱ የኔ ነው፣ የፍቅር ሸለቆ፣ ያልቀበረ መሰከረ፣ የቀትር ምች፣ ተዝካሯ ላይ ደረሰኩ፣ እንዴት አደርክ?፣*

የሕሊና ገባር፣ ጽልመተ ኦክብ፣ ያላሰበ ተጠረበ ወዘተ... ከነዚህ አርእስትም ሆነ በእነዚያ ላይ ከሚመጡት መካከል ጥሩ ድርሰት ሊያጽፉ የሚችሉ የሉም ማለት አይደለም። ድክመት አለባቸው ብለን ዛሲ ከምንሰነዝርባቸውም ውስጥ ቢሆን ደህና ሙከራ የሚታይባቸው አልፎ አልፎ ይገኛሉ። ለገበያ የሚጽፉና የራሳቸውን ወይም የሚያውቁትን ሰው ታሪክ እንዳለ ቀርጸው የሚያቀርቡ ባይታጡም በኪነጥበብ ፍቅርና የመጻፍ ፍላጐት የሚነሳሱም ስለሚኖሩ አስተያየታችን ሁሉንም በጥቅሉ የሚመለከት አይሆንም።

እንዲያውም በዚህ ረገድ ጠቀስ እናድርገው ከተባለ፣ የሚያነሳቸው ነገሮች ከሀገርና ከወገን ፍቅር፣ ከአክብሮት ጋር የተያያዙ ሆነው ባህልና ታሪክን፣ ማህበራዊ ኑሮን፣ ስራን የሚመለከቱ ናቸው። ብቻ ችግሩ፣ አቀራረባቸው በግርድፍና ትኩረት ባጣ መልክ ነው የሚሆነው። ሞራላዊ ስብከትና ማጋነን፣ ጀብደኝነት ይጐላባቸዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የማሳመንና የማርካት ኪነታዊ ኃይል ያንሳቸዋል። አንድም የልብወለድ ውበትና ቴክኒኩ ላይ ካለማተኮር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሙያውን ለማዳበር (ለምሳሌ በማንበብ) ካለመጣር የተነሣ የሚመጣ ችግር ነው።

ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ ለጀማሪ ደራስያንና የልብወለድ ንባብ ልምዱ ለሌላቸው አንባብያን በምሳሌነታቸው አሳሳች ነጥቦችን ጥለው እንዳያልፉ ጎላ ያሉትን ደካማ ጎናቸውን ማውሳቱ ጠቃሚ መሆኑ አይታበልም።

ቋንቋ ትልቅ መሳሪያ ነው —ባግባቡ ከሰሩበት። በገለጻና በዘይቤ እንዳስፈላጊነቱ በትክክል መጠቀም፣ የሰዎችን የአነጋገር ሁኔታ፣ በባህሉ ያለውን የሰላምታ ልውውጥ፣ ጭውውቱን፣ የተረትና ምሳሌውን አገባብ ከነዚህ ጋር አብረው የሚሄዱትን እምነቱን ልማዱን በደንብ ማወቅ ያስፈልጋል። በተለይ የሰዎችን የተለምዶ አነጋገር ከነለዛው ለመያዝና ያንን የመሰለ የንግግር ልውውጥ በልብወለድ ለመፍጠር ጆሮን በደራሲ ምናብ ማሰልጠን፣ በብዕርም መለማመድ ያሻል። ቃላትንና ዓረፍተ ነገሮችን ቋንቋው በለመደው መንገድ መጠቀም ለመግባቢያ ብቻ ሳይሆን ለአጻጻፍ ውበትም እንደሚረዳ የታወቀ ነው። በኪነታዊ ግፊት የሚፈጠር አንዳንድ ወጥ (original) አባባል ወይም አገላለጽ መምጣቱ ስለማይቀር፣ ደራሲው በዚህ ረገድ ተቀባይነትን ሊያገኙ በሚችሉ ሁኔታዎች ላይ በቂ ትኩረትና ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል።

ስድ ንባብ እንደግጥም ከፍተኛም ባይሆን፣ የራሱ የአወራረድ ቃና (ፍሰት) እና ለጆሮ የሚስማማ የማይሰለች ዜማ አለው። ይሄ ነው ተብሎ ጉልህ በሆነ ሁኔታ ሊጠቆም ባይችልም፣ በዓረፍተ ነገሮች መካከል፣ በተለይም በአንቀጽ ውስጥ በሚሰጠው ስሜት ዜማው የማይጐረብጥና የማያደናቅፍ መሆኑ ያስታውቃል። ስለዚህ የዓረፍተ ነገሮችን ዓይነቶች በተቻለ መጠን መለዋወጡ፣ ረጅሙን ከአጭሩ ማሰባጠሩ ደግሞም ከዚያው ጋር ቃላትን አለመደጋገም፣

በተለይም ማሠሪያ አንቀጾችን መቀያየር ለዛና ጣእም በመፍጠር ጥሩ ተደማጭነትን ከማትረፉም በላይ ለአብዛኛው ሰው የአነባብ ምቹ መንገድ መፍጠር ይሆናል። ሥዕላዊና አስረጅ ገለጻም ሊያስፍሩ ዓረፍተ ነገሮቹ የሚያስ ተጋቡት ድምፀት (tone) ወደሌላ አለመሄዱን ማረጋገጥና ተፈላጊውን ጉዳይ በሚገባ መጠቆሙን ማስተዋል ለቀልጣፋ አቀራረብ ያግዛል።

የቋንቋ ሌላው ዋና ተግባር ለድርሰት ኪነጥበባዊ ቀለም (creative colour) ማስገኘት ነው። ኪነጥበባዊ ቀለም ሲባል በቋንቋ ጥሩ አጠቃቀም የሚከሰት ውብ የሆነና ስሜት የሚማርክ አቀራረብ ማለት ነው። ለይዘቱ ሕይወት ይሰጠዋል። ጽሑፉን ተነባቢና ተናፋቂም ያደርገዋል። ለአንባቢው መንፈስ የሚማርክና የሚያስደስት የተመስጦ ጊዜን ከመለገሱም በላይ በታሪኩ ውስጥ ጥሩ ምናባዊ ተሳትፎም ስለሚሆንለት መጠቅ ካለ እርካታ ጋር አስተሳሰቡንና የስነ ውበት (aesthetic) ክልሉን ያሰፋለታል።

ታዲያ በዚህ ረገድ የቤሳ ልቦለዶችን ደካማ ጐን የተመለከትን እንደሆነ የቋንቋውን ልማዳዊ አካሄድ ካለማስተዋልና ካለማጤን፣ እንዲሁም በበቂ ልምምድ ኪነጥበባዊ ለዛና ድምቀት ላይ ካለማተኮር፣ እናም ችሎታን ካለማዳበር የሚመጣ ችግር ሆኖ እናገኘዋለን። የብዙዎቹ ችግር በጣም አብረቅራቂ በሆነ ቋንቋ (flowery language) የመጠቀም ልምድ መሆኑን በሁልጊዜ ንባብ የምናየው ነው። ቋንቋ

አብረቅራቂ ሆነ የሚባለው ከሚያስፈልገው በላይ ተጋኖና ተንዛዝቶ ደማቅ ቀለሙን ብቻ ወርውሮ ምንነቱን ለማየት እንደማይጋበዝ የቡና ቤት ስዕል በገጾች ላይ ዝም ብሎ እየጨፈረ የሚያሰለች፣ ለይዘቱ ምንም ዓይነት ጉጉት የማይጭርና በቂ ግንዛቤም፣ ኪነታዊ እርካታም የማያስገኝ ሆኖ አላግባብ ሲንዘላዘል ነው::

በአብረቅራቂ ቋንቋ የሚጻፍ ድርሰት በኪነጥበብ መድረክ ላይ መረን ያጣ ግልቢያ ማስጋለቡ አንድና ሁለት የለውም:: ሰማዩንና መሬቱን ከመግለጽ አይቆጠብም:: ሁሉን ነገር እንደሰዓት ሠሪ በታትኜ ካላየሁ ይላል:: የተበታተኑትን ግን መልሶ አይገጥምም:: ሰውኛ ዘይቤ (personification) ይሞጀርበታል:: ሳር ቅጠሉ፣ ቤቱ፣ ተራራው፣ ወንዙ፣ ድንጋዩ አፍ አውጥቶ ይናገራል:: ያልታደሉት ገፀ ባህርያትም አፋቸውን የተለጐሙ ይመስል ሌላውን ሁሉ አናግረው ራሳቸውን ይረሳሉ::

ይልቁንም ባንድ ቃል ፋንታ ሁለቱን ማጣመር፣ ወይም ምንም ዝምድና የሌላቸውን ነገሮች እንደፈለጉ ማገናኘት የተለመደ ነው:: «ዘነበ» በማለት ፋንታ «የውሃ ጠብታዎች ወደቁ» ሊል ይችላል ማለት ነው:: «ሁለቱ ሰዎች ተገናኙና ተነጋገሩ» ለማለት «...ንግግራዊ ግንኙነት አደረጉ» ቢል ጠባዩ ነውና ከማንበብ በስተቀር ምንም ማድረግ አይቻልም:: እንዲያውም በንግግራቸው መጨረሻ ላይ ሰላምታ ተጨምሮበት ከሆነ «ንግግራዊ ግንኙነታቸውን በሰላምታ

አሳረጉት» በሚል ሊራዘም ይችላልና ዘና ብሎ መቀበል ነው። በዚህ ዓይነት፣ «... *በስለት የተቆረጠ የዳቦ ቁራሽ የምታክል መጽሐፋቸውን በረጋግደው ከግራ ወደ ቀኝ በሚመላለሱ የፊታቸው ንቅናቄ ንባባቸውን ተያያዙት*» የሚል ዐረፍተ ነገር ባንድ ጽሑፍ አጋጥሞኛል። እኔም በዚያ አጋጣሚ አንድ ዓረፍተ ነገር ምን ያህል ሊረዝም እንደሚችል ማሰብ ጀምሬ ለመጻፍ ሞክሬ ነበር። ይኸውም «እንጀራ በላ» የሚለውን ወስጄ «*በቀኝ እጁ እንጀራውን ከቆረሰ በኋላ ሳህኑ ውስጥ የነበረውን ወጥ አጥቅሶ ወደ አፉ በማስገባት በመንጋጋው አኝኮ በምላሱ አማካይነት ወደ ጉሮሮው ቧንቧ በመወርወር ሆዱ ውስጥ አሰገባው*» ማለት ይቻላል ማለት ነው። ታዲያ አንድ ወዳጄ ይሄን አይቶ «የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ላይ ወጥ እሚል የለም፤ አንተ ከየት አመጣኸው?» ብሎኝ ነበር። እኔም «በቃሪያ በላ ካላለ በስተቀር ያው በወጥ መሆን አለበት ብዬ ነው» ስል መልሼለት ተግባብተናል።

እንዲህ ዓይነቱ የቋንቋ አጠቃቀም እውነታውን ጥሎ ሲፈነጭ ከሁሉም በላይ የሚጐዳው ገፀ ባሕርያቱን ነው። ይኸውም አንደኛ ለነሱ ሊውል የሚችለውን ገለፃና የትረካ ጊዜ ያባክናል። ሁለተኛ መቼቱን (setting) በዚህ ዓለም የሌለ አድርጐ ሲያቀርበው፣ ለአንባብያን ምናብ ገፀ ባህርያቱ (characters) በልዩ የዛር አገር ወይም መናፍስት ደሴት ውስጥ የተፈጠሩ ምስኪኖች ያስመስላቸዋል። ማታ እሳት ዳር በሚወራ ተረት የሰሟቸውን ዓይነቶች እንጂ ምድራዊ

አይሆኑላቸውም። ይህ ስሜት ከመጀመሪያው ከተፀነሰ ደግሞ በኋላ ለመለወጥ ያስቸግራል። ለማናቸውም ግን እዚያ ላይደርስ ከወዲሁ ትረካው ራሱ ዘጊ እየሆነ ለመቀጠል ያስቸግራል።

ቤሳ ልቦለዶች ውስጥ የሚፈጠሩት ገፀ ባሕርያት በቋንቋ መረን አጣሽነት ባይበከሉም፣ ከስም አወጣጥ ጀምሮ፣ በዚህ ዓለም የሌሉ ዓይነቶች ናቸው። አልፎ አልፎ ለመጥቀስ ያህል የለቀምኳቸው እነሆ። *ቤልሆር፣ ቂያሜር፣ ጃጃ፣ ምርምር፣ ቂፍቄ፣ ካክሬ፣ ቤንቢን፣ ኮፖሌፍ፣ ኪያቤር፣ ዛቆር፣ ጋጀማ፣ ሞራድ፣ ቆሮኖ ሊዎስ፣ ጴዛፊ ዶን፣ ቤንሳኒር፣ ደጋሎ፣ ዛክትሮስ፣ ሰብአራ፣ ጐማር፣ ጦብሪያኖስ፣ ፎፎ፣ ሳንዚነር፣ ዛፉር።*

አቋማቸውም ልዩ ነው። አንዳንዶቹ በናታቸው ሆድ ቋንቋውን ለምደው፣ ተምረው፣ ጥርስ አብቅለው ይወለዱና አምስት ዓመት ሳይሞላቸው ጣታቸውን እየቀሰሩ ዲስኩር ያደርጋሉ። ከባድ የተፈጥሮ አደጋ ላይ ወድቀው —ለምሳሌ ትልቅ ባሕር ላይ ተንሳፈው፣ ሰው በማይደርስበት ገደል ስር ተጥለው አቅም ሳይኖራቸው ያለምንም ዕርዳታ የተደቀ ነባቸውን ጋሬጣ በጣጥሰው የሚወጡም አሉ። ለምን እንደሆነ አላውቅም፣ ልክ በዚህ አንባር የሚታመን ገፀ ባሕርይ ይፈጥሩና በተግባር ላይ ግን ሳይውል እንዲቀር ያደርጉታል። አስተዋይና ብቁ ነው ብለው ይናገሩለትና በችሎታው ሲሰራበት አይታይም። ብቻ እናት አባቱ ያወጡለት ስም ይመስል

በየምዕራፉ እንዲሁ ሲጠራበት ይውላል። ስለዚህም መቃብር ሐውልት ላይ እንደተቀረፀ ፊደል 'ነበር' ተብሎ ይነበብና ይረሳል። በዚህ ዓይነት አንባቢው ዓብይ ሚና ያላቸው መስሎት ከሁነኛ ትርጓሜ ጋር ሲጠባበቅ፣ ብዙ ገፀ ባሕርያት በታመቀ መልክ በጥቅሉ ተጠቅሰው ይታለፋሉ።

የዚህ ችግር መነሾው በአንድ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ዋንኛው ግን ደራስያኑ ገፀ ባሕርያቱን በድርጊት አያንቀሳቅሷቸውም። አለበለዚያማ በጠባብ ቀዳዳ ሾልኮ ላይሾልክ፣ ወይም ጠላቱ እግር ሥር ተደብቆ ላያመልጥ፣ ወይም አጫዋች ሆኖ ላያዝናና ካልቸገረ ቁመት የግማሽ ሜትር ድንክ መፍጠርን ምን አመጣው? ለሁሉ ነገር ምክንያት መኖር አለበት ባይባልም፣ አንዳንድ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ ለገፀ ባሕርያት ዝም ብሎ ምልክት መስጠት የሚያመጣው ጥቅም አይታየኝም።

አሁን ለምሳሌ አነጣጥሮ ካልተኮሰበት፣ ወይም አስተዳደጉንና ጤንነቱን በሚመለከት ታሪኩ አንዳች መነሻ መድረሻ ኖሮት በቂ አስተዋጽኦ ካላደረገ በስተቀር ከመሬት ተነስቶ ደህናውን ሰው አንድ ዓይና ማድረግ ምን ያስፈልጋል? ለወጥ ያሉ ሁኔታዎችን ያለምክንያት በቁማቸው ለመናገር ሲባል ብቻ ለገፀ ባሕርያት ደማቅ መለያ አይበጅላቸውም። ስለአንድ ገፀ ባሕርይ አበክረውና ደጋግመው ከተናገሩ፣ እናም የሚጫወተውን ሚና ከተናገሩ፣ ወይም የሚጫወተው ሚና

ለታሪኩ ተገቢነት ያለው ከሆነ፣ ቢያንስ አንድ ትዕይንት ፈጥሮ ሁኔታውን ባንባቢው ምናብ እንዲቀረፅ ማድረግ ያስፈልጋል።

በቤሳ ልብወለዶች የሚቀረጹ ገፀ ባሕርያት በድርጊት ላይ በመዋል ፋንታ በአስገራሚ ተፈጥሮአቸው ተወልደው በአስገራሚ ተፈጥሮአቸው በሚገባ ሳይታወቁ እንዲሁ ይቀራሉ። በሁነኛ ዓላማ ተነሳስተው ኪግባቸው ሲደርሱ አናያቸውም። ከስሕተታቸው አይማሩም፤ አይለወጡም። ብቻ የደመነፍሳቸውን ባጋጠማቸው ጉዞ ላይ የመንቀዋለል ውሎ ይውላሉ። ሰዋዊ ባሕርይ የላቸውም። በተለያየ መልክና ቁመና፣ ጢማቸው ደረታቸውን ያለበሳቸው፣ የጥፍሮቻቸው አረዛዘም ከጣታቸው የሚበልጥ፣ ጀሮአቸው ወደዓይናቸው ተቆልምሞ የመጣ፣ ክርናቸው ፀጉር ያበቀለ እየተደረጉ ይቀረጻሉ።

ለየት ያለ አፈጣጠር ከታሪኩ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳይኖረው ለገፀ ባሕርያቱ ምንነት ወሳኝ ሊሆንም ይችላል። ቅንድቡ ስለሸበተና ጥርሶቹ ስለተበላለጡ ብቻ ክፉ (ጨካኝ) የተባለ ገፀ ባሕርይ አለ። ይህን ጽሑፍ በማዘጋጅበትም ጊዜ «ኪስ የሚያካክሉ ዓይኖች፣ እንደግራኝ መሐመድ ረጅምና ግዙፍ የሆነ መርከበኛ በአንድ የሳይንስ ልቦለድ አጋጥሞኛል» ሲል ያጫወተኝ ሰው አለ። ይሄንን ስሰማ፣ አንድ ኮሰስ ያለ፣ ድምፁ የደከመበት ገፀ ባሕርይ ሳይቸግረው ተቅለብልቦ እዚያ አካባቢ ውልብ ቢል፣ ወዲያውኑ ያለምንም ማመንታት እንዴት ፈሪ እንደሚደረግ ሁኔታው

ሁሉ በገሀድ ታየኝ። ገፀ ባሕርያቱ የሚሰጣቸው አካላዊ ገለጻ እጅግ የናረ ብቻ ሳይሆን ፍፁም በሆነ አቀራረብ በሐሳባዊ አመለካከት የተዋጠ ነው። ለምሳሌ በአንድ መጽሐፍ ላይ ወጣቷ እንዴት ውብ ተደርጋ እንደተቀረጸች እንመልከት፤

«ግሪኮች ቢያይዋት በሆሜር ዘመን የነበረችው በመንፈስ ሕሊና የሚያምኑባት የቁንጅና አምላክ በማለት በሰገዱላትም ነበር። ሮማውያንም በበኩላቸው የለም ይህች የኛ ቬኑስ ናት ብለው ከግሪኮች ጋር ሞረማ ሲጀምሩ፣ ግብጾች ቢያዩዋት ኖሮ ደግሞ ግማሾቹ ንግስት ኪሊዮፓትራ ብለው ሲሰግዱላት፣ ገሚሶቹ ነፈርቲቲ መስላቸው በግንባራቸው በተደፉም ነበር።

«አፍንጫዋ እንደ ስንደዶ ቀጥ ያለ ሆኖ የጣሊያን አርቲስትና ሊቆች ማይክል አንጀሎና ሊዮናርዶ ዳቬንቺ ተወራርደው ያስተካከሉት ወይም ስመጥሩው የሀገሬ ሰዓሊ አፈወርቅ ተክሌ በጥረት ያቀናው ይመስላል። ከንፈርዋ አሁን የፈነዳ ትኩስ ጽጌረዳ ይመስላል። ብርሌ አንገቷ ያለ አንዳች ልፋት ለመዞር እንዲመቻት በክንድ ተሰርቷል። ዓይኖችዋ የበጋ ጨረቃ አካክለው መለስለስ ስታደርገው ያያት ሳይወድ እንደታቦት እጅ ይነሳታል። የማዳም ኩሪ ካውያ ያላየው ጸጉርዋ የተገማሸረ ያራዳ ጤፍ መስሎ ከመጋሸቡ የተነሣ ለሸ ያለ መስሏል። በብርሌ አንገቷ በኩል ርችቱ ቁልቁል ወርዶ ሁለቱን ትከሻዋን እንደጋሻ ጃግሬ አጫፋሪ አርጎ በጀርባዋ ተጥመልምሎ ከዳሌዋ ደርሷል። እግሮችዋ ዝቅ ብለው ሲታዩ

ከፍጥረታቸው ጀምሮ ምድርን የረገጡ አይመስሉም። የግር ጣቶችዋ ረዘሙ አጠሩ የማይባሉ እንከነቢስ ሲሆኑ፣ ጥፍሮችዋ በቅርጽ በቅርጽ ሆነው በምስጉን ሰዓሊ የተስተካከሉ ናቸው። እንዲያው በጠቅላላው ጫማ አይቶ የማያውቅና የጫማ ጉጥ (ባሎ) ያላደፈረሰው ቁንጅና የአምላክን ረቂቅ ስራ ያመሰግናል። ዋ ሼክስፒር ቢኖር ኖሮ እኮ «አንቺ የበረሃ አበባ» ያላት ይች መስላው ሌላ ጥበብ ትንግርት የተሞላበት ቅኔ ባዥጐደጐደላት ነበር። የዓለም አንትሮፖሎጂስቶች ቢያይዋትስ? የመጀመሪያዋ ሔዋን ይህች ናት ብለው ባተቱላት ነበር። የዳሌዋን፣ የባት ተረከዝዋን መዘብዘብ ሌላ ታሪክ ነው። እንዲያው በደፈናው የውበት ሶፋኒት ናት ብሎ ማለፍ ይቀላል። «አልማዝ ነች የጠራች መስተዋት እንከን የሌለባት» የሚለውን ግጥም ለዚህ ሥፍራ ብናውለው ስሕተት አይሆንም።»

ጽሑፉ የማይጠራው ነገር የለም። ከጥንቶቹ ግሪኮች ይነሣል። የሆሜር ዘመንም ከጥንቱ የተለየ ይመስል በድጋሚ ይነሳል። ሮማውያኑ ከአማልክቶቻቸው፣ ግብጾች ከንግስቶቻቸው ጋር ይጠቀሳሉ። ኪሊዎ ፓትራና ነፈርቲቲ ስለውበት የሰውን ልጅ እንደገና ለማሰገድ በነፋሪት ሰረገላቸው ወደጥንታዊቷ ገበያ ይገሰግሳሉ። ግሪኮችና ሮማውያን የውበት ምስክር ለመሆን ለምን እንደበቁ ግን ምንም እሚታወቅ ነገር የለም። ማይክል አንጀሎና ሊዎናርዶ ዳቬንቺ በአፈወርቅ ተክሌ ደቀ መዝሙርነት በአድናቆት ያጅቧታል። ዊሊያም ሼክስፒር በግጥሙ ሊያሞግሳት አበባ ፍለጋ በረሀ ለበረሀ ይንከራተ

ትላታል። የዓለም አንትሮፖሎጂስቶችም የሰው ዘር ከገንጆሮ መምጣቱን እያወቁ፣ የዕፀ-በለሱን ሕግ በጣሰችው በሔዋን ይመስሏታል። በቁንጅናዋ ላይ አሻጥር ሊሰሩባት ፈልገው ግን ሳይሆን አይቀርም። «ሴት ተንኰለኛ ነች» ማለታቸው ሊሆን ይችላል።

ሁሉም የመጡት እሷን ለማድነቅ ነው። ባለፀጉር ካውያዋ ማዳም ኩሪ የአዲስ አበባዋ (የዶሮ ማነቂያዋ) አርመን ትሁን የፈረንሳይዋ ሳይንቲስት አልተገለፀም እንጂ ሁሉም ከልጅቷ ጋር መልካም መታሰቢያ አግኝተዋል። የኢትዮጵያ እውቅ ዘፋኝ ጥላሁን ገሰሰ ከወሊሶ እንደመጣ ሰሞን የዘፈናትን ዘፈን ይዞ፣ እንደምንም ተጨናንቆ ከወደመጨረሻው ግድም ገብቷል።

ታዲያ እንዲህ መሆኑን ስትመለከቱ ውበት የሚባለው ነገር ወደአስቀያሚነት እንኳን ባይለወጥባችሁ የአቀራረቡ ነገር የመናፍስት ዓለም (ፌይሪላንድ) ተረት አይሆንባችሁም? አንድ ፈረንሳዊ ፈላስፋ «በነገር ሲራቀቁ ያለው ታላቅ ጉድለት በነገሩ ባለመድረስ አይደለም። የነገሩን ወሰን አልፎ በመሄድ ነው እንጂ» ሲል የተናገረው ያለምክንያት አይደለም። እኔ በበኩሌ ግሪኮች ቢያይዋት ብሎ ገና ሲጀምር የውበት አምላክ ካለች ክንፏን አራግባ ወርዳ ይሄንን ጽሑፍ ራሱን ብታየው ምንኛ ትገረም ነበር የሚል ሐሳብ ነው የመጣልኝ። እንዲያውም «ይሄ ሁሉ በኛ አገር የት አለና!?» ብላ ለደራስያን ቃለ

መጠይቅ መልስም ሳትሰጥ ተመልሳ ትሄድ ነበር ብዬ ደምድሜያለሁ::

የገለጻውን ያህል ባይሆንም ድግግሞሽ ይበዛበታል:: አንገት አንዴ ብርሌ ይሆናል:: አንዴ በክንድ ይሰፈራል:: ዞሮ ዞሮ ግን ረጅም ነው ለማለት ነው:: የእግር ጣቶች ረጅምም አጭርም የማይባሉ ናቸው:: ቧቅርጽ የተስተካከሉም እንከን-ቢስም ናቸው:: ፀጉሯ እንደጤፍ ለሽ ያለ ነው:: ካውያ አላየውም:: ተጥመልምሎ እዳሌዋ ደርሷል:: የሚደርሰውም በጀርባዋ በኩል ነው:: ታዲያ ዱሮስ እንዴት ሆኖ ሊደርስ ነበር? «እግሮቿ ዝቅ ብለው ሲታዩ» የሚልም አለ:: አሁንስ ቢሆን እግር ሲፈጠር ዝቅ ብሎ እንጂ መቼ ሽቅብ ወጥቶ ያውቃል?! ነገር ነገሩ «ሾርባ በማንኪያ ጠጣሁ» ፣ «በእስክሪብቶና ወረቀት ጻፍኩ» እንደማለት ነው::

እሱ ሲገርመን «ሁለቱን ትከሻዎቿን» ይልና ይቀጥላል:: ባለአንድ ትከሻ ሰው በላቦራቶሪ እስኪፈጠር ድረስ ይሄም አስፈላጊ አልነበረም:: ሌላም ብዙ የቃላት መደረትና የሐሳብ መባከን አለበት:: ርችት፣ በግንባር መደፋት፣ መስገድ ጥቂቶች ናቸው:: ጤፉ ካልጠፋ ቦታ የአራዳ መሆኑ ከገለጸልን ውበት ጋር አብሮ አይሄድም:: እህሉ ታጭዶ ተወቅቶ ለገበያ ከቀረበ በኋላ ለምሳሌነት መዋሉ ደግ አይደለም:: ለንጽጽር ያዘረዘረው ጤፍ ከነፋሱ ጋር ግብግብ እንደመግጠም እያለ ገና በአዝመራነት እንደለመለመ በገጠር እያለ፣ እዚህ በነጋዴ

ጐርናና ድምፅ የዋጋ ክርክር እንዲጠፍበትና በቦት ጫማ መሬት እንዲደቃበት ለምን ይደረጋል?!

አንዳንዱ አገላለጽ የተጋነነ ብቻ ሳይሆን ፍፁም በማይመስል መንገድ የተዛባ ሐሳብም የያዘ ነው። «አንገቷ ያላንዳች ልፋት ለመዞር እንዲያመቻት በክንድ ተሰርቷል» የሚለውን እንመልከት። መቼም አንገት የኮክ ፍሬ ከመሰለ ማንቁርትም ጋር ሊረዝም—ብመርዘሙም እንደልቡ ሊዞር ይችላል። ቢሆንስ ለውበት እንዴት ምክንያት ይፈለግለታል?! አፍንጫ ሰልካካ ከሆነ ሰልካካ ነው —አራት ነጥብ። አየር መጥኖ ለማስገባት ወይም መጥፎውን ሽታ ከጥሩው ለመለየት ከሌሎች የተሻለ ዕድል የለውም።

ያም ሆነ ይህ ውበትን ፍጹም አድርጐ ከራስ ፀጉር እስከእግር ጥፍር ድረስ በድርሰት ማድነቅ ለምን ያስፈልጋል? ተፈጥሮ ከክፉውም ከበጐውም ነው ያደለችን። ከሁሉም ቀያይጣ ነው የምትሰጠን። የአጭር ደመ-ግቡ፣ የፉንጋ ድምፀ መልካም፣ የመላጣ ዓይናማ፣ የቀውላላ ሰልካካ አለ። የአንካሳ ቄንጠኛ፣ የገጣጣ ፍልቅልቅና ጨዋተኛም ሞልቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ምን የመሰለውን ቁንጅና አንድ የተረገመ አስቀያሚ ድምፅ እንዳልነበረ አርጐ ሲያበላሸው ዓይን ያደነቀውን ጆሮ ይሸረዋል። አንዳንዴ ደሞ በአድናቆት እሚያፈዝ ውበት በአንድ ለዛ-ቢስ ደረቅ ፈገግታ እዛው በዛው ልውጥ ብሎ ተራ መልክ ይሆናል። በርግጥም ተፈጥሮ

ለሁላችንም ድርሻ፣ ድርሻችንን የምትሰጥበት የራሷ ድንቅ መንገድ አላት። አሁን ለምሳሌ መጣጣና ወዝ - የለሽ ፀዳል በሰልካካነት ላይ የሚያስጠላውን ያህል ድንቡሽቡሽ ያለ የደስ ደስ ላህይ በቦርጭ ላይ የሚያምርበት ሁኔታ አለ። የባለጌ ዓይነት ቅጥየለሽ አቋቋምና አካሄድ ተክለመልካምነትን የሚያበላሸውን ያህል፣ ኩሩነት ያጀበው ለግላጋ አወጣጥና ተፈጥሮአዊ አኳኋን ድርቅ ያለውን ቅጥነት እያደመቀ የሚያጅብበት ጊዜም አለ።

ስለዚህ አንድ ውብ ገፀ ባሕርይ ለመፍጠር የግድ እዚህ-ቀረሽ የማይባል፣ የተሟላ ቁንጅና ሲገልጹ መዋል አያሻም። የተሟላ ቁንጅና የለም፣ ወይም የተሟላ ቁንጅና ቢቀረጽ አንባቢ ይከፋል ለማለት አይደለም። አለቅጥ ሲበዛና ገለጻው ራሱ ፋታ አልሰጥ ሲል፣ ሲበዛ ማር ይመራል ዓይነት ያሠለቻል ለማለት ነው። ፍጹም አድርጐ ማቅረብም እኮ ሳይቸግር ከማሰሮ ንፍሮ ውስጥ አንድ ጥሬ ባቄላ ሲፈልጉ መዋል ነው! ደግሞም ቁንጅናን ለማሳየት የዳዊትን በገናና የእዝራን መሰንቆ፣ የያሬድን ጥዑመ ዜማ አጃቢ ማድረግ ሁልጊዜ አይጠበቅም። ሌላ ብዙ የክየና ዘዴ ይኖራል።

በጥሩ ምልልስ፣ በአጫጭር ገለጻዎች፣ በምልሰት፣ በተለያዩ ትዕይንቶች ባንዴ ሳይሆን በጣልቃ ጣልቃ እያደረጉ፣ እንደዱብ ዕዳም ሳይሆን ቀስ በቀስ እያስናፈቁ፣ እየገነቡ ማቅረብ ይቻላል። በአኳኋን ማሳየትም ሌላው ዘዴ ሊሆን ይችላል። በአረማመድ፣ በአመለካከት፣ በአሳሳቅ፣ በአነጋገር፣

በተመስጦ፣ በቁጣ፣ በገዘምታ ወዘተ። በነዚህና በሌሎችም ብዙ ዘዴዎች ሚዛናዊ በሆነ አቀራረብ በታሪኩ ውስጥ እንደጌጥ እያፈናጠቁ በቀላሉ ማሳመን እንጂ በጥሩ ቋንቋ ሁሉን ነገር አጋነው ቢያንዠቀዥቁት የግሪኮችን አማልክት የሐውልት ቅርፅ ወረቀት ላይ መፍጠር ይሆናል።

ወደይዘታቸው ጠለቅ ብለን ስንገባ አብዛኞቹ ቤሳ ልቦለዶች የሃይማኖት ተፅዕኖ አለባቸው። አንዳንዶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሕግጋት፣ የአዳምና የሔዋንን አመፀኛነት፣ የጸም የጸሎትን ጠቃሚነት፣ ምንኩስናና ብሕትውናን መነሻ በማድረግ ግብረገብ የማስተማር ብርቱ ሙከራ ያደርጋሉ። ጥቂት ገፀ ባሕርያት ፈጥረው እንዲህ ያለ ቦታ ተወለዱ ብለው ይጀምሩና ለታሪኩ ጉዞ እምብዛም ሳይጨነቁ ወደዋናው ዓላማቸው ወደ ስነ ምግባርና ሞራል ስብከት ያዘግማሉ። በየምዕራፉም ባይሆን አልፎ አልፎ፣ በግልጽ፣ «ሰው ሆይ! ልባርግ፣ አፈር መሆንህን አትርሳ... እነሆ የመጥፎ ምግባር ውጤቱ በዚህ ታሪክ በገሀድ ታይቷል...» የሚሉበትም ጊዜ አይጠፋም። ዝርዝሩ ብዙ ነው። መቼም ምሳሌ ቢበዛ በትችት አይጫንም እንጂ ከዐስርቱ ቃላት አምስቱን ዋና ዋና ናቸው ብሎ እያብራራ የኃጢአትን ምስል ለማሳየት የሞከረ ጽሑፍ አለ።

አንዳንዶቹ የሃይማኖቱን ጉዳይ ከታምር ጋር አያይዘው ወይም ታምርን ሽፋን አድርገው ያመጡታል። ከሰዎች ለየት የሚያደርግ አፈጣጠርና ቋንቋ ያለውና ከልዩ

ምልክት ጋር የሚወለድ ገፀ ባሕርይ በታሪኩ ሂደት የማሸነፍ ዕድሉ ከፍ ያለ ይሆናል። ከስድስት ከሰባት ተወላጆች መሀል ለዘር የተረፈ፣ ለእናት ለአባቱ አንድ የሆነ «ጐበዝ»፣ እንደጣሊያንኛው ፊልም «ሚቺስቴ» እሳት በተለኮሰ ችቦ ሶስት ደርዘን ባላጋራ እያባረረ ባይረፈርፍም፣ በዛም በዚህ ብሎ በተቃዋሚዎቹ ላይ እንዳየለ ይዘልቃል። ታዲያ እንዲህ የሚሆነው መጀመሪያ ላንድ ታቦት የሰለት ልጅነት ከተሰጠ በኋላ ነው። ወይም በጠበል ጸዲቅና ዕዋ ማግስት «የበቃ የነቃ ወንድ ልጅ ትወልዳላችሁ» የሚል ተስፋ ለወላጆቹ በራእይ ከተገለጸላቸው በኋላ ነው።

እነዚህን ጽሑፎች ከልቦለድነት የሚያርቃቸው አንዱ ችግር እነዚህ ሁሉ ተደማምረው የሚያመጡትን በተአምርና ትንግርት በጥሩ አድናቆት የሚያስተናግዱ መሆናቸው ነው። በዚህ ላይ ሐሳባዊነቱ ሲታከልበት፣ ፍፁም የሆነ ገፀ ባሕርይ ፍፁም ድርጊት አርግዞ ይወለድና ታሪኩ መጥፎ ጠንቋይ የባረከው የኪነት ቁራጭ ይሆናል።

በትንግርት (ተአምር) የተለከፉ ጽሑፎች ለነገሮች ምክንያታዊ ግንኙነት አይፈልጉም። ምክንያቱም ውጤቱም ተአምሩ ራሱ ይሆን ላቸዋል። የመንግስተ ሰማያቱም፣ የሲኦሉም መንገድ እሱ ብቻ ሆኖ ይታያቸዋል። ስለዚህ የነገሮችን ጠቅላላ መልክ ወስደው ወይ በጣም አጋነው ያደንቃሉ፤ አለዚያም አክቸልችለው ያወግዛሉ። ለምሳሌ ስነ

ምግባርን፣ ፍቅርን እንደምሳሌ ብንወስድ ከዚህ ትንሽ፣ ከዚያ ትንሽ የሚል አማካይ አስተሳሰብ ሳይፈነጥቁበት፣ በነሲብ «አለ» ወይም «የለም» እንደሚል ተወራራጅ፣ ጥሩ ወይም መጥፎ ብለው በአንዱ መስመር ጭው ብለው ይሄዳሉ። ትፀድቃለህ ወይም ትኮነናለህ እንደሚለው ያለ ነው።

ስነ ምግባሩ በቅዱስነት ከተጀመረ ዘላለም ቅዱስ ሆኖ ያልቃል። አንድ ቀን እንኳ በስሕተት ከተለመደው አይዛነፍም። ገፀ ባሕርዩ እጅ መንሳት የማያስተጓጉል ትሑት ከሆነ በእንቅልፍ ልቡም እጅ ይነሳል። የሙት ልጆችን የሚያሳድግ ደግ ከሆነ የሙት ልጅ ከማሳደግ ሌላ የደግነት ስራ እሚኖር አይመስለውም። ምጽዋት መስጠት ተግባሩ ነው ከተባለ ሊሞት ሲያጣጥርም በመናዘዝ ፋንታ ተነስቼ ምጽዋት ካልሰጠሁ ይላል።

የፍቅር ጉዳይም ምድራዊ አይደለም። በፍፁምነት ደመና ተንጠልጥሎ የሚኖር የጥቃቅን ድርሰቶች ሁሉ ተወዳጅ ጌጣጌጥ ነው። ፍቅር ሲያሰኘው እዛው በሩቅ እንደተንጠለጠለ የፀሐይዋን ሙቀት እየከለለ ያሾፋል። ምስኪኖችን ገፀ ባሕርያት መብላት መጠጣት እየከለከለ እንደመናኛ ጨርቅ ኪስ ይጫወትባቸዋል። በቁርና በበረዶ አዘቅት ወድቀው ሲያቃስቱ ይቆዩና ሶስቱ ፊደል፣ ሶስት ሺ እየሆነ ለእብደት ይዳርጋቸዋል። እሱን ካላገኙ አማራጩ ሞቶ አንድ ላይ መቀበር ብቻ ነው።

የቤሳ ልቦለድ ፍቅር ሲያሰኘው አሁንም በደመናው እንደታዘለ በመልአክ ተመስሎ ገፀ ባህርያቱን በሕልም ብቻ እሚያነጋግርና ስለዓለም አፈጣጠር፣ ስለእንስሶች፣ ስለዕፅዋት፣ ስለትዳር ሁሉ እሚያመራምር ቅዱስ አካል ይሆናል። አንዳንዱ ርኅሩህ ሲሆን፣ በጉዞ ላይ (ለምሳሌ በአውቶቡስ) አዋዶ እዛው አለማምዶ ስለአረንጓዴ መስክና እምቦሳዎች ተመሳሳይ የሆነ ቀና አስተያየት እንዲለዋወጡ ያደርጋል። ሰይጣኑ ከመጣበት ግን እዛው አነጫንጮ ያለምክንያት አበሳጭቶ መንገድ ሊያስወርዳቸው ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ መልካም ውጤት ሲያስገኝ የሚታየው በእናታቸው ሆድ ተጫጭተው፣ በራእይ ታይተው፣ አንድ ላይ ተምረው ደብዳቤ እየተለዋወጡ በሚያድጉ ጐረቤታሞች በሆኑ ወጣቶች ላይ ነው።

የቤሳ ጽሑፎች ለተጨባጭ ነገሮች ቅድሚያ አይሰጡም። ገፀ ባሕርያቱ በዕድልና አጋጣሚ ውጣ ውረድ በሌለው ቀጥተኛ መስመር እንደዳማ ጠጠር የሚገፉ ናቸው። ቅያሱ ከመጀመሪያው የታወቀ ስለሚሆን በግድ እየተገፈተሩ ዕድላቸውን ከመጠበቅ ሌላ አማራጭ አይኖራቸውም። አማራጭ አገኙ እንኳን ቢባል ዞረው ዞረው በማይመስል የዱብ ዕዳ መድረክ ላይ ማረፋቸው አይቀርም። ለዚህም ምናልባት በአንዳንድ የሃይማኖት መጻሕፍት የሚታየው ሚስጥራዊ ባሕርይ ተፅዕኖ እያሳደረ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ዱብ ዕዳ በኪነ ጥበባዊ ቅርጽ ታሽቶ ሳይሰላ ሌጣውን እንዲሁ ቋንቋ ውስጥ ከተደነቀረ ዋጋ-የለሽ ምስጢር ይሆናል። ለማናቸውም

ምስጢር በምስጢርነቱ የሚሰምረው ታሪኩ ልብ እየሰቀለ ሲያጓጓ ነው እንጂ ገና ከመጀመሪያው፣ አንዱን መርጦ መጻፍ የሚያስፈልግ ይመስል፣ የወደዱትንና የጠሉትን ገፀ ባሕርይ መልአክና ሰይጣን በማስመሰል አይደለም።

ተአምርና ትንግርት የሚያዘወትሩ ድርሰቶች ምንግዜም ቢሆን ለሚቀርጹት ጉዳይ፣ ከቁሳዊው ዓለም ውጭ ምክንያትና ውጤት ይፈልጋሉ። ለታላቅ ተግባርና ሙያ ሰማያዊ ፀጋና ክብር መሰረት ያደርጉለታል። መፍጨርጨርን፣ ታግሎ ማሸነፍን፣ ለሀብትና ዝና መብቃትን የስራና የጥረት ውጤት አድርገው የሚያሳዩበት አጋጣሚ ጥቂት ነው። ሁሉ ነገር በደፈናው ታምር እንደሆነ ዘንቦ በተአምርነት ያባራል።

ለምሳሌ የምታነቡት ታሪክ ከቤቷ ኮብልላ ጫካ ለጫካ በግጥም ስለምታንጐራጉር ወጣት ከሆነ፣ መሸቶባት ተጨንቃ ከዛፍ ዛፍ እያማ ረጠች ሌሊቱን ለማሳለፍ ስትዘጋጅ፣ «አንድ ድምፅ ወደሷ ተቃረበ» የሚል ዓረፍተ ነገር ላይ ዐይናችሁ ቢያርፍ፣ አንዳች ታምር ሊከሰት መሆኑን ባንዴ ማወቅ አለባችሁ። ለአምላኩ ፀሎት በማድረግ ላይ ያለ ትልቅ ጉሬዛ ካንዱ ረጅም ጥድ ላይ ዘሎ ወርዶ በጐርናና ድምፅ «አይዞሽ አትፍሪ፣ አንቺን ለመጠበቅ ተልኬ መጥቻለሁ» ሊላት ይችላል። በአዕዋፍ ላይ ያልታየ ቀለም ያላት አሞራም ሰምታ በማታውቀው ቋንቋ የጫካውን ምስጢር እየተነተነች ልታስረዳት ትችላለች። እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

ይህን የመሰለው አስገራሚ ትዕይንት በኑሮ ውጣ ውረድም ላይ የማይኖር እንዳይመስላችሁ። ጨካኝ የሆነው ገፀ ባሕርይ ያለ ምክንያት ሲጨክን፣ ገንዘብ መሬት ወድቆ ያገኘው ለማግኘቱ ምክንያት ሲፈለግለት ታያላችሁ። ጐበዙ አነስተኛውን ተግባር ማከናወን ሲያቅተው፣ ደካማው ድንገት ኃይል አግኝቶ ሁኔታዎችን ሲለውጥ ትታዘባላችሁ። በእንጀራ እናቱ ክፋት ተሰቃይቶ ወደአንድ ደሴት የተሰደደ ገፀ ባሕርይ፣ አራዊቱ ሳይነኩት ብዙ ዓመት ቆይቶ፣ ባለፀጋ ሆኖ ወደትውልድ መንደሩ ሲመለስና የፈረሰውን የአባቱን ቤት ንብረት ለማቋቋም ቆርጦ ሲነሣ የሚተርክ ጽሑፍ ቢያጋጥ ማችሁ መደምደሚያውን ሳታነቡ ማቋረጥ የለባችሁም። ምክንያቱም በዚያም ብሎ በዚህ በጨረቃ ምሽት ጋቢውን ለብሶ እደጃፉ ቁጭ እንዳለ ከአንድ ባሕታዊ ጋር ስለሰላምና ጦርነት ወይም ስለሳይንስ በጥያቄና መልስ መወያየቱ አይቀርም።

በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ በጽልመ ታዊ አመለካከት የሚንሩ ጽሑፎች አሉ። ስለዘመድ፣ ጓደኛ፣ ገንዘብ፣ ፍቅር፣ ዕድል፣ ክፉውን ወገን ብቻ መርጠው አጠንክረው ያያሉ። ለሰው ማህበራዊ እንስሳነት ቦታ አይሰጡትም። ወይ ጥሩ ወይ መጥፎ ሆኖ መፈጠር አለበት። እንደጣት የሚበላለጠው በመለኮታዊ ትእዛዝ ነው። ሆኖም ተበላለጠም አልተበላለጠም፣ ሁሉም ነገር ከንቱ ነው — ፍጻሜው አያምርም። የሰው መጀመሪያውም መጨረሻውም

በጨለማ ተውጦ የሚቀር ትርኪ ምርኪ ህልውና ነው የሚል አስፈሪ ነጋሪት ይጐሰምባቸዋል።

በአንዳንዶቹ ጽሑፎች ሳይንስ ሰውን ለማጥፋት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ደግ ዓላማ የለውም። «ታሪክም ፍልስፍናም ከሰማይ በታች አዲስ ነገር የለም» በሚለው የሰለሞን ጥቅስ ስር ተጠቃለው የሚገኙና አድናቆትም ሆነ ትኩረት የማይገባቸው ናቸው። በአንዳንዶቹ ድርሰቶች ደግሞ ለይዘቱ የሚሰጠው ድርሻ የሚናቅም ባይሆን፣ ከሕይወት ጨፍጋጋነትና መላ ቢስነት ጋር ሲነጻጸር ተገቢ አፅንኦት አይደረግለትም።

ሕይወትንና ተፈጥሮን፣ የሰዎችን የመግባባት ግንኙነት ሁሉ በተንኮልና በኃጢአት አቅጣጫ እየተመለከቱ ጽልመታዊ ግንዛቤ ማንፀባረቅ የአብዛኛዎቹ ባሕርይ ነው። መዋደዱ በመከዳዳት ያከትማል። አብሮ-አደግነቱ በምቀኝነት ይበከላል። ስራ ፍለጋ በአጋርና በጉቦ ሲቀጭ፣ በሽታውና እርዛቱ ይከተላል። ተስፋ አተላ ሆኖ ሲበጠበጥ ምኞት ከጭጋግ ጋር በኖ ይጠፋል። ዓለም የእዬዬ መድረክ ትሆናለች። የታሪኩም አቀንቃኝ በተጻፈለት የአርባ ቀን ዕጣው፣ መራራ ፅዋውን እንደተሸከመ፣ በሐሳብ ነጐድጓድ እየተውዘገዘገ፣ በችግር ፍዳ እየተደፈጠጠና በማጣት ሳማ እየተለበለበ በስቃይ ምድረ በዳ በሠቀቀን ይንከላወሳል።

በነዚህ ጽሑፎች በመልካም ስነ ምግባር ከታነፀ መንፈሳዊ ቤተሰብ የሚወለድም ገፀ ባሕርይ የሚያነግተውን ዳዊትና ድርሳን አንዴ እንኳን ገልጦ ሳያነብ በአእምሮው የሚደቀኑበትን ምርጥ አስተያየቶች እያብላላ ምድርን ከነፍጥረቶቿ ይራገማል። አቀንቃኙ ብዙውን ጊዜ የሕይወትን ጤዛነት የሚሰብክ ይሆናል። የሚታገልለት «እውነት» የዛች ልብወለድ ብቻ ሆኖ መቀንጨቡ ያስቆጫል እንጂ በእንደዚህ ዓይነቱ አቀራረብ የክርክር ችግር አይኖርም። ክርክሩ ማሠልቸት ከጀመረም፣ ከየት መጣ ሳይባል፣ አንድ የተራበ አንበሳ ወዲያው ፈጥሮ በሆነ ቦታና ጊዜ ገፀ ባሕርዩን መገላገል ነው።

ብዙ ሐያሲያን እንደሚጠቁሙት፣ ሚዛናዊ የሆነ የ«ጊዜ» አጠቃቀም ለልብወለድ አጻጻፍ የግድ አስፈላጊ ነው። ይህም ትረካውን በጥሩ አቀራረብ ተሟልቶ እንዲሳካ የሚያደርገው ስለሆነ ገና ልብወለዱ ሲተለምና መዋቅር ሲወጣለት ሊታሰብበት ይገባል። ታሪኩ ከተጀመረም በኋላ ቢሆን ባልተዘናጋ ጥንቃቄ እየታቀደ ሊከወን ይችላል። የ«ጊዜ»ን ሚዛን ለመጠበቅ ከቋንቋው አንሥቶ እስከ ታሪኩ ውጣ-ውረድ ድረስ ተደጋጋፊ የሆኑ ብዙ ነገሮችን እንደ ጠባያቸው መያዝ፣ የሚስተካከለውን ማስተካከል፣ የይዘቱ ልዩ ልዩ ዘርፎች አንድ የጭብጥ ዋና አቅጣጫ እንዲይዙ ማድረግና ለልብወለዱ ተገቢውን ምልክት መስጠት ያስፈልጋል።

ለዚህም ዋንኞቹ የቴክኒክ ገፅታዎች፣ ማለትም የጠቅላላው ታሪክ ድርጊት፣ ስፍራውና ወቅቱ (መቼት) የሚባለው፣ የጠቅላላው ድርጊት አንጓዎች (ኤፒሶድስ)፣ ገፀባሕርያቱ፣ ትእይንቱ፣ ገለጻውና ምልሰቱ፣ ምልልሱ፣ ቅርጹ በሚፈቅደው መጠን በይዘቱ ስፋትና ጥልቀት መሰረት መመጠን አለባቸው።

ከነዚህ አንድ ሁለቱን ጠቅሶ ለማለፍ በድርጊት ፈጠራው በኩል የሚዘረዘረው ይዘረዘራል። በጠቅላላው መልኩ የሚቀርበው እንደዚያው ሆኖ ይቀርባል። ባጭሩ ተጠቅሶ የሚታለፈውም ጣእሙና ቃናው ሳይቀንስ ተጨምቆ ይቀናበራል። በገፀ ባሕርያት አሳሳሉም ረገድ አካላዊና ውስጣዊ ገለፃ የሚያሻውና በየትእይንቱ መምጣቱ ለትረካው ጠቃሚ የሆነው፣ እስከመደምደሚያው ቢዘልቅ የሚበጀውና መንገድ ቢቀር የማይጐዳው ገፀባሕርይ በጊዜ ሚዛን ላይ እኩል አይቀመጡም። ለአቀንቃኙ (ዋናው ባለታሪክ) አጋዥ የሆኑትና ራሳቸውን ችለው በሌላ አቅጣጫ የሚሄዱትም በየበኩላቸው ተመጣጣኝ ድርሻ ይሰጣቸዋል። በዚህ አኳኋን ደረጃውና መጠኑ እየተስተዋለ፣ ሳይትረፈረፍና ሳይቀነስ፣ የትረካው «ጊዜ» በተፈላጊው ቦታና አቅጣጫ ሊከፋፈል ይገባል።

በቤሳ ልቦለዶች አቀራረብ ላይ «ጊዜ» በቂ ትኩረት አይሰጠ ውም። ባመዛኙ እንደሚታየው የ«ጊዜ» አመዳደብ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው። በችኩል ምናብ ውስጥ ከተፍ ያለ ገፀ

ባሕርይ «ሎተሪ»ውን ይወስደዋል። ስለዚህም ገለጻና የድርጊት ውጣ ውረድ በመከታተል ይቀየስለታል። ቢያንስ ቢያንስ ንዑስ አቀንቃኝነት የሚገባው ግን፣ ከድርጊቱ መስክ ካልቆየሁ እያለ ሲወተውት በቅምሻ ይመለሳል። መቼም ከሎተሪው «ማስተዛዘኛው» እንደምንም ይደርሰዋል። ይሁን እንጂ እንቅስቃሴውን ለማሳየት ዕድል ሳይገጥመው እግሩን ተሰብሮ በቃሬዛ እንደሚወጣ ጥሩ ኪስ ተጫዋች አንባቢ የሚያዝንለት ገፀ ባሕርይ መሆኑ የማይቀር ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ «ጊዜ» ሲባል ለአንዳንዶቹ ምንም ትርጉም ላይኖረው ይችላል። ትርጉም አለው ቢባልም ድርሰቱ የተጀመረበትንና የሚያልቅበትን ወርና ቀን፣ ዓመተ ምሕረቱን በሚመለከት ሳይሆን የሚቀር አይመስለኝም። ታሪኩ ተጀምሮ ካለቀ፣ አንዳች ፍጻሜ ላይ ከደረሰ፣ ትልቁ ነገር እንደተከናወነ ይቆጠራል። በይዘቱ ውስጥ በነሲብ ተፈልጎ ወይም ለደራሲው ለራሱ ደስ ያለው ገፀ ባሕርይ ተመርጦ የትረካው ፈላጭ ቆራጭ የሚደረግበትም ጊዜ አለ።

በአብዛኞቹ ቤሳ ልቦለዶች የሚታየው ድክመት ለአቀንቃኙ ገደብ የሌለው ድርሻ ከመስጠት የሚመነጭ የስነ ጽሑፍ ብኩንነት ነው። ገለጻው ሁሉ ለሱ አፍንጫና ጥርስ፣ ቁመት፣ አነጋገር፣ አካሄድ ይውላል። ዳግመኛ ጠይም፣ ቆንጆ፣ ጉበዝ (ኃይለኛ) በድርሰቱ ውስጥ አይኖርም። በአእምሮ ደረጃም እንደአቀንቃኙ የሚያስብና የሚመራመር የለም። የሚፈጠርለት ደጀን ያደገበት፣ የተማረበት፣ የዋኘበት፣ ከብት የጠበቀበት ሁሉ

በአሸብራቂ ቋንቋ ይኳኳላል። እናት አባትን አልፎ አያት፣ አክስት፣ ወንድም፣ አበልጅ፣ ጓደኛ ይዘረዘርለታል። ሌሎቹ ገፀ ባሕርያት ግን ብቻቸውን እንደተፈጠሩ ሁሉ ማንነታቸው ሳይታወቅ በቁንጽል ትረካ ይውተረተራሉ። ሞትም ከሞቱ ባለቤቱ እንደጣለው ጌኛ በቆሙበት ሳያንቀላፉ አይሞቱም። ሁሉም ነገር የአቀንቃኙ ነው። መሬቱ፣ ምግቡ፣ ዕቃው፣ ሙክቱ፣ ዶሮው፣ ድመቱ፣ አብረውት ይነሳሉ። ሌላው ቀርቶ ካልጠፉ የሰፈር ውሾች የሱ ብቻ ተመርጣ ትረካው ውስጥ ብትዞር አያስገርምም።

በድርጊቱም ላይ አቀንቃኙ የትም ይገኛል። ጉዳዮች ሁሉ ከዚያው አንፃር ተወርውረው በተግባር ካልዋሉ ጉዳዮች አይደሉም። በመልካም ምግባር፣ በአርበኝነት ወኔና በሃይማኖት ጽኑነት ከዚያ ክልል ውጭ አይኖርም። ለማጎበሩ ማጎበርተኛ፣ ለክርክሩ ተከራካሪ፣ ለጠቡ አስታራቂ መካሪ፣ ለሰርጉ አድማቂ፣ ለጉዞው ተሳፋሪ አቀንቃኙ ብቻ ነው። ሃብትና ድኅነት፣ ስቃይና ደስታ፣ ሐዘንና ተስፋ፣ ምኞት፣ ስሜት፣ ፀፀት፣ ናፍቆት በተለይም ጋብቻና ፍቅር በሌሎች ገፀ ባሕርያት ላይ አያንጣብቡም። ሞንቀቱን እሱ ብቻ ይጨነቃል። ሙዚቃውን እሱ ብቻ ያዳምጣል። ሕልሙን ሳይቀር እሱ ብቻ ያልማል። ፍቺውንም ራሱ ይናገራል። ባጭሩ የልብወለዱ ብቸኛ ባለቤት ነው።

እስካሁን በተመለከትናቸው ዓበይት ምክንያቶች እነዚህ ጽሑፎች የትረካ ሚዛናቸው ይታወሳል። አንዱ ከሚገባው

በላይ ይጮላና የሌላውን ትኩረት ይሰርቃል። በዚያው አንጻር ሌላኛው አስፈላጊውን አፅንኦት ይነፈግና በኮሳሳ መልኩ ይንፀባረቃል። በተለይም ገፀ ባሕርያትና ድርጊት አንዱ ላንደኛው መኖር ምክንያት እንደመሆናቸው መጠን፣ ከጭብጡ ጋር የተመጣጠነ ሂደት ካልታቀደላቸው የልብወለዱ ሁለንተናዊ እድገት እንደሚፋለስ የታወቀ ነው። የትረካው አቅጣጫ ደብዛዛ ይሆናል። ተጨባጭ ነገሮች እየራቁ ይሄዳሉ። የሚገናዘቡ ሐሳቦች ይዘበራረቃሉ። የአቀራረቡ ሁኔታም ጣእም ስለማይለግስና ይዘቱን የሚያራምድ በቂ ኃይል ስለማይኖረው፣ ጠቀሜታ ሊኖራቸው የሚችሉ ጉዳዮች ተድበስብሰው ይታለፋሉ። ጉጉትና ስሜት የሚፈጥረው ኪነታዊ እሳት ገና ቦግ ማለት ሳይጀምር አንባቢውን በጨለማ ጥሎት ይጠፋል።

ሆኖም ለጊዜ ምደባ በጥቂቱም ቢሆን እድል አይኖርም ማለት አይቻልም። አንዳንዶቹ በእውነተኛ ታሪክ ላይ የሚመሰረቱ በመሆናቸው ራሳቸውን በራሳቸው የመመጠን (የትረካውን ጊዜ የማደላደል) አጋጣሚ ይኖራቸዋል። የተቀሩት፣ የሁለት ፍቅረኞችን ታሪክ በሚተርኩበት ወቅት ከኒያ ክልል እምብዛም ስለማይወጡ በሌላ ሌላው ላይ ጊዜ ከማባከን ይቆጠባሉ። አሁንስ ቢሆን፣ ልብወለዱ የሁለት ፍቅረኞች ከሆነ ማን ጣልቃ ሊገባ ኖሯል? አቀንቃኞቹ እነሱው ይሆናሉ። ጊዜውም ሳይወድ በግዱ ለነሱው ይመደባል።

ስለፈጠራ «ጊዜ» ስናስብ፣ «የትኛው ይነሣ፣ የትኛው ይቅር» የሚል ጥያቄ ምንጊዜም እንደሚኖርና በሚዛናዊ ሂደት መከወን እንዳለበት እናውቃለን። ታዲያ የስነ ጽሑፍ ጠበብት ለዚህ የሚመክሩት የጽሑፉን ዓላማዎች (በጭብጡም፣ በትረካውም ማለት ነው) የሚያዳብሩትን ጉዳዮች ከነአቀራረባቸው በጥንቃቄ መምረጥ የግድ አስፈላጊ መሆኑን ነው።

በመሰረቱ አንድ ደራሲ የሚያቀርበውን ዐብይ ጉዳይ ማወቅ አለበት። ዐብይ ጉዳዩን የሚያጐሉለትንም ቅርንጫፎች በደንብ ካሰበባቸው ለይቶ ማወቅ አይቸግረውም። ከዚያ ወዲያ የሚቀረው ያንን ደህና አድርጐ ማጤን ነው። ይሄንን መናገሩ ለገፀ ባሕርይው ምን ጠቀሜታ አለው? ድርጊቱን ያጐላዋል? እንዳይረሳ ያደርገዋል? ለጭብጡስ ምን አስተዋጽኦ ይኖረዋል? ይሄንን ብተወው ምን ሊያጐድል ይችላል? ገፀ ባሕርይው በቅጡ የማይታይ ይሆናል? የጭብጡስ መሟላት ይታወካል? እያሉ ከራስ ጋር መወያየት ችግሩን ያቃልለዋል። ዋናው ነገር በተገቢው ቦታና ወቅት የትረካ አቅጣጫ አዳባሪ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ማተኮር ያሻል። ላውራ ከተባለ የሕይወት ገጽታው ብዙ ነውና።

አናጢ ለሚሰራው የዕቃ ዓይነት እንጨቶችን ገምቶ መትሮ ይቆርጣል፣ ይሞርዳል። አንዱን ከሌላው ጋር ያያይዛል፣ ያለሰልሳል፣ ቅርጽ ያወጣል፣ ቀለም ይቀባል፣ ያስጌጣል። ከዚያ በፊት ግን ከተለያዩ ብዙ እንጨቶች መካከል

ለዚያ ስራ የሚስማማውን የእንጨት ዓይነት ይመርጣል። ይሄም እንዲሁ ነው።

ድርጊት በፈጠራ ጽሑፍ ትልቅ ድርሻ እንዳለው አይታበልም። ይሁን እንጂ ባጭሩ ተጠቅሶ ሊታለፍ የሚችለውን ሲዘረዝሩ መዋል ትረካውን መጉዳት ነው። ለምሳሌ አቀንቃኙ ጠላቱን የሚያሸንፍበት ሰዓት ሲቃረብ፣ አንባቢው ስሜትና ጉጉቱን፣ እልሁን፣ ውስጣዊ ትግሉን (የአቀንቃኙን)፣ ለማወቅና ለመስማት ሲቸኩል፣ ውጤቱ ላይ እስኪደርስ ጥሩ የትረካ ፍሰት ለማጣጣም ሲጠባበቅ መንገድ ላይ ቆም እያለ ሰባራ ስንጥሩን ጥቃቅን ጉዳይ ላሳይ የሚል ልብወለድ በፈጠራ ጊዜ ከመጫወት በስተቀር የሚፈይደው ቁም ነገር አይኖርም። አቀራረቡ በጣም ጥሩ ቢሆንም እንኳ፣ የሚፈለገውን አዘግይቷልና ለአንባቢው ደስታ አይለ ግስም። አሁንስ ቢሆን ስሜት የሚጠናከር ደረጃ ላይ ደርሶ፣ 'ካሁን አሁን ምን ሊመጣ ነው' ሲያሰኝ አቀንቃኙ በየሆቴሉ፣ በየአልቤርጐው፣ በአውቶብሱ ከየመንገደኛው ጋር ሲነጋገር፣ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲከራከር፣ ሲደ ባደብ የሚያትት ጽሑፍ ምን ደስታ ይሰጣል? ባጭሩ ነካ ነካ አድርጐ ጨምቆት ሊያልፍ ሲችል ምን አዘረዘረው?

የሚገርመው ግን ከትናንሽ ሁነቶች (ኤፒሶድስ) ዓቅም እንኳ አላግባብ የሚዘረዘሩ ጽሑፎች አሉ። ሰውዬው ስራ ሊገባ ፈተና ይፈተናል። ማለፍ ያልፋል፤ ስራውንም ይይዛል።

የፈተናው ሁኔታ ዓይነቱ፣ ሰዓቱ፣ ጥያቄው፣ መልሱ፣ ማርኩ ምን ያደርጋል? ልጅቷ ፍቅረኛዋ ትዝ ብሏት ታለቅሳለች። መቼም ያወረደቻቸው አሳዛኝ የእንባ ዘለላዎች ተቆጥረው ሊጻፉ አይችሉም። ግን ስለመሐረቡ መራስ፣ እንባ አጠራረጓ፣ የዐይኗ መቅላት፣ ራስ ምታቱ፣ ጉንፋኑ ሶስት ገጽ ሙሉ ማውራት ምን ያስፈልጋል? ሁለት ጓደኛሞች ቡና ቤት ገቡ። ሁለቱም ሻይ አዘዙ። እየጠጡ ተጫወቱ። ታዲያ በጭውውታቸው መሀል ስለስኒው ጆሮዋማ መሆን፣ ስለሻዩ መብረድ መቀዝቀዝ፣ ስለ ስኳሩ መብዛት ማነስ፣ ሁለት ሶስት አንቀፅ መጻፍ ምን ይጠቅማል? ሻዩን ስላመጣችው ልጅ የጧት ሻሽ አስተሳሰርና የዞረ ድምር ነጭናጫነት፣ እያንጐራጐረች ውጭ ውጭውን መመልከት፣ የነገውን ዕቁብ እያሰበች ቢራ መክፈቻውን በሲጃራ መተርከሻ ፋንታ ማቅረቧ ትንሽ ጠቅሶ የቡና ቤት ትግርምት ጫር ቢደረግ እንኳን አይከፋ ይሆናል። ስለሻይ ማንኪያው ጠማማነት መናገሩ ግን ሩብ መስመር ያህልስ ቢሆን ምን ይሰራል? የቡና ቤቱስ ባለቤት «ኮስታራ አስተያየት» ምን ይፈይዳል? ሁለቱን ጓደኞች አርፈው ከሚጠጡበት «ውጡ!» ብለው ካላስነሱ በስተቀር!

እንዲያውም እኮ የአንዳንዱ የልብወለድ ድርጊትም ሆነ ትርክት እስከናካቴው ከቀለም ጠብታ ላያልፍ ይችላል። ሀብታም የተባሉትን ነጋዴ ቢያስፈልግ ሀብታቸውን ጠቅሶ ማለፍ እንጂ የገንዘብ ማስቀመጥ ዕቅዳቸው (ሌሊት ሌሊት)፣ ወደባንክ ቤት አካሄዳቸው (ጧት ጧት)፣ የብር አቆጣጠር

ዘዴያቸው (ለእሱም ዘዴ ካለ)፣ የማስቀመጫው ዓይነት፣ ጥንካሬው መወራቱ ምን ይጠቅማል? ወጣቱ በትረካው ውስጥ በምልሰት የገጠር ልጅ ሆኖ አባቱን በእረኝነቱ ሲያገለግል ብሎ ለመዘርዘር ምልሰቱን የሚጋብዝ በቂ ምክንያት እንዲኖር ያስፈልጋል። አለበለዚያ አለማንሳት ነው። ያኔ እረኛ የነበረ ጊዜ ያጋጠመው አንዳች ችግር ካለ፣ ለምሳሌ በሬ ጠፍቶበት የማይረሳው ቅጣት ደርሶበት እንደሆነ፣ በጉን ሌቦች አርደው ሲከፋፈሉ ደርሶ በአስደናቂ ዘዴ ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ጮሆ በማስፈራራት አስጥሎ እንደሆነ (ከዚያ ስጋውን እንዴት ቤት እንደሚወስደው እንጃ!)፣ ወይም ፍየልና ፍየል እየቀለደ ሲያደባድብ በሁለቱ መሀል ድንገት የገባ አልፎ ሂያጅ ውሻ ደንግጦ ቁርጭምጭሚቱን ነክሶት እንደሆነ ካሁኑ ሁኔታ ጋር በተዛመደ መልክ ሊወራ ይችላል። ታዲያ የሚዛመድበት ጥሩው አጋጣሚ ጫማውን ሲያወልቅ ነው። በትዝታ መቅረቡም አመቺ እሚሆነው ፍቅረኛው «ወይኔ እስከዛሬ ሳላየው!! ደሞ ይሄ ጠባሳ የምንድንዬ ይሆን? 'ፋየር' ነው አትለኝም!» ስትለው ነው። ከዚያም እሱ ትዝታውን በቦዘ አመለካከት ሲያፈልቅላት፣ እሷ ጡጦ እምታክል አፏን በናፈቁ ዓይኖቿ እያማተረች ስትሰማው ማየት ይቻላል። በቂ ምክንያት ሳይኖር ከብቶች ሣር ሲያበላ፣ ውሃ ሲያጠጣ ወዘተ እያሉ ዝርዝር ውስጥ መግባት ግን የትረካን ውድ ጊዜ ማባከን ነው።

ደጋግሞ የሚታየው ሌላው ቀርነት የማያስፈልጉ ምልልሶችን የሚይዙ መሆናቸው ነው። ምልልስ በመሰረቱ፣ ትረካውን የሚያሽከረክር እስከሆነ ድረስ፣ ለጭብጡ ተገቢነት ያለው እስከሆነ ድረስ፣ ለፈጠራ አጻጻፍ ቀልጣፋ አቀራረብ የሚረዳ ነው። ገፀ ባሕርያት በአነጋገራቸው ይሳላሉ። ብዙ ቃላት ተደርድሮ ሊገለጽ የሚችለው ጠባያቸውና አስተሳሰባቸው ባቋራጭ በትእምርተ ጥቅስ መካከል ይንፀባረቃል። የችግራቸው ሳቢያና የሚፍጨረጨሩለት ውጤት ውጋጋኑ በንግግር ልውውጣቸው ይፈነጠቃል። በምልልስ ድርጊት ይዳብራል፤ ታሪክ ይገፋል።

በነዚህ ጽሑፎች ግን ይሄ አይስተዋልም። ከትዕይንቱ ጋር ዝምድና የሌላቸው ነገሮች ዝም ብለው በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ይቀመጣሉ። በተለይም ከሚወራው ፍሬ ነገር ውጭ የሆኑ ጉዳዮች ያለምክንያትና ያለዓላማ ሲዘረዘሩ ይውላሉ። በዚህ ሁኔታ፣ በማከታተል እስከ አስር ገጽ ድረስ የንግግር ልውውጥ የተጀነጀነበት ድርሰት አጋጥሞኛል።

ቤሳ ልብወለድ በአመዛኙ በአነስተኛ ጥራዝ ቁንጽል ታሪክ ይዘው የሚጻፉትን የሚመለከት ቢሆንም ትልቅ ጥራዝ ያላቸው፣ በቅርጻቸው ወጥ ያልሆኑና የኪነት ላሕይ የተነፈጋቸውና አሰልቺ ሆነው ትልቅ አርእስት የተሸከሙትም የቤሳነት ባሕርይ እንደሚታይባቸው መታወቅ አለበት። በሌላ አነጋገር የቤሳነት ባሕርይ የአጻጻፍ ድክመት እንደመሆኑ

የቃላትና የገፀ ባሕርያት መብዛት፣ ወይም የአስተሳሰብ ክብደትና መታመቅ ብቻውን ምርኩዝ ሆኖ የአንድ ሺ ገፁንም ጽሑፍ ብቁ ሊያሰኘው አይችልም። ጥቂቶቹን እንኳ ለመጥቀስ ለቤሳነት ዋና ዋና ምክንያቶች የታሪክ ጣእም መታጣት፣ በምናብ የሚቀረጽ እይታ መጥፋት፣ የቋንቋ ደረቅነት፣ የትረካ ሂደት መዛባት፣ የገፀ ባሕርያት አለመታወስ ወይም ብሩህ ተደርጐ አለመሳል፣ የድርጊቶች መዝረክረክ፣ የጭብጥ አለመሟላት ናቸውና በነዚህ ቀርነት ያለበት መጽሐፍ የተሟላ ልቦለድ ነው ማለት የኪነጥበብን ዐይን መደንቆል ይሆናል።

የሌሊት ድምፆች

ድምፅ ሕይወት ባላቸው ተንቀሳቃሽ ፍጡራንና ግዑዛን በሆኑ ነገሮች ላይ ነባራዊ የሆነ የተፈጥሮ ክስተት ነው። ከሰው አንስቶ ትንኝን እሚያህሉ ነፍሳት ድረስ የተለያዩ ድምፆች አሉ። የነፋስ፣ የከበሮ፣ የዝናብ፣ የፈላ ቡና ጀበና፣ የፏ ፏቴ ወዘተ ድምፆችም እንደዚሁ ይለያያሉ።

ጥሩ ችሎታና ተሰጥኦ ያለው ዘፋኝ ሲያንጐራጉር፣ ንቦች ሲተሙ፣ ወፎች ሲያዜሙ፣ ነፋስ በጥድ ዛፎች ላይ ሲያፋዋጭ ምን እንደሚሰማን እናውቃለን። የመብረቅ ነጐድጓድ፣ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ፣ የለቅሶ ዋይታ ስንሰማም ምን እንደሚሰማን እናውቃለን።

ድምፅ የቋንቋ፣ ከዚያም በመለስ የምልክት መተላለፊያ፣ የመግባ ቢያ ቁልፍ ነው። የስሜት መለኪያም ነው። ድምፅ የተውኔት ስጋና ደም ብቻ አይደለም። ከብዙው በጥቂቱ የፍቅር ቋንቋ መከሰቻ፣ የሐዘን ብሶት መተርጐሚያም ነው። እንጀራ ያለ ወጥ እንጀራ እንደማይሆን፣ ሲኒማም ያለ ሙዚቃ ሲኒማ እንደማይሆን ያስተውሏል።

ድምፅ ግለሰቦችን ይወክላል ለማለት ይቻላል። የምናውቀውን ሰው በምናባችን ስናስብ ከመልኩ ጋር አብሮ የሚሰማን ድምፁ ነው። ዓይነ ስውራን ሰዎችን የሚለዩት

በድምፃቸው ነው። ሌላው ቀርቶ የአንድን ሰው ድምፅ በሬዲዮ ስናዳምጥ በአካል ምን እንደሚመስል ዝም ብለን ለመገመት እንቃጣለን። ከምስል ጋር አብሮ እንደሚሄድ ሌሎች ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል። ከሰው በአእምሮ ያነሱትንም ብናይ ውሻ ለምን እንደሚያላዝን፣ አህያ ለምን እንደሚያናፋ፣ ዶሮ ለምን እንደሚኮኩል አበክረን ባናውቅም ድምፅ ያለአንዳች ምክንያትና አላማ አየር ሰንጥቆ እንደማይባክን እንገምታለን። ባጭር አነጋገር ድምፅ በራሱ ሕይወት ነው።

ቀኑ ነግቶ እስከሚመሽ ባሉት ሰዓታት በኑሮአችን የሚፈራ ረቂትን ትዕይንቶች በአንድ አባባል እናጠቃላቸው ብንል የቤቱም፣ የውጭውም፣ የሰዉም፣ የእንስሳቱም፣ የመኪናውም፣ የምኑም፣ የምኑም እየተቀያየጠ የሚስማባቸው በመሆናቸው ለድምፅ እምብዛም ትኩረት የምንሰጥ አይመስለኝም። በተቃራኒው ግን በሌሊት የሚሰሙ ድምፆች በጭርታ መሀል ተለይተው ሊታወቁ ይችላሉ። ለሌሊት ድምፆች ትኩረት ሰጥተን እንተንትናቸው ስንል በመሰረቱ አንዳንዶቹ ለጥሩ የእንቅልፍ ሰመመንና እረፍት የመንፈስ ፍስሐ የሚሠጡና የጨለማውን ግርማ የሚያጐላምሱ እንደሚሆኑና አንዳንዶቹ አሰልቺ፣ አስፈሪና ጤና ነሺ እንደሚሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያለብን ይመስለኛል። ከሁለቱም ለመዳሰስ እንሞክራለን።

የቤት ውስጥ የሌሊት ድምፆችን መጥፎ ጐን ሳስበው ለኔ በመጀመሪያ ገዝፎ የሚታየኝና የሚዘገንነኝ የአይጦች ረብሻ ነው። ከነገራቸው ሁሉ በጣም የሚገርመው ቀን ቀን የትም ሲዞሩ ይውሉና ሰው ገና ሊተኛ ሲል፣ እንደውም ሽለብ ሊያደርገው ሲቃጣው መዝለል፣ መጨፈርና ማሸካካት ይጀምራሉ። አልፈው ተርፈው ጤና ለመንሳት የውሸት ንክሻ ሁሉ ይቀጥላሉ። አይጦች ፀጥ ያለውን ሌሊት የሚያደፈርሱት በቡድን እየጮኹ ብቻ አይደለም። በተናጠል ከጓደኞቹ ወደኋላ ቀርቶ ካልጠፋ ቦታ ልክ በራስጊያችሁ ግድግዳ፣ እንቅልፍ ሊጥላችሁ ሴኮንዶች ሲቀሩ በጥፍሮቹ ማገሩን ከመሬት ተነስቶ እሚቧጭር አንድ ከይሲ አይጥ አይታጣም። አመጣጡ ምግብ ፍለጋ ሳይሆን ሰላም ለመንሳት ነውና መፍትሔው ትዕግስት ብቻ ነው።

የቤት ውስጥ ጸጥታን የሚያውኩ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ሕፃን ልጅ ድንገት እሪ ብሎ ሲያለቅስ ወይም ጉንዳን ቤት ገብቶ ቤተሰብ ሲተራመስና ሲንጫጫ መንቃት የመጥፎ ሌሊት እርግማን ነው። እንደሚያንኮራፋ ሰው ግን መፈጠርን እስከሚያስጠላ የሌሊትን ድምፅ የሚያወጣ የለም። አነስ ያለ ማንኮራፋት እንኳን በትራስ ሊስተካከል ይችል ይሆናል። ከበድ ያለው ግን ሰውዬውን ራሱን በወሳንሳ ተሸክማችሁ ውጭ ብታወጡትም ለውጥ ብሎ ነገር ንክች አያደርገውም። የማንኮራፋቱ ሂደት በጧት እንደሚሞቅ የመኪና ሞተር ከሩቅ

እየተነሳ እንደሱዳን ዘፋኞች በረጅሙ ሳያቋርጥ የሚሄድ መሆኑ ደግሞ ከማናደድ አልፎ ያበሳጫል።

በጣም የሚያንኮራፋ ሰው ከነገሩ ሁሉ የሚገርመው ቢቆነጥ ጡትም አይሰማም። ትራስ ቢቆልሉበት፤ አንሶላ ቢነጥቁት፣ ቢገፉት፣ ቢገፈትሩት እንደደግ ነገር ጤና ነሺ ድምፁን በከንፈሩ ጭምር እያረዘመው ይሄዳል።

ችግሩ በነዚህ አያበቃም። ከየትና እንዴት እንደገባ የማይታወቅ መለስተኛ ጢንዚዛ ሊያክል ምንም የማይቀረው ዝንብ በሰኮንድ አስር ሜትር እየበረረ ከግድግዳ ግድግዳ እየተላጋ ያበሽቃችኋል። ካላጣው ቦታ የአፍንጫችሁን ቀዳዳ እየኮረኮረ ሲዝናና ለጠብ የመጣ ሊመስላችሁ ይችላል። በሩንም መስኮቱንም ብትከፍቱ በቀላሉ የሚወጣላችሁ ሞኝ ዝንብ አይደለምና የሚኖራችሁ አማራጭ ኮርኒስ ላይ እስኪያርፍ መጠበቅ ብቻ ነው። የሱን ስትሉ ፊታችሁን በንዴት በጥፊ እምታስመታችሁ ቢንቢ ትመጣላችኋለች። ቀጫጫ ድምጿን ለምን ጆሮአችሁ ላይ ሆነ ብላ መርጣ እንደምትረብሻችሁ ማሰብና መገረም ስትጀምሩ፣ ጭንቀታችሁን በመገላበጥ ለመርሳት ስትሞክሩ፣ ገና ሳይነኩት የሚጮኸው አልጋ በተራው ይቀበላችኋል። እያባበላችሁ ቀስ ብላችሁ ገልበጥ ስትሉበት በጣም ስለሚጮህ ሌሊቱን እረፍት የነሳችሁ ጠላታችሁ ይሆናል።

ከቤት ውጭ ያሉ ድምፆችስ? የዚህ ዋነኛ ተዋናዮች ጮርደሜ ወንዝ ገብተው ሀብተጊዮርጊስ ድልድይ የሚወጡና ሌሊቱን ያለምክንያት በቡድን ሲጮሁ አድረው ጧት ከዱርዬዎች ጋር ፀሐይ የሚሞቁ ባለጌ ውሾች ናቸው። ሌላው ቦታ በሰላም ሲጫወቱ ውለው ልክ ደጃፋችሁ ላይ በማያቋርጥ አስቀያሚ ድምፃቸው ጠብ የሚጀምሩ ድመቶችም አሉላችሁ። ከነሱ ቀጥለው በማያቋርጥ አስቀያሚ ድምፃቸው በዘግናኝ ድምፅ የሚታወቁት ዘራፍ የሚሉ ሰካራሞች ሲሆኑ፣ ሌሊቱን ለማበላሸት ስምንት ሰዓት ላይ ምስማር እየመታ የሚቀሰቅሳችሁ ክፉ ጮረቤትም አልፎ አልፎ ያጋጥማል። ከሁሉ ከሁሉ ግን ምርቃት ከፈለጋችሁ፣ የመሸበት ቁራ ጣራችሁ ላይ ተቀምጦ አይጩህባችሁ። እሳት አደጋ መኪና በአስፋልታችሁ ላይ አይሩጥባችሁ።

የሌሊት ድምፆች ሁሌም በመጥፎ ጐናቸው ብቻ መታየት የለባቸውም። ስንት ደስ የሚሉ ድምፆች አሉ። ለምሳሌ ለሰስ ያለ ዝናብ በምናብ ደስ እያሠኘ ያስጉዛል። ለእንቅልፍ ሰመመን ይለግሳል። ወላጆች የልጆቻቸውንና የራሳቸውን ቤተሰባዊ ደስታ እያሰቡ የዕድሜን ሂደት በተመስገን ለማጣጣም ትፍሥሕት መሳይ ስሜት ቆርቆሮውን ከሚያነጋግረው የውሃ ጠብታ ያገኛሉ። ከሁሉም በላይ ግን የዝናብ ድምፅ ለፍቅረኞች ትስስር ትልቅ አስተዋፅዖ ያደርጋል። ገና የመጀመሪያዎቹ ጠብታዎች ወረድ ሲሉ እጆቻቸው ዓይን ያላቸው ይመስል ይፈላለጋሉ። የልባቸው

ትርታ ጨመር ያደርጋል። ትንፋሻቸው ይቻኮላል። ዝናቡ ሿ እያለ መውረድ ሲጀምር የሞቀው ገላቸው እርስ በርስ ይቆራኝና ከገነት መልካም አታክልት የተወረወረ የሚመስል ሽቶ እዚያው በዚያው ስለሚፈጠር በለመዱት ጠረናቸው ላይ ሲነሰነስ፣ ከዝናቡ ዜማ ጋር የፍቅር ሙዚቃቸው ይሰናኛል። እናም ወደራሳቸው ልዩ ዓለም በደስታ ይጓዛሉ። በቤት ቆርቆሮ ላይ ፍቅር የሕይወት ቅመም የምትሆነው ያኔ ነው። ለሰስ ባለ ፍጥነት እየሾለከ የራሱን ሙዚቃ የሚፈጥር ነፋስም ለሌሊቱ ግርማ ይሆናል።

በከተሞች የሚያስጠሉን ውሾች በገጠር የሌሊት አድማቂዎች ናቸው። ከሩቅ ጋራውን ሲዞር በውድቅቱ ጸጥታ መሀል ድምፁን እያስተጋባ በጥሞና ላሸለበች መንደር 'ደረስኩልሽ' በሚል የከባድ መኪና ድምፅ ጣልቃ እየገቡ፣ የገጠር ውሾች ከየመስኩና ከየኮረብታው ኮራ ባለ ድምፅ በየተራ ሲጮሁ የልጅነትን የተረት ተረት ትዝታ እንደ ቆንጆ ሕልም እያስጌጡ በውብ የእንቅልፍ ሰመመን ያስጉዛሉ። ሌላው ቀርቶ በአውሬነታቸው የሚፈሩት ጅብና ቀበሮ እንኳ የራሳቸው የሆነ አንዳች ደስ የሚል ሁኔታ ለምናብ ይለግሳሉ። ሲር፣ ሲር የሚሉ የሚያበሩ ነፍሳትማ ሌሊቱን በዝምታ ከሚያደምቁት ጨረቃና ከዋክብት ጋር እየተጠቃቀሱ ሲያዜሙ ለሌሊቱ እንደፈርጥ የሚቆጠሩ ትናንሽ ልዕልቶች ሊመስሉ ይችላሉ። በብርሃን እይታ አስቀያሚ የምንላቸው እንቁራሪቶች በጨለማ የሚያሰሙት የሕብረት ድምፅም ለጆሮ ልዩ ስሜት

ይሰጣል። በነዚህ ላይ የዋሽንት ወይም የክራር ስርቅርቅታ በአየሩ ላይ ከተናኘ አንዳች ጥሩ ስሜት በመንፈስ እንደሚርመሰመስ ግልጽ ነው።

የሌሊት ድምፆችን ከሚያስወድዱን መካከል ዶሮዎችም ይገኙበታል። ዶሮዎች ባንዴ እየጮሁ የውድቅቱን ግርማ አያጨናንቁም። አንዱ ኩኩሉ ሲል ሌላው ይቀበለዋል። ዕድሜያቸው ሳይደርስ ገና በትንሽነት አለመጮህቸው አጭር ዕድሜ ቢኖራቸውም ብስለት ያላቸው መሆናቸውን ያሳያል።

ዶሮ በተፈጥሮው ጾም መፈታቱን የሚያበስር ሆኖ የፍስኩ ዕለት ያለ ርህራሄ ታርዶ የሚበላ ምስኪን የአዕዋፍ አንጋፋ ዘር ነው። በሌሊቱ ሂደት የዶሮ ድምፅ የሰማ ሁሉ አንድ ከቡና ጀበና የማይበልጥ ፍጡር እንዴት ንጋት ላይ ኮራ ካለ ጉሮሮው ያንን ኃይለኛ ድምፅ ያወጣል ብሎ መገረሙ አይቀርም። የጮህን መቅደድ አብሣሪ ስለሆነም ጣፋጭ ዜማ ያላቸው ጥቃቅን ወፎች አርአያ እንዳደረጉት ይኖራሉ።

እና ጭር ባለ ሌሊትም ሆነ ብዙ ድምፆች ተቀላቅለውና ተስተጋብተው በሚሰሙበት ወቅት ከሩቅ የሚሰማውን ነጮድጓድና የዝናብ አመጣጥ ከዶሮዎች ኩኩሉና ከጤነኛ ውሾች የሩቅ ጩኸት ጋር በሰመመናዊ የሕሊናችን ጓዳ ለአንዳፍታ ዝም ብለን ብናስብ አንዳች ደስ የሚያሰኝ ስሜት ሊያድርብን ይችላል።

ከሌሊት ድምፆች ሁሉ በከተሞች ጉልሁን ሥፍራ የሚይዙት የመስጊድ አዛን፣ የቤተክርስቲያን ደወልና ቅዳሴ ናቸው። የሌሊቱ ውጋጋን በምሥራቅ ደም መስሎ መታየት ሲጀምር፣ ወፎች ዜማቸውን ለማንቆርቆር ሲዘጋጁ በሚጣፍጥ የእንቅልፍ ሰመመን መሀል ምዕመናን የሚናፍቁትን ድምፅ የሚሰሙት ያኔ ነው። የሌሊቱ ግርማ ይጐላል። ይሄ ነው የማይሉት ውስጣዊ ትፍስሕት በደካከመ ሰውነት ጫና ይተካና ብሩህ ተስፋ እንደምንጊዜውም እዛው በዛው መለምለም ይጀምራል። ጐህ መቅደዱ ነው። ሌላ ቀን ይጀመራል። የጧት ስራ፣ ወይም ስራ ፈትነት በግማሽ እንቅልፍ ጭጋግ ምናብ በለመደው የብርሀን ጮራ ታጅቦ ከፊት ይደቀናል። የዛሬ ውሎ እንዴት ይሆናል? ትናንት የተያዘው ጉዳይ ምን መቋጫ ይኖረዋል? የቱ ይቅደም የቱ ይከተል? ይሳካል ወይ አይሳካም? ይሄን ይሄን ለማሰብ ጊዜ የለም። ምንም ይሁን ምን፣ ሌላ ንጋት ግን አለ። ሌላ የሌሊት ድምፅ አለ። የቤተክርስቲያን ደወልና የመስጊድ አዛን ሁልጊዜ ይቀጥላሉ —እስከ ምጽአት እስከ ዮምአልቂያማ። ከሁሉ በፊት ግን «ተመስገን ጌታዬ በቀኝ ያሳደርከኝ በቀኝ አውለኝ!»፤ «ኢንሻላህ! አልሃምዱሊላሂ ረቢልአዓለሚን» —አሜን።

የዋጋ ተመን ጉዳይ

ከአነስተኛ ቸርቻሪዎች አንስቶ እስከ ትላልቆቹ (ማለትም አስመጪና አከፋፋዮች) ድረስ ባለው የንግድ መስመር የሚታየው የዋጋ ውጣ ውረድ ጉዳይ ወደፊት በመንግስትና በሕዝብ ትብብር አማካይና ተገቢ አቅጣጫውን እንደሚይዝ ተስፋ ብናደርግም ችግሩን ከምናየውና ከምንሠማው እያጠናቀርን ማቅረብ የኛ የሸማቾቹ ድርሻ ነው።

ችግሩ ሁልጊዜም የገበያተኛው ብቻ ነው ማለት አይደለም። ነጋዴውም ሸማች መሆኑ አይቀርምና የማማረሩ ዕጣ ሁሌም ባይሆን በመጠኑ እንደሚደርሰው መታወቅ አለበት። ባለሱቁ ለምግቡ ጤፍ ያስፈልገዋል። የጤፍ በረንዳውም ሰው ከባለሱቁ ክብሪት መግዛቱ አማይቀር ነው። ለአንዷ ክብሪት ሃምሳ ወይም ስድሳ ሳንቲም ማውጣቱን በራሱ የዋጋ ተመን የሚያካክስም እንኳን ቢሆን በክብሪት እንጨቶቹ መጉደል ስለሚጐዳ ቶሎ ቶሎ እያለቀበት ደጋግሞ ይገዛል ማለት ነው።

በርግጥ የገበያው ጉዳይ ሻጮቹን እንደገዥዎቹ አይጫናቸውም። ከጠበሉ ግን በጥቂቱ ይደርሳቸዋል። የጫማ ሱቅ ያለው ግለሰብ ልብስ ከሌላ ቦታ ይገዛል። ሌላው ቀርቶ ልብሳልብስ የሚነግድ ሰው እሱ ጋ የሌለውን ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ አንዱ ጋ ሄዶ ይመርጣል። ይሁን እንጂ ጉዳዩን ከሞላ ጐደል እናጠቃለው ቢባል አብዛኛው ነጋዴ በሌላው ገበያ

የሚጐዳውን በራሱ «እጥፍ ድርብ አሻሻጥ» አካክሶ የችግሩን ሚዛን በራሱ ዘዴና መንገድ ያስተካክለዋል ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ቤት የሚሠራ ነጋዴ ለሚስማር፣ ለድንጋይ፣ ለመስተዋት፣ ለአሸዋ እና ለመሳሰለው የሚያወጣውን የናረ ክፍያ በኛ በሸማኞች ላይ ላካክስ ብሎ ሲነሳ፣ የሚቆለልብን የዋጋ ክምር የቱን ያህል እንደሚሆን እስቲ ላንዳፍታ ይታያችሁ።

እኔ ከሚገርሙኝ ብዙ ነገሮች መካከል አንዱ የዋጋ መናር ጉዳይ እንደሰንሰለት የተያያዘ ወይም በተለያዩ አቅጣጫዎች የተደጋገፈ መሆኑ ነው። ውረድ ተዋረዱ ከላይ ወደታችም ቢሆን የጐንዮሽ ግንኙነት መኖሩ ደግሞ የተለየ ጥናት ሳይጠይቅ አይቀርም። እኛ በቅርቡ ከምናውቀው እንኳ ብንነሳ ብዙ የምንገነዘበው ውስብሳቤ አለ። እንጨት ሲጠፋ ከሰል ይቀጥላል። ከሰል ሲጠፋ ደሞ አሀያ እሚያስሮጠው ጭራሮ እንጨት ይወደዳል። ባትሪ ድንጋዩ ጥሩ የሬዲዮ ፕሮግራም አለ ሲባል ዋጋው ይቆለላል። እንዲያውም ያችን ወቅት ጠብቆ ከባድ ዝናብ ይዘንብና መብራት ይጠፋል። የሻማው ዋጋ ሰማይ ይወጣል። ወሬ ማስወራትም አንዱ የነዚህ ተጓዳኝ ዘዴ ነው። «እንትን ሊጠፋ ነው። ቶሎ ገዝተህ አስቀምጥ» ከተባለ ሸማቹ ባጋጠመው ተመን ገዝቶ ያስቀምጣል። እነ ጌሾና በርበሬማ ዓውዳመት ሊመጣ ሲል ብርቅ እየተደረጉ ለጆሮ ይቀርባሉ። እና በሆነው ዋጋ በችኮላ ይቸበቸባሉ።

እንደምታውቁት ለብዙ ነገሮች ደጋፊ የሚሆኑ ሰዎች በንግድ ዓለም ይፈለጋሉ። ቲፎዞዎች ልንላቸው እንችላለን። አንዱ አንድ ጊዜ ሁዋይት ሆርስ ውስኪ ሊሸጥ የተጠቀመው በቲፎዞዎች ነበር። በየትላልቁ ቡና ቤት እየገቡ «ሁዋይት ሆርስ የለም? በቃ እንሂድ!» የሚሉ ሰዎች በብዛት ከተማው ውስጥ አሰማራና ተፈላጊነቱ ተጋኖለት፣ ዋጋ ቀጥሎ፣ ዚታም ሙሉ ውስኪውን በጥቂት ቀናት እንደሸጠ ይነገራል። አንድ ሰሞን ደሞ ከተማችን ፊኛ ብቻ ሆኖ ነበር። ዓዋቂው ሁሉ የላስቲክ ፊኛ እየነፋ ሲሄድ የተመለከትኩ ይመስለኛል። የሱ ነገር ግን፣ የቲፎዞ ይሁን የሌላ፣ ምስጢሩ እስከዛሬ ተሰውሮብኛል። ንግድ ዓለም ውስጥ በትንሹ አጮልቀን እንይ ካልን ስንት በውድ የመሸጥ ታክቲክ አለ መሰላችሁ? ውድ ነው ብላችሁ ስትከራከሩ እናንተን የመሰለ ገዥ «እስቲ አምጣው!» ብሎ ይመለከት፣ ይመለከትና ሁለት ሶስቱን ከፍሎ ይዞ ይሄዳል። እውነቱን ነው ብላችሁ እናንተም እንደዚያው ታደርጋላችሁ። ሰውዬው ግን ጓደኛው ነው። በኋላ ይመልስለታል። እንዴትስ ታውቃላችሁ? ማንስ ይነግራችኋል? «የመኪና ዕቃ መለዋወጫ ጠፋ» የሚባባሉ በጣም የሚግባቡ ሰዎች ድምፃቸውን አጥፍተው ስንት የሚጫወቱት ጨዋታ አለ?! እና ሁሉ ነገር መወደዱን እየተራገመ ሽማቹ ላይወድ ይበዘበዛል። በተለይ በምግብ ነክ ረገድ ያለው የገበያ ሁኔታ እጅግ አስመራሪ ነው። ጭብጥ ምስር ክክ፣ ለራት የማይበቃ የወር ጮመን፣ ቀጫጫው ድንች ሁሉ ዋጋው ሰማይ

ወጥቷል። ያልተወደደ ነገር የለም። ካለፈው የደርግ ዘመን የወረስነው የረከሰ ነገር ቢኖር ችግርና ረኃብ፣ ስቃይና ብሶት ያልተለየው፣ በዚያም ሳቢያ ማህበራዊ ፍቅርንና ልባዊ ፈገግታን የረሳ፣ ሰብዓዊነትን የተነፈገ ህልውና ብቻ ነው ለማለት ይቻላል።

በውነቱ አንዳንዴ የዋጋ ሁኔታ እንዴት እየቀጠለ እንደሄደ ስታስቡት ትገረማላችሁ። "ዕቃው በራሱ ኃይል እዚያ ላይ ደረሰ እንዴ?" ብላችሁ የማይመስል ግምት ውስጥ ትገባላችሁ። ለምሳሌ የመጸዳጃ ወረቀት (በተለመደው አጠራር ሶፍት) ከደርግ ዘመን በፊት አርባ ሳንቲም ነበር። ኢሠፓ አስከፊ ማኮብኮቡን ገና ሳይጀምር አንድ ብር ከሀያ አምስት ሳንቲም ገባ። "እጥረት ይኖር ይሆን? ወይስ ለውጡን ምን ነካው?" አልንና ምክንያቱን ለማወቅ ጓጓን። ቄሱም ዝም የደርጉም መጽሐፍ ዝም ሆነ። በኋላ አንድ ብር ከሰባ አምስት ሳንቲም፣ሁለት ብር ሲገባ፣ «አቅርቦት» የሚለው ነጃሳ ቃል የማይጠፋበትን፣ ጦርነቱን ምኑን እያስታከኩ ወረቀት እስኪጠፋ ድረስ ወረቀቱ ላይ የውሸት ስታቲስቲክስ ይቸከችኩበት ጀመር። ሳንወድ የአስራ አምስት ሳንቲም ጋዜጣ መግዛቱን መፍትሔ አደረግነው። ከዚያ እንዲያ፣ እንዲያ እያለ አራት ብር ሲደርስ እንደነጋበት ጅብ ተደናግጠን እርማችንን ዋጥነው። እንደዚያው ሆኖ ብዙ ቆየ። «መፍትሔው ምንድነው?» ብለን በየቤታችን ማጉረምረም ስንጀምር «በአቅምህ መጠን በቁጠባ ኑር!» የሚል ጽሑፍ፣ በየሆስፒታሉ

ሳይቀር፤ የጦር ጉዳተኞችና ወደአፓራሲዮን ክፍል በጋሪ የሚገፉ ሰዎች ጭምር እንዲያነቡት፣ በየኮሪደሩ አስደንጋጭ ቀይ ጽሑፍ ተለጠፈ። ያኔ ፍጹም አልገባን አለ። «መረቀቱ ወፍራም ሆነ እንጂ በሶፍት ፋንታ የነሱን መፈክር እየቀደዱ መጠቀም ነበር» የሚለው የአንድ ወዳጄ የምሬት አነጋገር በዚህ አጋጣሚ ትዝ ይለኛል። አሁንም ቢሆን የሶፍት ዋጋ አለመቀነሱ እንደገረመኝ ነው።

ሌላው ስለዕቃዎች ዋጋ መቀጠል ሳስብ ድንቅ የሚለኝ ነገር ዋጋቸው ሲጨምር ጥራታቸው የማቆልቆሉ ጉዳይ ነው። አንዳንዱ ሳሙና ዋጋ ሲጨምር በደንብ አያጠራም። በተለይ ከበርበሬ ጋር ስምም ይሆንና ሁለት ሶስቴ እሹኝ ይላል። የሆቴል ቤቶች የመታጠቢያ ወረፋ ደሞ አንዱ ለማሸትም እንኳ ጊዜ አይሰጥም። የስክሪፕቶ ደማቅ ቀለም ሆነ ብሎ መደብዘዝ የጀመረው አንድ ብር በገባ ጊዜ ነው። ዳቦና ፓስቴን ጨምሮ የሆቴል ምግብ ሁሉ ዋጋው በናረ ቁጥር ጥራቱ ቀንሷል። የመጠን ማነስም አለ። ለምሳሌ ድራፍት፣ ቢራ፣ ሻይ፣ቡና... ሻጮቹ በዝግ ስብሰባ አጀንዳ ይዘው የተነጋገሩባቸው ይመስል፣ ጭማሪ ከተደረገባቸው ቀን ጀምሮ ጐደሎ እየተደረጉ እንዲሸጡ በጠጪዎች ላይ ከተፈረደ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ከዚህ ጋር ሳናነሣ የማናልፈው ዕቃና ሸቀጥ የማስወደድ ብልሀትና በተለያዩ ፈጠራዎች የመጠቀም ስልት ነው። ይህም በአቀራረብ (ማለትም የተለየ በማስመሰልና)

በማደበላለቅ ይካሄዳል። በመጠን ከቀድሞው የማይበልጠው ክትፎ «ስፔሺያል» ተብሎ ጐመንና ዐይብ ከተጨመረበት ክፍያው ይቀጥላል። ስጋ ጥብሱም ከሶስት አራት ካሮት ጋር ከተጠበሰ እንደዚሁ አንዱን ከሌላው ማደባለቅም ለትርፍ ትርፍ ያዋጣል። «ጐመን በሥጋ» ዓይነት ሲሆን ለማለት ነው። ብቻ በዚህ ረገድ ጐመን በሩዝ፣ ድንች በዐይብ፣ቅንጬ በካሮት እየተባለ ሳይቀርብልን ይቀራል?

"ስፔሻል" የሚለው ቃል "ሱፐር" ከሚለው ይበልጥ የትም የሚሰማ፣ የትም የሚገባ መሆን ከጀመረ ቢያንስ ሦስት ዓመት ያልፈዋል። ከቆሎ ብስተቀር በምግቡ በመጠጡ ሁሉ አለ።

አንድ ነገር "ስፔሻል" መባሉ ብቻ ግን ስፔሻል አያደርገውም። ለምሳሌ አፕሬቲቭ «ስፔሻል» እንዲባል ኮምጣጤና ቁራጭ ሙዝ ደሞ አንዳንዴ ደስ ብሎን እንድናይ መንደሪን፣ ብርቱካን ተቆራርጦ ይጨመርበትና እንደስሙ "ስፔሻል" ይደረጋል። እና እሚያስደምማችሁ ነገር ምን መሰላችሁ? የአታክልቱ ቁርጥራጭ ሲጨማመርበት አፕሬቲቩ ከፍ ማለት ይጀምራል። ቶሎ ብለው አምቦ ውሀ ሲጨምሩበት፣ ብርጭቆው የድራፍት እንደመሆኑ ልክ የድራፍትን ያህል ከፍ ስለሚል አዲስ ነገር ይመስላል። ታዲያ ሃምሣ ሳንቲም ያስጨምራል እንጂ ከ «ኖርማሉ» ምንም ልዩነት የለውም።

የዕቃዎች ውጣ ውረድ ጉዳይ ገበያተኛን ሁሉ ይመለከታል። የኑሮ ደም ስር ያለው ከዚያ ነው። አንዳንድ ሰዎች ግን ከማንም ይበልጥ ይከታተላሉ። ዋጋ ማጠያየቁን እንደልማድ ያደርጉታል—የሚፈልጉትንም የማይፈልጉትንም ሳይመርጡ። ወሬው እቤታቸው ቁጭ እንዳሉም ይመጣላቸዋል። በተለይ ሴቶች በዋጋ ከፍታና ዝቅታ ላይ ጥብቅ ናቸው። ለከሰል የሚልኳትን ልጅ ሳይቀር ብዙ ነገር አስጠይቀው የዕለት ተዕለቱን ተመን ይከታተላሉ። በዚህ ዓይነት፣ በየቀበሌው፣ «እስቲ እሷን ጠይቁ» የሚባሉ ዋጋ ነጋሪ ሴቶች አልፎ አልፎም ቢሆን አይታጡም።

ቢሆንም ግን ከሴቶች ይበልጥ የገበያውን ጉዳይ አበጥሮ እሚያውቅ ወንድ እማይኖር እንዳይመስላችሁ። ባለፈበትና ባገደመበት አቅጣጫ ሊገዛ ያላሰበውን የልጆች ልብስ ብድግ አድርጎ «ስንት ነው?» የሚል፣ ያጋጠመውን ልብስ ለክቶ ዋጋውን የሚያጣራ፣ ታክሲ ውስጥ ከየበረንዳው የተገዙ ዕቃዎችን «ለመሆኑ ስንት አወጣ?» እያለ የሚያጠያይቅ አለ። እንዲህ አይነቱ ሰው ገዥና ሻጭ ሲከራከሩ ያለስራው ቆሞ ቢያዳምጥ ደስ ይለዋል። ፀጉር አስተካካይ ወዳጆቹ ጋ ገና ገባ ብሎ፣ ባዶ ወንበር ላይ እንደተቀመጠ፣ ፂሙን በመቀስ ነካ ነካ እያደረገ «ቡና ስንት ገባ አሉ እጣክህ? ጤፍስ?» ማለትም ይቀናዋል።

476/2000



ሚጋ አሳታሚ ድርጅት

ዋጋ ብር 8.90

በሚጋ ማተሚያ ድርጅት ታትሟል